# በማቴዎስ ወንጌል

# ትምህርቶች ላይ

# የተመሠረተ

# የመጽሐፍ

# ቅዱስ

# ጥናት

**EEBC March 2016**

# ምስጋና

ይህን ጥናት በማዘጋጀት፣ በማሰልጠንና በማረም ያገለገላችሁትን ወገኖች ጌታ በነገር ሁሉ አብዝቶ ይባርካችሁ። (መዝ 20፥1-8)

የጥናት ቡድኖችን የምታስተባብሩ አስተባባሪዎች እና ጥናቱን የምታስጠኑ መሪዎች ሁሉ ጌታ ሁለንተናዊ ስኬት እንዲሰጣችሁ የዘወትር ጸሎታችን ነው። ለረዥም ጊዜ በየሳምንቱ ተሰጥታችሁ ስለምትፈጽሙት አገልግሎት ጌታ ብድራታችሁን ይክፈል።(1 ቆሮ 15፡58)

ይህን የቡድን ጥናት መጽሐፍ ለመሥራት የቤተ ክርስቲያኒቷ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዝግጅት ክፍል የበኩሉን ጥረት አድርጓል። ይህ የጥናት መጽሐፍ ለጌታ ክብር በህይወታችን ለበረከት እና በአገልግሎታችን ለብዙ ፍሬ ምክንያት ይሁንልን።

የኢትዮጵያውያን ወንጌላዊት ባፕትስት ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ክፍል

# የማቴዎስ ወንጌል ጥናት

## የጥናቱ አጠቃላይ መግቢያ

መጽሐፍ ቅዱስ 66 የተለያዩ መጽሐፍቶችን የያዘ ሲሆን 39ኙ በብሉይ ኪዳን እና 27ቱ በአዲስ ኪዳን ይገኛሉ። የማቴዎስ ወንጌል ከአዲስ ኪዳን 27 መጽሐፍት በቅደም ተከተል የመጀመሪያው ሲሆን ከሶስቱ ተመሳሳይ ወንጌላት ማለትም ማርቆስና ከሉቃስ አንዱ ነው። ይህ ወንጌል የተጻፈው በመጀመሪያው ሃምሳዎቹ ዓ/ም እንደሆነ ይታወቃል። ከብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ብዙ ጥቅሶች ከተጠቀሱበት የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት አንዱ ነው።

ይህ ወንጌል የተጻፈው ከ12ቱ ደቀ መዛሙርት በአንዱ ሲሆን ጸኃፊው ክርስቶስን ከማወቁ በፊት ቀራጭ ነበር። ስሙም ሌዊ ተብሎ ይታወቅ የነበረው ማቴዎስ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። እንደሚታወቀው በአይሁድ ህብረተሰብ ቀራጮች ብዙ ተቀባይነት ያላቸው ሰዎች እንዳልነበሩ የታወቀ ነው (ሉቃ 5፡27-32 ይነበብ) ።

የማቴዎስ ወንጌል የቅርብ አድማጮቹ ወይም ተቀባዮቹ አይሁዶች ሲሆኑ ከንጉስ ዳዊት ዘር የተወለደ ክርስቶስ መሲህ ወይም ሌሎችን ለማዳን የተቀባ ንጉስ መሆኑን ማስተማር ነው። በዚህም ምክንያት ከሉቃስ ወንጌል በስተቀር በሌሎች ወንጌላት የማናየውን የክርስቶን የዘር ሀረግ ከሉቃስ በተለየ አቀራረብ ተጽፎ እናገኛለን (ማቴ 1፡1-17)። ይህ አዳኝ ደግሞ እንደ እንደ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የተወለደ የዳዊት ዘር እና የአብርሃም ዘር እንደሆነ ማቴዎስ ነግሮናል። ወንጌል ለዓለም ሁሉ የተሰጠ የምሥራች እንደሆነ የሚናገር ታላቁ ተልዕኮ ያለበት መጽሐፍ ነው (ማቴ 28፡19-20) ።

ይህ ወንጌል 28 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን ከምዕራፍ 1፡1-4፡11 በክርስቶስ ማንነት ላይ ያተኮረ ትረካ ሲሆን ከምዕራፍ 5-28 ደግሞ ክርስቶስ በድርጊት ጀምሮ ትምህርትን እያፈራረቀ በማስተማር አገልግሎቱን ያጠቃለለ መሆኑ የሚያሳይ ነው። በአጭሩ የመጽሐፉ ሁለተኛ ክፍል በአምስት ታላላቅ የገላጻ ትምህርቶች ላይ የተመሠረተ ሲሆን የመጨረሻ 28፡16-20 ያለው ክፍል መደምደሚያ ትምህርት እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። ትምህርቱም የሚገኘው በማቴ ከምዕራፍ 5-7፣ማቴ ምዕራፍ 10፣ ማቴ ምዕራፍ 13 ፣ ማቴ ምዕራፍ 18፣ ማቴ ምዕራፍ 23-25 እና መደምደሚያው ማቴ 28፡16-28 ይሆናል። ይህ ዓይነት መዋቅር ሆነ ተብሎ የተቀነባበረ መሆኑን የወንጌል ተርጓሚዎችና አስተማሪዎች ይስማማሉ። ወንጌሉ መግቢያና (ማቴ 1-2) ብርቱ ጥሪ የሚያቀርብ መደምደሚያ አለው (ማቴ 28፡16-20) ።[1]

በተለይም የተራራውን ስብከት ማቴ 5-7 መመልከት ጥሩ ማስረጃ ይሆናል። ያህዌ ለሙሴ ሙሴም ለእስራኤላዊያን ህግን እንደሰጠ (ዘጸ 19-20)[2] ጌታ ኢየሱስም ለደቀ መዛሙርቱ ለሌሎች እንዲያስተምሩ ይህንን የአዲስ ኪዳን በጸጋ የተሞላ ህግ አስተማረ። ክርስቶስ በማቴዎስ በወንጌል ያስተማረው ጠንካራ ትምህርት ለአዲስ ኪዳን መሠረታዊ የህይወት መመሪያ ነው። እስራኤላዊያን ህግን መጠበቅና ማስተማር ይጠበቅባቸው እንደነበረ ሐዋርያትም ከጌታ የተቀበሉትን ህግ እንዲጠብቁና እንዲያስተምሩ ታዘዋል።

**<u>ጸሎት፡-</u>** ይህን መጽሐፍ ስናጠና ጌታ በመንፈሱ እውነተኛ ደቀ መዛሙርት እንድንሆን ይርዳን ደግሞም በተለያዩ ችግሮቻችን ላይም የእርሱ

[1] ስለ አወቃቀር የተሻለ ለማወቅ በመጨረሻ ገጽ ስለ ማቴወስ ወንጌል አወቃቀር የተጻፈውን ተመልከቱ።
[2] ጊዜ ሲኖራችሁ ለተጨማሪ እውቀት አዲሱን መደበኛ ትርጉም ገጽ 1432 ይመልከቱ

እጆች በመካከላችን ለበረከት እንዲሆንና እንዲሁም ይህን ታላቁን ታልዕኮ ለሌሎች ለማካፈል ክብራችንን እንድንተው ጸጋው ይርዳን። አሜን!

## የመግቢያ ጥናት የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከማቴዎስ ወንጌል ጥናት በፊት ካጠናችሁ ጥናት ምን እንደ ቀረላችሁ አካፍሉ።
2. ስለ ማቴዎስ ወንጌል የምታውቁትን ነገር ለቡድኑ አካፍሉ
   ለምሳሌ፡-
   ፩. ይህ ወንጌል በዋናነት በወቅቱ የተጻፈው ለማን ነው?
   ፪. የክርስቶስ የዘር ግንድ መዘርዘሩ ለምን ይጠቅማል?
3. ሉቃ 5፡27-32 በማንበብ ስለ ማቴዎስ ምን እንደተረዳችሁ ተወያዩ
   ፩. የአይሁዳዊያን ችግር ምን ነበር
   ፪. ጌታ ወደ ምድር የመጣበት ዓላማ ምንድ ነው
4. በማቴዎስ ወንጌል የተጠቀሱትን አምስቱን የትምህርት ክፍሎች ጥቀሱ (በቃላችሁ ለመያዝ ሞክሩ) የትምህርቶቹን መደምደሚያዎች በምን እናውቃለን?
5. የማቴዎስ ወንጌል ከሙሴ የህግ መጽሐፍት ጋር እንዴት ሊነጻጸር ይችላል። ልዩነቱና አንድነቱስ ምንድ ነው?
6. ጥቂት ደቂቃዎችን ወስደን ከዛሬ ጀምሮ የሚኖረን የጥናት እና የኅብረት ጊዜ የበረከት እንዲሆንልን በጌታ ፊት እንጸልይ።
   ጌታ በታላቅ ሞገሱ ከእኛ ጋር ይሁን!

# የማቴዎስ ወንጌል ትምህርቶች ጥናት
# ክፍል አንድ
# ጥናት አንድ
# ማቴ 5፡1-16

**ዓላማ፡-** የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋዎች ባህሪያትን፥ የደስታቸውን ፍሬና ሊያስከፍላቸው የሚችለውን ዋጋ በማሳየት፤ የራሳችንን ህይወት እንድንመረምር ማሳሰብ።

**መግቢያ፡-**

የማቴዎስ ወንጌል የመጀመሪያ ትምህርት ያለው በማቴ ወንጌል ከምዕራፍ 5-7 ባለው ክፍል ነው። ይህም ክፍል የሚገኘው "የተራራው ስብከት" ተብሎ የሚታወቀው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ሲሆን የሚከተሉትን ሶስት ዋና ዋና ትምህርቶችን ይይዛል። የመጀመሪያው ስለ ብጹዓን የተነገረ (ማቴ 5፡1-12) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ስለ ሥነ ምግባር የተሰጠ ትምህርት (ማቴ 5፡13-20፣ማቴ 6፡1-7፡23) እና ሶስተኛው ክፍል ደግሞ በኢየሱስ የስነ ምግባር ትምህርትና በአይሁዶች ወግ መካከል ያለው ተነጻጻሪነትን የሚያስተምር ትምህርት ነው (ማቴ 5፡21-28) ። በመጨረሻም ትምህርቱ የሚያጠቃልለው ትምህርቱን በሥራ ላይ ማዋል ምን ያህል እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በመንገር ነው (ማቴ 7፡28-29) ።

በማቴ 5፡1-2 የምንመለከተው የመከፈቻ አሳብ ከዘጸአት 20፡21 ጋር የሚመሳል ነገር አለው። በዘጸአት 20፡21 እግዚአብሔር በተራራው ላይ፥ ህዝቡ ርቀው ቆመው፥ ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ቀርቦ እንደበረ ተዘርዝሯል። በማቴ 5፡1-2 ደግሞ ኢየሱስ በተራራው ላይ ሆኖ ፥ ደቀመዛሙቱ እና ህዝቡ ሰብስቦ አፉን ከፍቶ ሲያስተምራቸው እናያለን።

ይህ የሚያሳየው 1) ኢየሱስ ያኔ በሲና ተራራ የተናገረው ያህዌ እርሱ እንደሆነ ወይም ከእርሱ ጋር አንድ እንደሆነ 2) ደቀ መዛሙርቱ የሙሴ

አገልግሎት እንዳላቸው 3) አሁን ኢየሱስ በዚህ ስብከቱ የአዲስ ኪዳንን ህግ ለደቀ መዛሙርቱ እየሰጠ መሆኑን ያሳያል።

**ትምህርቱ ማቴ 5፡3~16**

ይህ ክፍል የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ የሆነ አማኝ የሚኖረውን ባህርያትና ከዚህ የተነሳ ስለሚከፍለው ዋጋና በምድር በመኖሩ ለሌሎች የሚያመጣውን ጥቅም ያሳስበናል። ስለዚህ ክፍሉን በሁለት ኑዑሳን ክፍሎች በመክፈል እናጠናዋለን።

**የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ ባህርያት ማቴ. 5፡3~10**

እያንዳንዱ ቁጥር ሁለት አርፍተ ነገሮች አሉት። የመጀመርያው ከደቀመሙርት የሚጠበቅ ሲሆን፥ ሁለተኛው እግዚአብሔር የሚሰጣቸው በረከት ነው። ቁ3 እና 10 በረከቱ የእግዚአብሔር መንግሥት የእነሱ ናትና ይላል። ይህ ክፍሉ በራሱ የሚቆም መሆኑንና የዚህ ክፍል ርዕሰ ጉዳይ የእግዚአብሔር መንግሥት መሆኑን ያመለክትል።

በማቴ 4፡17 ላይ ኢየሱስ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች ብሎ ስብኮ ነበር። አሁን የዚህ መንግሥት ዜጋ ህይወት ምን እንደሚመስልና ምን እንደሚጠይቅ ያስተምራል።

በማቴ. 5፡3~10 **ስምንት** አርፍተ ነገሮች አሉ። የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች እነዚህን አረፍተ ነገሮች እንደሚከተለው በአራት ክፍል ይከፍሏቸዋል። መሰረታዊ አከፋፈሉ ይዘት በመንግሥት ልጆች ባህርያትና ህይወት ላይ ያተኮረ ነው።

- ስለራሳቸው ያላቸው እይታ (ማቴ. 5፡3)፤
- ስለኃጥያት ያላቸው እይታ (ማቴ. 5፡4-6)፤
- የጌታን ባህርይ እንዴት እንደሚያንጸባረቁ (ማቴ.5፡7-9) እና
- ልዩ መሆን የተነሳ ዋጋ እየከፈሉ መኖራቸው ላይ ያተኩራሉ ((ማቴ.5፡10፣ 11-16)።

## ፩ኛ. በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና

ሚዛናዊ ትርጉምን ለመጨበጥ የብሉይ ኪዳንን አሳብ መመልከት ተገቢ ነው። በኢሳያስ 61:1-3 የመሲሁ አገልግሎት እንደነዚህ ያሉትን መደገፍ መሆኑን ተተንብዮ ነበር።

በመንፈስ ድሆች የሆኑ ከጉድለት ጋር ተያይዞ አንድ ሰው የሚገኝበት ሁኔታ አይደልለም። አለም በምታስቀምጠው መስፈርት መንፈሰ ደካማ ከመሆን ጋር የተያያዘም አይደለም። እንደውም ሁሉ እያለው እንደሌለው ሆኖ መገኘት ነው። ይህ ባህርይ በውስጡ ለሰማዩ መንግሥት የሚያበቃቸው የራሳቸው ነገር እንደሌላቸው ሙሉ ለሙሉ የመገንዘብና መንፈሳዊ ድህነትን መለየት ነው።

ስለዚህ እንደነዚህ ያሉ ሰዎች በዚህ አለም ያላቸው አንዳች ነገር ለመንግስቱ ሊያበቃቸው እንደማይችል የተረዱ ሰዎች ባህርይ ነው። የትህትና ልብ ያላቸው፤ ተስፋቸውን በጌታቸው ላይ ብቻ ያደረጉ መንፈሳዊ አይኖቻቸው የበራላቸው ናቸው። ስለዚህ "በመንፈስ ድሆች" ማለት የተሰበረ መንፈስን ያላቸውንና አዳኝ፣ መድህን እንደሚያሻቸው የተረዱ ሰዎችን ያመለክታል። እነዚህ ንሰሃ የገቡና የሚገቡን ከጌታ ጋር እውነተኛ ኅብረት ያላቸውን በትዕቢት የማይነዱን ሰዎች ናቸው።

ሁሌ የእግዚአብሔር ልብ፣ ምህረቱና ጸጋው ድካማቸውን ተረድተው ወደርሱ ወደሚጠጉ ነው።(መዝ 40:17፤ ምሳሌ 29:23)

ይህ ባህርይ ጅማሬው አዳኝን በመፈለግና በመቀበል፥ በእምነት ተጀምሮ በዚሁ መንፈስ የሚቀጥል ህይወት ነው። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚገባው በእምነት ነው። የነዚህ ብጽዕናቸው፥ ደስታቸው የመንግስቱ ወራሽ መሆናቸው ነው።

## 2ኛ የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፥ መፅናናትን ያገኛሉና።

በኢሳያስ 61:1-3 መሲሁ የተሰበረ ልብን እንደሚጠግን ይናገራል። እንባቸው እንደሚታበስ ውርደታቸው በደስታ ዘይት እንደሚለወጥ ይናገራል። በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ሀዘን ከዕለት ኑሮ ጉስቁልና ያለፈ ነው።

የሚያዝኑ የሚላቸው መተላለፍን፣ እግዚአብሔርን ማሳዘንን ከማሰብ ጋር የተያያዘ ሀዘንን ይጨምራል።

ዛሬ የሀዛናችን ምክንያት ምንድን ነው? ከአዘንንስ ወዴት ነው የምናቀርበው? በምንስ መንፈስ? የጌታን ልብ በሚያሳዝነው ጉዳይ፤ ስለኃጢያት የሚያዝኑ መፅናናትን ያገኛሉ። የመንግሥት ልጆች ሀዘን ወደ ትንሳኤ የሚያመራ ሀዘንን ነው።

ስለራሳቸውና ስለ ዓለም ኃጢያት የሚያነቡ፥ እንባን ከሚያብሰው ጌታ የእንባቸውን ፍሬ ያገኛሉ (ኢሳ 62:1 ኤርምያስ 33:14-16)። ዛሬ ነፍሳችን የምታዝነው ሀዘን ምን አይነት ሀዘን ይሆን?

## 3ኛ የዋሆች ብፁዓን ናቸው፥ ምድርን ይወርሳሉና።

የዋህ ሰው ራሱን የሚገዛ፥ የሰከነ፥ ትዕቢትና ሌላውን የመናቅ መንፈስ ያልያዘው ነው። የዋህ የሆነ ሰው ራሱን ዝቅ ቢያደርግ ከጉድለት ወይም አቅም ከማጣት ሳይሆን ሌሎችን ከማስቀደምና ራስን ከመግዛት የመነጨ ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዚህ ህይወት አብይ ምሳሌ ነው። በብሉይ ኪዳን የተሰጠን ሌላው ምሳሌ ሙሴ ነው። ሙሴ ትሁት ተብሏል (ዘኁልቅ12:3)።

አለም እንደዚህ ያሉትን ትገፋለች አልፋም በአባይ ሚዛን ልትጠቅምባቸው ትሞክራለች። ፍጻሜያቸው ግን መገፋትና መናቅ አይደለም። በብሉይ የመሲሁን ህይወት ሲገልጽ በምድር እንደሚሰልጥን እንደሚገዛ ተተንብዮል (መዝ 2:8-12)። ስለትሁታንም ተስፋ የተነገረ እውነት አለ (መዝ. 37:9፣ 11,29)። ከመሲሁ ጋር ምድርን እንድሚገዙ እንደሚወርሱ እናነባለን። ትሁታን የሚወርሱት አለም አሁንም፣ ወደፊትም አላቸው።

እንዴት ነው ይህ መንፈስ የሚኖረን? እውነተኛ ትህትና የመንፈስ ፍሬ ነው። ትህትና በመንግሥት ልጆች ህይወት የጌታ መንፈስ የሚያስቀምጠው ድንቅ ባህርይና ታላቅ ኃይል ነው።

## 4ኛ ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፥ ይጠግባሉና።

ረሀብና ጥማት የሰውልጆች በምድር ኑሮ የሚለማመዱት የተፈጥሮ ስሜቶች ፍላጎቶች ናቸው። ረሃብና ጥማት የምንፈልገውን እስክናገኝ ድረስ ለሰውነታችን እረፍት የማይሰጡ ናቸው። አልፈውም ለክሳት ለጤና መታወክ ደግሞም ለሞት ያደርሱናል። በውስጣቸው የሞትና የሽረት ነገር አለባቸው።

ስለዚህ ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ የሚለው አባባል፣ በቅድስና ለመኖር ያለ ብርቱ መሻትና ቁርጠኛነትን ነው። እነዚህ ደቀመዛሙርት ጌታን በባህርይው ለመምሰልና ፍቃዱን ለመፍጸም ደግሞ ያለቸውን ጽኑ አቋምና መስጠትን ያመለክታል።

## 5ኛ የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፥ ይማራሉና።

"የሚምሩ" የሚለው ቃል በደልን የመተውና የተቸገረን አይቶ የሚራራ ልብ ያለውን ህይወት ያመለክታል። ይህ ባህሪይ ያለው፥ የአንድ ሰውን በኃጢያት መሆኑን አይቶ በርኅራኄ ይዋጣል። ከኃጢያት ህይወት እንዲወጣም እገዛን ለማድረግ የፍቅር እርምጃን ይወስዳል። የሚምሩ ምህረትን ከጌታ እንዴት እንደተቀበሉ በማስተዋል፤ እንደተቀበሉት ምህረት፣ ምህረትን ለሌሎች ለማድረግ ሁሌ ይተጋሉ። ሌሎችን አይገፉም በልባቸው አድሎ የለም በመመጻደቅም አይፈርዱም፤ ይልቁን ምህረትን ስለቀበሉት ምህረት ማድረግን ይለማመዳል።

ይህ ክፍል ሰዎች ይድኑ ዘንድ ርህራሄንና ምህረትን የሚሳይ ሥራን መሥራት አለባቸው አይደለም የሚለው። ርህራኄ ለሚያስፈልገው የሚያዝን እና ተገቢውን ምላሽ የመስጠት የህይወት ባህርይን ነው የሚያስተምረን። መሲሁ እንደተለማመደው የእርሱም እውነተኛ ደቀመዛሙርት በምድር ለሌሎች የሚያሳዩት የቸርነት ህይወት ነው። (ኢሳ. 49:10፣ 13፣ 54:8፥10፤ 60:10 ዘካ 10:6)

## 6ኛ ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፥ እግዚአብሔርን ያዩታልና

ልብ ንጹሀን በሙሉ አሳባቸው ጌታን የሚያስላስሉ፥ የሚያስቀደሙ፥ በመልካም ስነምግባር ህይወታቸውን የሚመሩ ናቸው። በልባቸው ከአምላካቸው ባህርይ ጋር የሚቃረንን አሳብ አይአስተናግዱም። ሰውን ያረክሳሉ ተብለው የተገለጡትን ባህሪዎች በህይወታቸው ሥፍራ አይሰጦቸውም፥ አያስተናግዱም (ማቴ 15፡ 18-19)። አይዋልሉም፥ በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ እግዚአብሔርን መውደ የሚለው ወርቃማ ትምህርት በልባቸው ጽላት ተጽፏል። ልባቸውን ከሚያጎድፍ ነውር ሁሉ ይጠብቃሉ። ስለዚህ የህይወታቸው መመሪያ አድርገው ቃሉን ይደገፋሉ፤ የቃሉም እውነት ጉልበትና ተድላቸው ሆኖ ይመራቸዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው ማንም እግዚአብሔርን አላየም (ዘጸ. 33:18-23; 1 ጢሞ. 6:16)። ታዲያ እንዴት ነው እነዚህ ጌታን የሚያዩት? ጌታን በህይወታቸው በሚከናወኑ ነገሮች ውስጥ ያላንዳች ውዥንብር ጌታቸውን በሥራው ያዩታል። መጸሐፍ ቅዱስ በዮሐንስ 1 እና 14 ላይ እንደሚናገረው እግዚአብሔርን የምናየው በልጁ በኩል ነው። በዮሐ 1:14፤ 14:8-9 እግዚአብሔርን የማያው መንገድ ምን እንደሆነ እና እንዴት እንደሆነ ተገልጦል።

ሙሴ ልይህ ብሎ በአለት መካከል ጀርባውን አይቶ ታላቅ ልዩነት እንደተፈጠረ፤ ለነሱ በሚገባቸው መንገድ በሕይወት ዘመናቸው በገደብ ያዩታል። ልበ ንጹሖች ከክርስቶስ የተነሳ በመጪው አለም ደግሞ ጌታ እግዚአብሔርን በሙላት ያዩታል።

የልብ ንጽህና ዳግም ከመወለድና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ከመሆን ጋር የተያያዘ ነው። የሰውን ልብ ማን ያውቀዋል እንደተባለ፤ ድንጋዩን ልብ ለውጦ የስጋ ልብ የሚሰጥ ጌታ ነው። ከርሱ ጋር ባለን ቆይታና ራሳችንን ለቃሉን ለመንፈሱ በሰጠን መጠን የልባችን ንጽህና ይጠበቃል።

## 7ኛ የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና።

የዚህ የተባረከ ባህርይ መሰረቱ ከመሲሁ የሚገኝ ምህረት ነው። በእውነተኛ ደቀመዝሙርና የመንግስት ዜጋ ህይወት የሚታይ ባህርይ ነው። በኢሳያስ 9፡6-7 ክርስቶስ የሰላም አለቃ በመባል ተገልጿል። የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ምድር የመጣው ሰውን ከአብ ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነበር።

የማስታረቅ አገልግሎት ከሰማይ የወረደውን የጌታን ባህሪይ መለማመድ ነው። 2ኛ ቆሮንቶስ 5:18-21 ስለማስታረቅ አገልግሎት ምንነትና ከምን የተነሳ ይህን እንደተቀበልን ይናገራል። በዚህ ክፍል እንዲህ የሚል ሀረግን እናገኛለን “በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ...”ከዚህ የምንረዳው የሚያስታርቁ አስቀድመው ከሰላም አለቃ ጋር የታረቁ መሆናቸውን ነው።

ለአለም እውነተኛ ሰላም የሚሰጥ፥ ከሰው የሚመጣ አንዳች የለም። እውነተኛ ሰላም ከእግዚአብሔር ጋር በመታረቅ ብቻ ይገኛል። የወንጌል ኃይል፥ የእርቅ ሰላም ይሰጣል።

## 8ኛ ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና

በመበደልና ግፍን በመሥራት የሚሰደዱ አይልም:: ስለጽድቅ ግን የሚሰደዱን ሲል እውነተኛ ደቀመዝሙር ማለት ነው። የመንግስት ልጅ የሚያልፉበት እውነት እንደሆነ ያሳያል። ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ 15:18-21 እንዲህ አለ፥

> “ ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደ ጠላኝ እወቁ። ከዓለምስ ብትሆኑ ዓለም የራሱ የሆነውን ይወድ ነበር፤ ነገር ግን እኔ ከዓለም መረጥኋችሁ እንጂ ከዓለም ስለ አይደላችሁ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል። ባርያ ከጌታው አይበልጥም ብዬ የነገርኋችሁን ቃል አስቡ። እኔን አሳደውኝ እንደ ሆኑ እናንተን ደግሞ ያሳድዱአችኋል፤ ቃሌን ጠብቀው እንደ ሆኑ ቃላችሁን ደግሞ ይጠብቃሉ።”

በ2ጢሞ 3:12 “በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ።” ይላል። ከነዚህና ከሌሎች የምንረዳው የምንግሥት ልጆች ባህርይ ለአለም ከፋቷንና ጉድለቶን ስለሚያሳዮት አይመቿትም፤ ስለዚህ ታሳድዳቸዋለች።

በጽድቅ የሚመላለሱ ሁሉ በዚህ አለም መጻተኞች ናቸው፤ አገራቸውም በሰማይ ነው። ምንም እንኳን ብድራታቸው በሰማይ የተቀመጠላቸው ቢሆንም፤ ስለጽድቅ የሚሰደዱ ሁሉ በምድር ቆይታቸው ደግሞ በጉዳት ብቻ አይኖሩም። የክብር መንፈስ በነሱ ላይ ይሆናል። በ1ኛ ጴጥሮስ 4:13-14 “ነገር ግን ክብሩ ሲገለጥ ደግሞ ሐሤት እያደረጋችሁ ደስ እንዲላችሁ፥ በክርስቶስ መከራ በምትካፈሉበት ልክ ደስ ይበላችሁ። ስለ ክርስቶስ ስም ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ” ይላል።

ከአለም ያልሆነው ይህ ክቡር መንፈስ በነሱ ህይወት፥ በሁኔታዎቻቸው ሁሉ ላይ የሚሰራውን ድንቅ መገመት ያዳግታል። መንፈሱ መከራን የሚያስችል ብቻ ሳይሆን፥ በመከራ መደሰትን ሀሴት ማድረግን የሚያለማምድ ከመከራው የላቀና ክቡር እዳሎትን ይፈጥራል።

## ማቴ 5፡11 -16 የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች ባህርያት የሚያስከፍሉት ዋጋ፥ አስፈላጊነትና ጥቅም

ቁ11 ብፁህ የሚለውን ቃል ቢጠቀምም፥ ከቁ3-10 ካለው ጋር ይለያል። ይህንም ከአገላለጹ ማየት ይቻላል፤ “ከናቸው” ወደ “ናችሁ” መቀየሩ ልዩነቱን የሚያመለክት ነው። ከቁ 11-16 ኢየሱስ የሚናገረው እናንተ እያለ ነው። በዚህ ክፍል ከ3 -10 የተናገረውን እያደረጉ በዓለም ሲኖሩ ምን እንደሚጠብቃቸው ያስተምራቸዋል።

1) የመንግሥት ዜጎች በምድር ዋጋ እንደሚከፍሉ ይህ ደግሞ ከቀደሙት የጌታ ባርያዎቹ መካከል ይጨምራቸዋል፤ ያስቆጥራቸዋል። ቁ 11 -12

2) በምድር የመኖራቸው አላማ፤ አለምን የሚያጣፍጡ በክፋት ከመበላሸት የሚጠብቁ ጨው እንዲሆኑ ቁ 13

3) እግዚአብሔርን የሚያከብሩ፥ ስዎች ጌታን በእነርሱ እንዲያዩ የሚያስችል ብርሃን መሆናቸውን ያስተምራቸዋል። (ቁጥር 14-16)

## የመወያያ ጥያቄዎች ( የሁለት ቀን ጥናት ማድረግ እንችለለን)

1. በመግቢያው መሰረት ስለ ማቴ ወንጌል 5-7 ያለውን ጠቅላላ ነገር ተወያዩ።
2. በማቴ 5:1-2 ያለው የመክፈቻ ሃሳብ በዘጸአት 19፡25-20፡17 ከሰፈረው ሃሳብ ጋር ያለው መመሳሰልና ልዩነት ምንድን ነው? በዝርዝር ተወያዩበት።
3. ቁጥር 3 ጀምሮ "ብፁዓን" የሚለውን ቃል በመደጋገም ተጠቅሶል። ስለ ቃሉ ትርጉም ተወያዩበት።
4. በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው ማለት ምን ማለት ነው? (የሚከተሉትን ክፍሎች ተመልከቱ በኢሳያስ 61:1-3 ፥ ምሳሌ 29:23)
5. በመንፈስ ድሃ የመሆን ውጤቱ ምንድን ነው? ከዚህ አንጻር ራስህን እንዴት ታያለህ?
6. እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ሃዘን ምን ዓይነት ነው? ምንስ ያስገኛል? 2ቆሮ 7:10
7. በማቴ 5፡5 የዋህ የሚለው የቃሉ ትርጉም ተወያዩበት "የዋሆች ብፁዓን ናቸው፥ ምድርን ይወርሳሉና።" ሲል ምን ማለቱ ነው?
   - የየዋህ መሆንና ምድርን መውረስ እንዴት ይዛመዳሉ? (መዝ. 37:9፤ 11,29)
   - የየዋህ የመሆኛው መንገድ ወይንም ሚስጢሩ ምንድን ነው ትላለህ?

8. ቁ. 6 ጽድቅን መራብና መጠማት ምንድን ነው? (ማቴ5:6) ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብድራትስ ምንድን ነው? (መዝ 106:1-3 ምሳሌ 11፡5-6 )
9. በማቴ 5:7 "የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፥ ይማራሉና" ሲል ምን ማለቱ ነው? ስለ መሲሁ ከተተነበየው ጋር በማስተያየት ተነጋገሩበት። (ኢሳ. 49:10፣ 13፣ 54:8፥10፤ 60:10 ዘካ 10:6)
10. **በ**ማቴ 5፡ 8 "ልበ ንጹሖች" ማለት ምንድን ነው? የተረዳኸውን አካፍል።
    - ❖ እግዚአብሔርን ከማየት ጋር ለምንድነው የተያያዘው ትላለህ? ዘጸ. 33:18-23; ከዮሐ 1:14፤ 14:8-9
11. "የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው" ማለት ምን ማለት ነው? የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና ሲል ምን ያመለክታል? በ2ቆሮንቶስ 5:18-21 ኢሳያስ 9፡6-7
12. ቁ. 10 ስለ ጽድቅ መሰደድ ምንድን ነው? መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ከመሆኗ ጋር እንዴት ይገናኛል? 2ጢሞ 3:12 በ1ኛ ጴጥሮስ 4:13-14
13. ከዛሬው ጥናት ከተማርከው አንዱን እንዴት በህይወትህ እንደምትተገብረው ለቡድንህ አካፍል።
14. በቁ. 11 የእግዚአብሔር ልጆች ይደርስባችኋል፥ ይናገሩባችኋል የተባሉትን ቃላቶች ጽንሰ አሳብ ከባህርያቸው አንጻር ተወያዩባቸው። ከምን የተነሳ ነው በዚህ የሚያልፉት?
15. በቁ. 12 መሠረት በመከራ ሲያልፉ በምን አይነት ልብ ነው እንዲሆኑ የተመከሩት? የቀደሙት ነቢያትም በመከራ ከማለፋቸው የምንማረው ነገር ምንድን ነው?

16. በቁ.13 የእግዚአብሔር ልጆች በዓለም ላይ ስለሚኖራቸው ተጽዕኖ የተገለጸው እንዴት ነው? ይህን ለመግልጽ የተጠቀመበትን ምሳሌ እና የአማኞችን ባህርይ በማነጻጸር ተወያዩባቸው።
17. ከቁ13-14 ጨውና ብርሃን እንደመሆናቸው መጠን ሊሆኑ የማይገባቸው ምንድን ነው?
18. ማቴ 5፡ 15-16 ለአካሄዳችንም ሆነ ለህይወታችን በዙሪያችን ያሉትን ሰዎችን በማሰብ መጠንቀቅ የሚኖርብን ለምንድን ነው?
19. በቁጥር 16 መሠረት የመንግሥት ልጆች በህይወታቸው የባህሪይ ጥራት፣ በዕለት ኑሮቸው ስልፍ ለመጽናት አብይ ምክንያታቸው ምንድን ነው? ዛሬ በነገር ሁሉ ለማን ነው የምንኖረው? እንዴትስ ይገለጻል?

***መደምደሚያ:-***

የእግዚአብሔር መንግስት ዜጋዎችን ልዩ የሚያደርጋቸውን ማንነታቸውን ምን እንደሚመስል ነው ጌታ ያስተማረው። እነዚህ "ብፁዓን" የተባሉ ስለራሳቸው ያላቸው መረዳት፤ ያለ ጌታቸው አንዳች እንዳልሆኑ ነው። ስለራሳቸው ኃጢአትና ስለ ዓለም ኃጢአት የሚያለቅሱ ናቸው። የህያወታቸው ዓላማ አምላክ፥ ጌታና አባታቸው የሆነውን የእግዚአብሔርን ባህርይ ማንጸባረቅ ነው።

ምንም እንኳን ህይወታቸው በመልካም ነገር የተሞላ ቢሆንም፥ ከሰልፍ ነጻ የሆነ አይደለም። ዓለም እሰየው መልካም ባህርይና ምግባር አላችሁ አትላቸውም፤ እንዳውም መከራና ፍዳን ታሳያቸዋለች። በተቃራኒው በሰማይ ያለው አባታቸው ደግሞ አለም የማታውቀውን ሰላም ይሰጣቸዋል።

## ጥናት ሁለት

## ማቴ 5፡17-48

**ዓላማ፡-** እውነተኛ የጽድቅ ኑሮ ከውስጥ የማንነት ለውጥ ጀምሮ፥ የሰማይ አባታችንን እየመሰልን በየዕለቱ የምንኖረው ክቡር ህይወት መሆኑን ማስገንዘብ።

***መግቢያ፡-***

የብሉይ ህግን በመጠበቅ ማንም ጌታን ያስደሰተ አልነበረም። አዲሱ ኪዳን ግን ከብሉይ አድርግና አታድርግ ትእዛዝ በተለየ መንገድ የልብ ለውጥን በመቀበል የላቀ ሥነ ምግባርን የሚጠይቅ መሆኑን እንማራለን። ይህን ህግ የሚጠብቁ ወይም በዚህ የሚተዳደሩ በብርታታቸው ሳይሆን፤ በመንፈሱ እና በጸጋ አስደናቂ እገዛ ነው።

በዛሬው ጥናታችን የእግዚአብሔር መንግሥት ልጆች የሚተዳደሩበት ህግ ውጫዊ ከሆነ ድርጊት ያለፈ እንደሆነና የህይወት ለውጥን የሚጠይቅ መሆኑን እንመለከታለን። በተጨማሪ ጌታችን “ህግን ልፈጽም እንጂ ልሽር አለመጣሁም” ሲል ምን ማለቱ እንደሆነም እናያለን።

**የመንግሥተ ስማያት ህግ ከብሉይ ኪዳን ህግና ነቢያት የበለጠ ነው** (ማቴ 5፡17~20)

ማቴ 3~16 ኢየሱስ የመንግሥተ ስማያት ዜጋ የሆኑ ሰዎች ስለሚኖራቸው ባህርያት አስተምሯል። ቁጥር 16 ደግሞ የመንግሥት ዜጎች በአለም፥ በመልካም ሥራቸው ሊታወቁ እንደሚገባ ገልጿል። በመቀጠል ደግሞ መሰረታዊ ስለሆኑና በአይሁድ መምህር ዘንድ በአፈጻጸማቸው የተሳሳተ ትርጎሜ ስለሚስጥባቸው ስለ ህግና ነብያት እንመለከታለን።

በጥያቄ ለተሞሉ ምላሽን ይሰጥ ዘንድ፤ ጌታ ህግን ሊጠብቅ እንጂ ሊሽር እንዳልመጣ ተናገረ። እንዲያውም ከህጎቹ አንዲት እንኳ የሚሽርና ስለመሻር የሚያስተምር በመንግሥተ ስማያት ታናሽ መሆኑን፥ የሚጠብቅና

የሚያስተምር ደግሞ በተቃራኒው ታላቅ እንደሚሆን አስተማረ። ጽድቅን መፈጸም ማለት ከእግዚአብሔር ፍቃድ ጋር ሙሉ ለሙሉ መስማማት ነው።

ህግና ነብያት የሚለው አባባል ምን ያመለክታል? ብሉይ ሦስት ዋና ክፍሎች አሉት እነሱም፥ ህግ፥ ነብያትና መዝሙር ናቸው። ስለዚህ ህግና ነብያትን ሲል ሁለቱን የብሉይ መጽሐፍትን ማመልከቱ ነው። በተለያዩ ሥፍራዎች ህግና ነብያት የሚለው ሀረግ ተጠቅሰዋል።(. 7:12; 11:13; 22:40; ሉቃስ 16:16; ዮሐ 1:45; ሐዋ 13:15; 28:23; ሮሜ 3:21) ህግንና ነብያትን በተመለከተ የጌታ ኢየሱስ ትምህርት የሚያተኩረው ከውጫዊ የታይታ ነገር ይልቅ በውስጣዊ ለውጥና የልብ ቅድስና ላይ ነበር።

ጌታ ኢየሱስ ህግን ልፈጽም መጣሁ ሲል ምን ማለቱ ነበር? እንዴትስ ነው የፈጸመው? በዚህ አባባል ላይ የተለያዩ አተረጎጎሞች አሉ። ልንጨብጠው የሚገባ አንድ እውነት ጌታ በነዚህ ላይ ሥልጣን እንዳለውና በሙሴ የተሰጠው ህግ ከባርነት ነጻ ለወጡ መተዳደሪያ እንጂ የደህንነት መንገድ እንዳልነበረ ነው። ጌታ አሁን ለደቀመዛሙርት የሚያስተምራቸው ህጉ የሚገልጠው ነገር አለ፤ እኔ ግን የማስተምረው ከማድረግ የላቀ ነው የሚል ነው። ከአድርግና አታድርግ አሳብ የበለጠ እንደሆነ ለምሳሌ ማር 7፡ 16-23 ማየት እንችላለን። ይህ ክፍል ዋናው ነገር የልብ ጉዳይ እንደሆነ ያመለክታል። ውሃ ቀጠነ ከሚል ከፈሪሳውያን የተሳሳተ ትምህርት፤ የህጉ ባለቤት ከድርጊቱ በፊት የልብን ሁኔታ ስለሚያሳይ፥ ልብን እንድንመረምር ይሳስበናል።

ልፈጽም እንጂ ልሽር አልመጣሁም ሲል የህጉን ጽንሰ አሳብና አፈጻጸሙን ካለመገበዝ ታዛዥ መሆንና በዛም ጌታን ማክበርን የሚያመለክት ነው። ስለዚህ ጌታ ኢይሱስ ይህን ሲል በምንም መልኩ የብሉይን ትምህርት በመቃረን ማስተማሩ አልንበረም።

ኢየሱስ የመንግሥተ ስማያት ዜጋ የሆኑ ሰዎች ስለሚያሳዩአቸው ባህርያት አስተምሯል። ይህን በሰሙ አይሁዳውያን ዘንድ ጥያቄን ፈጥሮ ነበር። በቃ ይህ ብቻ ነው ህጉ? እንዴት ነው እንደዚህ የምታቀለው?

በዘመኑ የነበሩ አይሁድ እንዲህ ስታስተምር የብሉይ ኪዳኑን ህግና ነቢያቱ የተናገሩትን እየሻርክ ነው የሚል አሳብ አድሮባቸው ነበር። ስለዚህ ኢየሱስ ህግን ልጠብቅ እንጂ ሊሽር አልመጣሁም አለ።

ህግን መጠበቅ አያስፈልገንም፤ ተሽሯል፤ ብሎ እንዳስተማረ አድርገው ለተረዱ አይሁዳውያን ተቃራኒውን አስተማረ። እንደውም እነርሱ ከነበራቸው መረዳት በላቀ መረዳት ነው ያስተማረው። ከህጎቹ አንዲት እንኳ የሚሽርና መሻርን የሚያስተምር በመንግሥተ ስማያት ታናሽ መሆኑን፥ የሚጠብቅና የሚያስተምር ደግሞ በተቃራኒው ታላቅ እንደሚሆን አስተማረ።

በቁጥር 19 ላይ "ከነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት" ሲል የህጉን ጽናት በመጠበቅና በማስተማር ታማኞች ያላቸውን ብድራት በማበከር ይገልጻል። ህጉን በተለያየ መልክ እየሸነሸኑ ከተደነገገው ውጭ ለሚያስተምሩና ለሚጠብቁ፤ ራሳቸውንም ደግሞ በጽድቅ ወንበር ላይ ያስቀመጡን ሚዛን ላይ አስቀመጣቸው።

ከመንግሥትን ልጆች የሚጠበቀውን በቁጥር 20 "ፅድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ካልበለጠ" በማለት የመንግሥተ ስማያት ዜጎች ጽድቃቸው የላቀ መሆኑን አስተማረ። የመንገሥት ልጆች እንደ ፈሪሳዊያንና ጻፎች ያነሱትን የብሉይ ኪዳን ህጎች ከመጠበቅ ያለፈ መሆኑን አሳየ። እንደውም በቁጥር 48 የመንግሥት ልጆች የሚጠበቅባቸው ህይወት የላቀ መሆኑን "የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ" በማለት ገለጸው። በጌታ ፍጹምነት መመዘን ከሰው ችሎታ ያለፈ ነው።

የብሉይ ኪዳን ህጎች ዋና አላማቸው ፍጹም ሊያደርጉ ሳይሆን የከበረውን ህይወት ለመጥቆም ነበር። እንደ ኪዳን ህዝብ በዙርያቸው ካሉ አህዛብ የተለዩ ሆነው እንዲመላለሱ የሚያደርግ መመሪያ ነበር። የጌታ ኢየሱስ ትምህርት የብሉይ ኪዳንን ህግ አከበደው እንጂ አልሻረውም።

## ማቴ 5፡ 21-48 የመንግሥተ ስማይ ህጎች የጠበቁ የብሉይ ኪዳን ህጎች ናቸው።

የብሉይ ህጎችን የመጠበቅ ጉዳይ በውስጥ ከማሰላሰል ከስር መሰረቱ ላይ በማተኮረ እንዲመሩባቸው የመንግሥተ ልጆችን ጌታ አስተማረ። ይህን እውነት በሚቀጥሉት ቁጥሮች ውስጥ እንመለከታለን።

**የክርስቶስ ትምህርት "አትግደል" በሚለው ትዕዛዝ ላይ** (ማቴ 5፡21-26)

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ "አትግደል" የሚለውን ትዕዛዝ ከድርጊት ያለፈ ሥሩ ላይ አተኮረ። ከዚህ በደል ለመዳን ሰው ጥላቻን መተው እንዳለበት አስተማረ። ሰውን መጥላት ነው እንደዚህ ያለ ተግባር ላይ የሚያደርሰው። መግደል የጥላቻ ፍሬ ነው። በምንም በደል ሰውን ብናገኘው እንኳን ሰው በግሉ ፍርድን በራሱ መፈጸም አልተፈቀደለትም።

ይህን ድርጊት ጌታ "ወንድሙን" ከሚል ቃል ጋር በማያይዝ ነው ያስተማረው። ይህ የምንግሥት ልጆች ላይ እንደሚያተኩር አድርገው ብዙዎች የሚረዱት። ቃሉን የሰው ልጅን በሙሉ አድርጎ መውሰዱ ለአንድ ደቀመዝሙር ትክክለኛ ህይወት መሰረት ነው።

አትግደል ከሚለው ሀሳብ ጋር የጠቀሳቸው ሦስት ነገሮች የልብን ሁኔታ ያሳያሉ። ከብሉይ አሳብ ጋር በተያያዘ መልኩ ፍርድ የሚገባውን ከመግደል ሌላ ወደ እንድዚህ አይነት እርምጃ ሰውን ሊያደርሱ የሚችሉ ነገሮችን በማንሳት አሳቡን ጌታ ያጠንክረዋል።

የሚቆጣ፥ ጨርቃም የሚል እና ደንቆሮ የሚል ፍርድ እንደሚገባው ይናገራል። እነዚህን በደሎችና ፍርዳቸውን እንዲህ ብሎ ገልጦታል። "በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ <u>ፍርድ</u> ይገባዋል፤ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ <u>የሸንጎ ፍርድ</u> ይገባዋል፤ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ <u>የገሃነመ እሳት ፍርድ</u> ይገባዋል።"

ከፍርድ ለመዳን ስላለው እርምጃ ሲናገር፤ በአምላክህ ፊት መባህን ስታቀርብ ቅር የተሰኘህበት ወይ የበደልከው ካለ መባህን ትተህ ችግሩን ፍታ። አልያ አምልኮህ ከንቱ የሆናል። በህዝብ ዳኛ ፊት የሚያስቀርብህ ጉዳይ ቢኖርብህ መፍትሄን በጊዜ ፈልግ፤ ፍርዱ እንዳይጸናብህ። [ኤፌ 4:26-27፤ 1ቆሮ 6:1-11]

***የክርስቶስ ትምህርት "አታመንዝር" በሚለው ትዕዛዝ ላይ*** ማቴ 5፡27-32

የዝሙት ህይወትና መፋታት የብዙ ሰዎችን ህይወት ያመሳቀሉና የቀድሞ ድፍረትን ያስጣሉ ናቸው። በዘጸ 20:14 እና በዘዳግም 6:18 የተጠቀሰው "አታመንዝር" የሚለውን ትዕዛዝ ጌታ ከድርጊቱ ሳይሆን ትኩረትን በምንጩ ላይ በማድርግ አስተማረ።

***የማመንዘር ሥሩ አይቶ መመኘት ነው።***

አንድ አማኝ በማመንዘር ኃጢያት ከመውደቁ በፊት በሥጋ ምኞት ይጠመዳል። የሥጋ ምኞት አማኝን በጌታ ፊት በበደል እንዲገኝ ያደርገዋል። ይህ በድርጊት ከመገለጡ በፊት የመንግሥት ልጆችን ህይወት የሚያረክስ መሆኑን ያሳያል። ጌታ ኢየሱስ በክፉ ምኞት መጠመድን ከማመንዘር ጋር በማያያዝ ነው የሚያስተምረው። ስለዚህ ከውጫዊው ፍሬ ይልቅ ከመርዘኛው ጅማሬ ላይ ያተኩራል።

***መፍትሄው ምንድን ነው?***

ማሰናከያውን ማስወገድ፤ አጥርን ማድረግ ነው። ጠንከር ባለ አባባል ጌታ አሳቡን ይገልጣል። አይንህ ከአሰናከለችህ "አውጣት።" እጅህ ካሰናልከለችህ "ቆርጥህ" ጣላት። ምን ማለት ነው? አይነ ስውርና ጉንድሽ ሁኑ እያለ አይደለም። ከዚህ ይልቅ በአይንህ ከሆነ የምትቸገረው የምትቸገርበትን ጉዳይ የማታይበት ሥፍራ ሁን። ቁርጥ የሆነ ውሳኔን ውሰን ነው የሚለው። ልትነካ የማይገባህን ለአደጋ የሚዳርግህን አትንካ። እንዳትጠመድ ወጥመድ ከሚሆንብህ ነገር ራቅ። እሳት ነውና አትንካው።

ቀኝህ ከምታሰናክልህ የሚለውን አሳብ የሰውነት አካል እንደሆነ በማድረግ በሰውነታቸው ላይ አቋም የወሰዱ የጥንት አማኞች ነበሩ። የከፋውን የገሀነም ቅጣትን ከመቀበል ይህን የመረጡ ነበሩ። በአካል ላይ ጉዳት ከማድረስ ጋር የተያያዘ አይደለም መልዕክቱ፤ ይልቁንም ሊታሰብበት የሚገባው የልብ ጉዳይ ነው።

መፍትሄው ህሊናን፥ ልቧናን በተቀደሰ ነገር መሙላት ነው። ፊሌ 4:8 ላይ የተዘረዘሩትን በህሊናችን ማስተናገድ አንዱ መፍትሄ ነው።

**ፍቺን አስመልክቶ የጌታ ትምህርት፡**

መፋታት በጌታ ዘንድ አስጸያፊ ነው። በዚህ ክፍል የተፈታችውን የሚያገባ አመነዘረ በማለት ይናገራል። በዘዳግም 24:1-4 ለእሥራኤል ምክርን ጌታ ይሰጣል። በፈሪሳውያን ፍቺን አስመልክቶ ለቀረበለት ጥያቄ የሰጠው ምላሽ "እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው" የሚል ነበር። (ማር. 10፡1- 12) በመደጋገም የሚናገረው በምንም ምክንያት መፋታት እንደማይፈቀድ ነው። [ሉቃስ 16:18፣ ማቴ 19:3-9]

ሰውን ወደ ፍቺ ሊያደርስ የሚችለ ምክንያት ሲናገር የጠቀሰው የዝሙት ጉዳይ ነው። ቤት
የሚያፈርስ አደገኛ ህይወት ዝሙት ነው። በሰው ዘንድ እንደ መፍትሄ ታይቶ ቢፈጸምም ሌላውን ደግሞ በሌላ የበደል ህይወት የሚጨምር መሆኑን እንመለከታለን። ጌታ በሌላ የወንጌል ክፍል ለጠየቁት ምላሽ ሲሰጥ፤ ከሰው የልብ ጥንካሬ የተነሳ ሙሴ ያንን አሳብ ቢያቀርብም ጌታ "ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም" በማለት ፍቺን ተቃወመው።

**የክርስቶስ ትምህርት "አትማል" በሚለው ትዕዛዝ ላይ** ማቴ 5፡33-37

በዘጸ 20:7 ላይ "የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና" ይላል። መሃላን በተመለከተ የጌታ ቃል ተገቢ እንዳልሆነ ነው የሚያስተምረው። ለዚህም የሚከተሉትን ክፍሎች መመልከት መልካም ነው። (ዘሌ. 19:12፥ ዘዳ 5:11፥ 6:3፥23:21-23) መሃላን በተመለከተ ጉዳያችን ልክ መሆኑን ለማሳወቅ ምንም አይነት ሁኔታ ውስጥ እንድንገባ ጌታ አይፈልግም። የመንግሥት ልጆች ሁሌ እውነትን በመከተልና በማድረግ ከመታወቅ የተነሳ እውነተኛነታቸው መረጃ የማይሻ መሆን አለበትም።

በስሙ ስንምል እርሱ ምስክር ይሆናል ማለታችን ነው። ጌታ በአሳቡ ይስማማል ማለታችን ነው። በመሃላችን ባልሆነ ነገር እርሱን ልናስገባ አይገባንም። እርሱ ተስማምቷል ወይም ይስማማል ማለታችን ነው። መጸሐፍ ቅዱስ መሃላችን ጌታን ሳይጨምር ግልጽ በሆነ መንገድ አዎን ከሆነ አዎን ወይም አይደለም ከሆነ አይደለም ብቻ እንዲሆን ያስተምራል። (ያዕቆብ 5:12)

**የክርስቶስ ትምህርት "ፍትህን" በተመለከተ ማቴ 5፡ 38-42**

ሰው የበደሉትን ለመበቀል የሚፈልግ ልብ አለው። ጌታ ግን ይህን አይፈቅድም። ሆኖም በብሉይ ይህን ሀሳብ የሚያሳዩ ክፍሎች አሉ። በዘፀ 21:24፥ ዘሌዋ 24:19-20፤ ዘዳ 19:21 ላይ የበደለ እንደበደሉ መጠን ዋጋን መክፈል የሚገባው መሆኑን እናነባለን። ከነዚህ አሳብ ጋር ልናየው የሚገባ "አትበቀልም፥ በሕዝብህም ልጆች ቂም አትያዝ፥ ነገር ግን ባልንጀራህን እንደ

ራስህ ውደድ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ" የሚለውን የዘሌዋ 19:18 ክፍልም ነው።

በማቴ 5:39 ላይ ያለው አሳብ አማኝን ዝም ብለህ በደልን ታገስ ነው ወይስ ከዛ የተለየ ሀሳብ አለው? በርከት ባሉ ክፍሎች በቀል፥ ፍትህ የጌታ መሆኑን እናነባለን [ዘሌዋ. 19:17-18፤ ዘዳግም 32:35፤ መዝ 94:1፤ ምሳሌ 20፡ 22፥ 24:29]። አማኝ ለእርሱ የሚቆም ጌታ አለው፤ እርሱ ግን ለሌሎች ሰላም ሊቆም ይገባል። እስከምን ድረስ ነው ለመሆኑ አማኝ ሳይበቀልና ሲገፉት ዝምብሎ የሚያሳልፈው? ከመበቀል ይልቅ በተቃራኒው አራት ነገሮችን እንዲያደርግ ይህ ክፍል ያሳየናል።

አንደኛ **ክፋውን ለመቋቋም አትነሳሳ፡-** "ክፋውን አትቃወሙ፤ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት" ሲል ክፋውን በመልካም መልስ ማለት ነው። ከዚህ ሌላ የሚያመለክተው በእውነት ስትገፋ ፍትህን በዛው በአመጽ መንገድ አትሻ የሚል ነው።

ሁለተኛ **ስትነጠቅ ምላሽህ እምቢተኛነት አይሁን**፡- በግፍ ሊነጥቅህ ለሚነሳ ጨምረህ ሰጠው። ዓይን ለዓይን፥ ክፋትን በክፋት ሳይሆን እንደውም ሲቻልህ ትርፍን በመስጠት በጎነትን አሳይ። (ዘጸ 22:26-27፥ ዘዳግም 24:13)

ሦስተኛ **የማይገባህን ሲያሠሩህ ሳታጉረመርም ትርፍን ሥራ**፡- ይህ በሮማውያን አስተዳደር ውስጥ ሆነው ለሚያማርር ትዕዛዝ ምልሽ ከመስጠት አንጻር የተጻፈ ነው። አንድ የሮም ወታደር ሻንጣውን በግድ የተወሰን መንገድን እንድትወስድለት ቢጠይቅህ ከጠየቀህ በላይ አድርግለት የሚል ምሳሌያዊ አባባል ነው። ጥቅምን ወሰደብኝ በማለት አታጉረምርም። ወይም ቆይ ግዴለም በማለት ለመበቀል ሁኔታን አትፈልግ የሚል መልዕክት አለው።

አራተኛ **ከአንተ ለሚፈልግ፥ ሊበደርህ ለሚሻ ስጥ**፡- በሌሎች ዘንድ እንደተለመደው በአራጣ ሳይሆን በልግስና ያደርጉት ዘንድ ነበር ጌታ የሚያስተምረው። የሚከተሉትን የብሉይ ኪዳን ትምህርቶችን የተመለከተ አሳብ ነው። ዘጸ 22:25፥ ዘሌዋ. 25:37፥ ዘዳግም 23:19፥ መዝ 37:26፥ 112:5

ይህ ክፍል የመንግሥት ልጆች ለክፉ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ተግፍተውም ቢሆን እንኳን ያላቸውንና መብታቸውን በደስታና በፍቅር ለሌሎች በመተው ሰላምን እንደሚሹ ነው የሚያሳየን።

**የክርስቶስ ትምህርት "ባልንጀራን መውደድን" በተመለከተ** ማቴ 5፡43-47

ጠላትን ለመበቀል ከመነሳሳት ይልቅ ለማፍቀር የሚያነሳሳ ትምህርትን ነው የእግዚአብሔር መንግሥት ትምህርት። እንዴት ነው ለጠላቶቻችን መልካምን ማድረግ የምንችለው?

**የመንግሥት ልጆች ልምምድ፡-**

የመንግሥት ልጆች ያልሆኑት የሚወዷቸውን ይወዳሉ፤ ወዳጅ የሚሏቸውን ብቻ ሰላም ይላሉ። በተቃራኒ፥ እውነተኛ ደቀ መዝሙርና የሰማይ አባት ልጆች የሚከተሉትን ያደርጋሉ። ጠላቶቻችውን ይወዳሉ። የሚረግሟቸውን ይመርቃሉ። ለሚጠሏቸው መልካም ያደርጋሉ። ለሚያሳድዷቸው ይጸልያሉ። እንዴትና ለምን? በመጀመሪያ ይህን ለመለማመድ የሚያስችላቸው ልብና ቅን መንፈስ በመንግሥት ልጆች ዘንድ አለ። እውነተኛ ፍቅር (መውደድ) ስሜትንና ምግባርን ያካተተ ነው። [ሉቃስ 6:32-35] አድሎ የሌለውና ሁሉን በአንድ የሚያይ ህይወት ነው።

ሁለተኛ ይህን ሊያደርጉ የሚጠበቅባቸው የሰማይ አባታቸው ባህርይ ስለሚያንጸባርቁ ነው። የሰማይ አባታቸው የማይወደዱን የሚወድ ታላቅ ጌታ ነው። ይህ አባት በፍቅሩና በቸርነቱ ለሰው ሁሉ በምድር በረከትን ያፈሳል። የፀሐይ መውጣትና የዝናብ መዝነብ የጌታ በጎ ስጦታ ናቸው። የእነዚህ መፈራረቅ ምድር ፍሬን እንድትሰጥና የሰው ልጅ እንዲመገብ ምክንያት ናቸው። ይህን ሁሉ በቸርነቱ ማንንም ሳይለይ ያደርጋል።

**ከደቀ መዝሙር የሚጠበቅ ህይወት ምን ይመስላል?** ማቴ 5:48

"እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ።" ሲል ምን ማለቱ ነው? ጌታ በባህርይው እንከን የሌለው ነው። በፍቅሩ፥ በልግስናው፥ በምህረቱ፥ በእውቀቱ ወዘተ። ይህ ጌታ እንደሆነ ሁኑ ሲል ቀላል ነገርን አይደለም የሚጠይቀው። ቢያንስ የአማኝ ህይወትን ጥራት

ያመለክታል። ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንዳንድ አሳቦችን እንውሰድ።

ከኤፌ 4:13 እና 1 ቆሮ 14:20 ሁለት መሰረታዊ ነገሮችን እንውሰድ። በመጀመሪያ ሙሉ ሰው መሆን ነው። ሁለተኛ ለክፉት ነገር ሕፃናት መሆንና እንደ በሰሉ ሰዎች መሆን ነው።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በማቴ 5፡17 ሕግንና ነቢያትን የሚለው አባባል ምን ማለት ነው? ጌታ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም" ሲልስ ምን ለማለት ነው?
2. ስለህግ ማቴ 5፡ 18-20 የተጠቀሱትን አሳቦች በሚከተሉት ነጥቦች ዙሪያ ተወያዩባቸው።
    - ❖ ስለህግ በቁጥር 18 ምንድን ነው የተጠቀሰው?
    - ❖ በቁ.19 መሰረት ከህግ ጋር በተያያዘ የተጠቀሰው መርገምና በረከት እንዴት ነው?
    - ❖ በ ቁጥር 20 "ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ ወደ መንግሥተ ሰማይ አትገቡም" የሚለው አባባል ምንድ ነው?
3. ከቁ.21-22 ላይ የተጠቀሰው የብሉይ ህግ እንዴት ነው የተገለጸው? ፍርዱስ?
4. ጌታ "እኔ ግን" በማለት ከዚህ በማያያዝ የጠቀሳቸው ሦስት ፍርድ የተገባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? አትግደል ከሚለው ጋርስ እንዴት ይያያዛሉ?

5. ከቁ.23-26 በወንድማማቾች መካከል ያለውን ችግር ለመፍታት የቀረበው ምክር ምንድን ነው?
6. ከቁ.27-30 የተጠቀሰው ህግ ምንድን ነው? መንሰኤውን አስመልክቶ የጌታ ትምህርት ምንድን ነው? መፍትሄውስ?
7. "አውጣት"፥ "ቁረጣት" እያለ የሚናገረው መልዕክቱ ምንድን ነው? ምንስ ማለት ነው?
8. ከቁ.31-32 ስለመፋታት የተሰጠው ትዕዛዝ ምንድን ነው?
   - ❖ "እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው።" እና "ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም" የሚሉት አባባሎች ምን ያስተምሩናል?
   - ❖ እንደ ምክንያት የቀረበውና የሚያስከትለው በደልስ ምንድን ነው?
   - ❖ ቀደም ብሎ ከተሰጠው ትምህርት ጋር እንዴት ይያያዛል? (ለውይይት የሚረዱ ጥቅሶች በዘዳግም 24:1-4፤ ማር. 10፡1-12፤ ሉቃስ 16:18፣ ማቴ 19:3-9)
9. በቁ.37 እና በያዕ 5፡12 በመመልከት ስለ መኃላ የተጠቀሰውን ተወያዩበት።
10. ማቴ 5፡33-36 በማን እና በምን ነው እንዳትምል የተባለው? ለምን?

❖ ከሚከተሉት የብሉይ ጥቅሶች ጋር በማነጻጸር ተመልከቱት።

(ዘጸ 20:7 ዘሌ. 19:12፥ ዘዳ 5:11፥ 6:3፥23:21-23

11. ከቁ 38-41 በቀልን አስመልክቶ የክርስቶስ ትምህርት ምንድ ነው? ለሚጎዱህ፥ ሰዎች እንድትሰጥ የሚጠበቅብህ ምላሽ ምንድን ነው?

12. በቁ. 42 እንድናበድራቸው አለያም እንድንሰጣቸው ለሚጠይቁን ምላሻችን መሆን ያለበት ምንድን ነው? ከዘጸ 22:25፥ መዝ 37:26፥ ጋር ተመልከቱት።

13. ከ44-45 እኔ ግን እላችኋለሁ በማለት ጌታ፤

❖ በሰጠው አራት ጥንድ ተጻራሪ አሳቦች ላይ ተነጋገሩ።

❖ ምን ትሆኑ ዘንድ ነው እነዚህን ድርጊቶች አድርጉ የሚለው?

❖ ይህ የሚያመለክተው ድነትን ነው ወይስ ሌላ ነገር?

❖ እንዲያደርጉት የሚሰጣቸው ተጨማሪ ምክንያት ምንድን ነው?

14. ከቁ.46-47 ወንድሞችን ከሌሎች ጋር በማነጻጸር ምን ዋጋ፥ ምንስ ብልጫ አላችሁ የሚላቸው ስለምንድ ነው? (ከሉቃስ 6:32-35 አብራችሁ ተመልከቱ) ይህ ስለእያንዳንዳችን ኅብረት ምን ያሳስበናል?

15. "የሰማይ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ" ሲል ምን ማለቱ ነው?

❖ በምዕራፉ ውስጥ ከተሰጡት ሃሳቦች ጋር እንዴት ይያያዛል?

❖ ይህ ሃሳብ እንደ አማኝ የግል ህይወትህን በተመለከተ ምን ያሳስብሃል?

16.ከዛሬው ጥናት ይህን ማድረግ እንደሚገባኝ ተረድቻለሁ የምትለውን ለቡድንህ አካፍል።

***መደመደሚያ***

የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋዎች ህይወት ቅድስና የተሟላና ለሌሎች አብነት ያለው መልካም ምግባር ነው። በብሉይ የነበረው ህግን የመጠበቅ ጉዳይ ለድርድር የሚቀርብ ሳይሆን ለመጠበቅና ላለመጠብቅ ምክንያቱ የሆነው የውስጥ ማንነት ላይ ያተኮረ ነው። ህጉን ለመተላለፍ ምክንያት ሰው በልቡ ያለ የምኞት ሁኔታ እንደሆነ እንመለከታለን።

የህጉ ባለቤት የሆነ ጌታ ኢየሱስ የሚያስተምረው ልባችንን እንድንመረምርና ወደ እርሱ እንድንጠጋ ነው። የሰማይ አባታቸውና ከሰማይ የወረደው አዳኝና ጌታ ያለውን ባህርይ የሚያሳይ የህይወት ጥሪ ነው። የክፍሉ መዝጊያ ላይ እንደተጠቀሰው የእግዚአብሔር መንግሥት ልጆች በባህርያቸው "የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ" በሚለው ሀረግ የተጠቃለለ ነው። ይህም የእኛ ህይወት እንዲሆን ጌታ ጸጋውን ያብዛልን።

# ጥናት ሶስት

# ማቴ 6፡1-18

# ለታይታ ያልሆነ እውነተኛ መልካም ስራ

**ዓላማ፡-** አማኝ የሚያደርጋቸውን ማንኛውንም ነገር ለሰው ለመታየት እንዳያደርግ ማስገንዘብ

**መግቢያ**

እግዚአብሔር በቃሉ የሚያዛቸውን መልካም ነገሮች ሁሉ ማድረግ መልካም ነው፤ ነገር ግን መልካም ተግባር ነው ብለን የምንፈጽመው ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ይኖረዋል ማለት አይደለም። የትም ፍጪው ዱቄቱን ብቻ አምጪው እንደሚባለው አይነት ተረት አይደለም። እግዚአብሔር መልካም ነገር ማድረጋችንን ብቻ ሳይሆን የሚያየው ፤ የምናደርገውን እንዴት ባለ መንገድ እንደምናደርገው እና ለምን እንደምናደርገው ሁሉ ሳይቀር ይመለከታል። ስለዚህም ከእግዚአሔር ቃል ጋር በተጣረሰ መንገድ ተጉዘን የምናደርገው ማናቸውም ነገር የቱንም ያህል መልካም ቢመስል እግዚአብሔር እንደ መልካም ተግባር ሳይሆን እንደ እኩይ ተግባር ነው የሚያየው።

ልክ እንዲሁ በማቴ 6፡1-18 ባለው ክፍል ለታይታ የሚደረጉ መልካም ስራዎች በሙሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ እና ተቀባይነት እንደሌላቸው ያሳስባል። ስለዚህም ሕዝበ ክርስቲያን (አማኞች) በጌታ ዘንድ የተወደደ እና ተቀባይነት ያለው ነገር ለመስራት መልካም ስራቸውን የሚያደርጉት ከሰው ክብር ለማግኘት ወይንም ለታይታ ሳይሆን፣ በንጹህ ልብ ጌታን ስለሚወዱ እና እሱን ደስ ለማሰኘት ከመፈለግ የተነሳ ብቻ ሊሆን እንደሚገባ ያሳስባል።

በማቴ 6 የምዕራፉ መጀመሪያ ላይ ማቴዎስ “ለሰዎች ትታዩ ዘንድ **ምጽዋታችሁን** በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ” ይላል። ይህ በቁ.1 “ምጽዋት” የሚለው ቃል በአማርኛ ትርጉም ላይ በድጋሚ በቁ 2 እና 4 ላይ በመጠቀሱ፣ ከቁ 1-4 ያለው ክፍል የሚናገርው ስለተመሳሳይ ነገር ሊመስል ይችላል። ሆኖም ግን በቁ 1 ላይ ያለው ቃል ትክክለኛ ትርጉሙ “የጽድቅ ሥራ” ወይንም “መልካም ሥራ” የሚል ነው። ስለዚህም በቁ 1 ላይ ያለው ጥቅስ “ለሰዎች ትታዩ ዘንድ መልካም ስራችሁን እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ” የሚል አሳብ ያዘለ ነው።

## የክፍሉ አጭር ማብራሪያ

ስለዚህም ገና በቁ. 1 ላይ ማቴዎስ መልካም ስራችንን ለታይታ ማድረግ እንደሌለብን ያሳስባል። ሆኖም ግን አማኝ የጽድቅን ሥራ የሚያደርገው በሰው ለመታየት፣ ወይንም በሰው ፊት ሆይታ እና ከበሬታ ለማትረፍ ከሆነ፣ በእርግጥም ግለሰቡ እንደፈገው፣ አንቱታውን እና ከበሬታውን ሊያገኝ ይችላል፤ ችግሩ ግን እንዲህ ያለ ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚቀበለው ዋጋ አለመኖሩ ነው። ማቴዎስም ይህንኑ እውነት “ያለዚያ በሰማያት ባለው አባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም” ሲል አስምሮበታል (ማቴ 6፡1)።

ከቁ. 2- 18 ያለውን ክፍል ስናነብ፣ ለታይታ እና የሰውን ከበሬታ ለማግኘት መልካም የሚያደርጉ ሰዎችን፣ ጌታ ኢየሱስ እየደጋገመ “ግብዞች” እያለ ሲጠራቸው እናያለን (ቁ.2፣ 5፣ እንዲሁም 16)። ግብዝ የሚለው ቃል አስመሳይ ወይንም ያልሆነውን መስሎ ለመገኘት የሚሞክር ወይንም ቲያትረኛ የሚል ትርጉም ያለው ነው። በዚህም ቃል መሰረት ለታይታ መልካም አድራጊ መስሎ ለመገኘት የሚጥሩ ሰዎች፣ እውን መልካም ሰዎች ሳይሆኑ ከላይ የመልካምነትን ጭምብል የለበሱ ውስጣቸው ግን ሌላ ክፉ ተልዕኮ ያላቸው መሆኑን ያስገነዝባል። በጌታም ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው፣ እውነተኛ መልካም ሰራተኛ ባለመሆናቸው ነው።

እንግዲህ እንደ አማኝ መልካም ነገርን ሁሉ ከንጽህ ልብ ልናደርገው ቢገባንም በማቴ 6፡2-18 ባለው ክፍል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለታይታ ልናደጋቸው የማይገቡ ሦስት መልካም ነገሮችን ይጠቅሳል፤ ምጽዋት ማድረግ (2-4)፣ መጸለይ (5-15) እንዲሁም መጾም (16-18)። በዛሬው ጥናታችን እነዚህን ሦስት ሰናይ ምግባራት በመ'ደገፍ በጎ አድራጎታችንን ሁሉ በቅንነት እና ጌታን ስለመውደድ ስንል ማድረግ እንዳለብን እንመለከታለን።

1. **ምጽዋት ማድረግ (6፡2-4)**

ከመልካም ስራዎች መካከል ከቁ. 2-4 ባለው ክፍል ጌታ የጠቀሰው ምጽዋት ማድረግን ነው። ከላይ እንዳየነው በዚህ ክፍል ውስጥ "ምጽዋት" የሚለው ቃል በቁ. 1 ላይ ከተጠቀሰው የተለየ ነው። በዚህ ክፍል "ምጽዋት" የሚለው ትርጓሜ ትክክለኛ ሲሆን፣ ካለን ለሌሎች መስጠትን፣ እንዲሁም ለተቸገሩ መልካም ወይንም ቸርነት ማድረግን ያመለክታል። እንግዲህ በቁ. 2 ላይ ምጽዋት ስናደርግ ልናደርገው የማይገባንን ሲዘግብ፣ በቁ. 3 እና 4 ላይ ደግሞ ልናደርግ የሚገባንን ያትታል።

በመጀመሪያ ምጽዋት ስናደርግ፣ አድራጎታችን እንደ ግብዞች ሊሆን አይገባም። ከላይ እንዳየነው፣ ግብዞች መልካም የሚያደርጉት ለተቸገረው አዝነውለት ወይንም አስበውለት ሳይሆን፣ በመልካም አድራጎት ስም ዝና እና አክብሮት ለማግኘት ነው። ለዚህም ነው በምኵራብ በጉባዔ ፊት ወይንም ደግሞ በመንገድ፣ በአላፊ አግዳሚው ፊት፣ የእዩልኝ ጥሪ እያቀረቡ (መለከት እያስነፉ)፣ ገንዘብ የሚሰጡት። እንደዚህ ያሉት ሰዎች በእርግጥ ከልብ እየሰጡ ወይንም እየረዱ ሳይሆን፣ በሰጪነት ስም ዝና እና አድናቆትን ከተመልካች እየገዙ ነው። ስለዚህም "ዋጋቸውን ተቀብለዋል።" ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያገኙት ሌላ ዋጋ የለም። አማኝ ግን ምጽዋትን ሲያደርግ እንደ ግብዝ ሊሆን አይገባም።

በሁለተኛ ደረጃ፣ ምጽዋት የምናደርገው እንደ ግብዞች ካልሆነ፣ እንዴት መስጠት እንዳለብን ያሳስባል። "አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ፣ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን ቀኝህ የምትሰራውን ግራህ አትወቅ" ይላል(ቁ.

3)። ለእግዚአብሔር ቤት የሚሰጥ ስጦታም ሆነ ለችግረኛ የሚደረግ ቸርነት፣ በስውር ሊደረግ ነው የሚገባው ሲል ያሳስባል። በእርግጥ ይህ ማለት ሰው መልካም ባደረገ ቁጥር ሁሉ ደግነቱ እንዳይታወቅበት መደበቅ አለበት ወይንም በድብቅ ማድረግ አለበት ማለት እንዳይደለ ሊስተዋል ይገባል። በእርግጥም ክርስቲያን መልካም ሲያደርግ ኃጢአት እንደሰራ ሰው መደበቅ እና መሸሸግ አያስፈልገውም ፤ ብርሃኑ በሰው ሁሉ ፊት እንዲበራ እንጂ! ሆኖም ግን ከልብ ለተቸገረው አዝኖ የሚረዳ፣ ወይንም ለእግዚአብሔር ቤት ከልብ መስጠት የሚፈልግ መጽዋች፣ እዩልኝ አይልም፣ ወይንም ለጎረቤት አዋጅ አያስነግርም። ወይንም አድራጎቴን ሰው ካላወቀልኝ አይልም። ነገር ግን ጌታን ከመውደድ እና ለተቸገረው በቅንነት በማሰብ ብቻ ለሌላው አዋጅ ሳያስነግር ይሰጣል። ግለሰቡ እዩልኝ እያለ እስካላደረገው ድረስ፣ ቸርነቱን ሌላው ሰው ቢያውቀው ምንም ችግር የለውም።

በዚህ ክፍል ውስጥ (ከቁ. 2 -18) ጌታ በተደጋጋሚ የሚያሳስበን ነገር፣ እግዚአብሔር ልብን የሚያይ እና ዋጋ የሚሰጥ መሆኑን ነው (ቁ. 4፣ 6 እንዲሁም 18 ልብ ይበሉ)። ሰው ለክብር እና ለዝና ብሎ መልካም ቢያደርግ ጎረቤቱ በልቡ ምን አስቦ እንደሰጠ ላያውቅ ይችላል። እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል (1ኛ ሳሙ 16፡7)። ልክ እንዲሁ ሌላው ሰው ያደረገውን እንኳ ሳያውቅ፣ አማኝ ስለ ጌታ ሲል ብቻ መልካም ሊያደርግ ይችላል። ሆኖም ግን ጉዳዩ ከሰው ቢሰወርም ከእግዚአብሔር ዘንድ ግን የሚሰወር ነገር የለም (ኤር 23፡23-24)። ስለዚህም ልብን የሚያየው እግዚአብሔር ግብዙን ዋጋ ሲነሳው፣ በስውር ስለጌታ የሚሰጠውን ግን በአደባባይ ዋጋ ይሰጠዋል።

**2. መጸለይ (6፡5-15)**

ምጽዋት ከማድረግ በመቀጠል፣ ጌታ በሁለተኛ ደረጃ የሚጠቅሰው መልካም ወይንም የጽድቅ ሥራ ጸሎት ነው። በዚህ ክፍል (ከቁ 5-15 ባለው)፣ ስለ ጸሎት ሲናገር፣ በጸሎት ጊዜ ልናደርጋቸው የማይገቡ ሁለት ነገሮችን ያሳስባል። በመጀመሪያ “ስትጸልዩ እንደ ግብዞች አትሁኑ” (ቁ. 5) ሲል፣ በሌላ በኩል ደግሞ “ስትጸልዩ እንደ አሕዛብ በከንቱ አትድገሙ” (ቁ. 7) ይላል።

እንግዲህ እንደ ግብዞች አትጸልዩ ሲል፣ ከላይ እንደገለጽነው፣ ጸሎትን ለታይታ ብላችሁ አታደርጉ ማለቱ ነው። በእርግጥም ጸሎትን ማዘውተር ተገቢ እና መንፈሳዊ በመሆኑ፣ ለግብዞች ጽሎተኛ መምሰል እና በሌላው ሰው ዘንድ ከፍ ተብሎ መታየት አንደኛው የሚፈታተናቸው ነገር ነው። ስለዚህም በሰው ዘንድ ሲጸልዩ የሚታዩበትን ቦታ ይመርጣሉ። “በምኵራብ እና በመንገድ ማዕዘን ቆመው መጸለይን ይወዳሉና” (ቁ. 5)። ከላይ እንዳየነው እንደ መጽዋቹ፣ ለታይታ የሚጸልየው፣ ከሰው አድናቆትን ለማትረፍ በመሆኑ፣ ከሰው ዋጋውን ይቀበል ይሆናል፣ ከጌታ ዘንድ ግን ዋጋ የለውም።

ታዲያ ሰው እንዴት ነው ሊጸልይ የሚገባው ለሚለው ጥያቄ  ቁ. 6 መልስ ይሰጣል። “አንተ ግን ስትጸልይ፣ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ”። በስውር ጸልይ ሲል ከላይ እንዳየነው ሁሉ፣ ሰው ሲጸልይ መደበቅ አለበት ወይንም የሕብረት ጸሎት ሊያደርግ አይገባም ለማለት እንዳይደለ እንድናስተውል ይገባል። ጌታ ራሱ በሕዝብ ፊት ብዙ ጊዜ የጸለየበት ጊዜ እንዳለ አንዘንጋ። ቁም ነገሩ ለጸሎት የምንቀርብበት አላማ ነው። መንፈሳዊ ለመምሰል በሰዎች ፊት ከመጸለይ፣ በንጹህ ልብ ጌታን ለመፈለግ በጸሎት ሰው ሊቀርብ እንደሚገባው የሚያሳስብ ነው። በሰው ልብ ውስጥ ያለውን እውነተኛ አላማ የሚያይ እግዚአብሔር፣ ሰው በማያየው ቦታ እንኳ ሆኖ በጸሎት ጌታን የሚፈልገውን፣ ምንም በድብቅ ቢደረግ፣ እግዚአብሔር ግን በአደባባይ በግልጽ ዋጋ ይሰጣል።

ስትጸልዩ እንደ አሕዛብ በከንቱ አትድገሙ ሲል ደግሞ በጌታ ፊት በተደጋጋሚ በጸሎት መቅረብ መልካም ቢሆንም ፣ጸሎትን እንደ ዳዊት በዘልማድ መደጋገም ግን ትርጉም የለሽ መሆኑን ያሳስበናል። አሕዛብ የሚጸልዩት ለጣኦትም ይሁን ለምን፣ አምላካቸው የሚያስፈልጋቸውን ያውቅልናል ብለው ስለማያስቡ፣ በድግግሞሽ ብዛት የሚሰሙ ይመስላቸዋል (1ኛ ነገ 18፡25-26 ያለውን ያወዳድሩ)። እኛ ግን፣ ስንጸልይ፣ በመጀመሪያ የምንጸልየው ጌታ የሚያስፈልገንን ስለማያውቅ አይደለም። በጸሎትም ለጌታ አዲስ የምንነግረ ነገር የለም። በሁለተኛ ደረጃ የምንጸልየው ጸሎትን እንደ

ዳዊት በመድገም አይደለም። ጸሎት አማኝ ከአባቱ ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኝበት፣ በእግዚአብሔርም ፊት የልቡን የሚያፈስበት መንገድ ነው። ሰው ለእግዚአብሔር የልቡን የሚናገረው በልማድ ጸሎቱን በመድገም አይደለም።

ታዲያ እንደ አሕዛብ ጸሎትን መድገም ከሌለብን እንዴት እንጸልይ ቢባል፣ ከቁ 9-15 ባለው አማኝ እንዴት ሊጸልይ እንደሚገባ ጌታ ያስተምራል። በተለምዶ "የሐዋሪያት ጸሎት" የሚባለው እና ጌታ ያስተማረው ጸሎት፣ በመሰረቱ ጸሎት እንዴት መሆን እንዳለበት ለማስተማር የተሰጠ እንጂ በየጊዜው እንደ ዳዊት እንድንደግመው የተሰጠ እንዳልሆነ ልናስተውል ይገባል። በዚሁ ክፍል ከላይ እንዳየነው ጸሎትን እንደ አሕዛብ አትድገሙ መባላችንን ልብ ይበሉ። በዚህ ጸሎት ውስጥ ስድት ኃረጎች/ ዓርፍተ ነገሮች ያሉ ሲሆን፣ የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ኃረጎች ስለ እግዚአብሔር እና ስለ መንግስቱ  የሚናገሩ ሲሆን የቀሩት ሦስቱ ደግሞ ስለ እኛ የሚናገሩ ናቸው። ነገርየው አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግስት ፈልጉ እንደተባለው ነው። ጸሎቱ በመጀመሪያ እግዚአብሔርን የሚያወድስ፣ መንግቱን የሚሻ ነው። ወይንም በመጀመሪያ በሙሉ ማንነትህ እግዚአብሔርን ወደድ፣ ቀጥሎም ባልንጀራህን እንደራስህ ወደድ እንደሚሉት ሁለቱ ታላቅ ትዕዛዛት አይነት ነው። ስለ ሰው ልመና የቀርብበት የጸሎት ክፍል ላይ፣ ጸሎቱ ለእለት የሚያስፈልገንን ከመጠየቅ ሌላ፣ ይቅርታን እንድንማር እና በይቅርታ ኑሮአችንን ከእግዚአብሔር ጋር እንድናድስ፣ እንዲሁም ደግመን በፈተና ወድቀን ደግሞ እንዳንበድል እግዚአብሔር ከፈተና እንዲጠብቀን የሚጠይቅ ነው። ይህ ጸሎት በፍጹም ዝና እና አድናቆትን ከሰዎች እንድናተርፍ የሚናገር አይደለም። ጸሎት እግዚአብሔርን የምናወድስበት እና ፈቃዱን የምንሻበት፣ እንዲሁም በግል ሕይወታችን ደግሞ ለእለት ከሚያስፈልገን አልፎ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መኖር እንድንችል የምንለምንበት መድረክ ነው።

በዚህ ክፍል ፍጻሜ ላይ (ቁ. 14 እና 15) ለጸሎት እንቅፋት የሚሆንብንን ነገር ማስወገድ እንደሚገባ ያሳስባል። "ሳል ይዞት ስርቆት፣ ቂም ይዞ ጸሎት" እንደሚባለው የሌላውን በደል እየቆጠሩ በእግዚአብሔር

ፊት በጸሎት መቅረብ ሞኝነት ነው። እንዲህ ባለ ሕይወት በጸሎት እግዚአብሔር ፊት መቅረብ፣ ከጣሪያ የማያልፍ ጩኸት እንደመጮህ ነው፤ የሌላውን በደል የሚቆጥር፣ የእሱም ስለሚቆጠርበት ንጹህ ሆኖ በጌታ ፊት መቅረብ አይችልም እና።

**3. መጾም (6፡16-18)**

በሦስተኛ እና በመጨረሻ ጌታ የሚጠቅሰው መልካም ሥራ መጾም ነው። አሁንም በድጋሚ ምጽዋት እንደ ማድረግ እና እንደ መጸለይ ሁሉ ጾም እንደ ግብዞች ሊደረግ አይገባም። ጿሚ መሆናቸው እንዲታወቅላቸው እና መንፈሳዊ ሰው ለመባል ፈልገው ፊታቸውን የሚያጠወልጉ እውነተኛ ጿሚ አይደሉም። እውነተኛ ጿሚ የሚፈልገው፣ የሰውን ክብርና ፊት ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ፊት ነው። በሰው ዘንድ ለመታየት የሚጾመው፣ እንደ ግብዙ መጽዋች እና ጸሎተኛ ሁሉ፣የሚፈልገውን የሰው ክብር  (ዋጋ) ከሰው ያገኛል። የሰውን የልብ አሳብ በሚያውቀው በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ዋጋ አይኖረውም።

አማኝ እንዴት ይጹም ለሚለው ግን ጌታ መልስ ሲሰጥ “አንተ ግን ስትጾም፣ በስውር ላለው አባትህ እንጂ እንደጦመኛ ለሰዎች እንዳትታይ ራስህን ተቀባ፣ ፊትህንም ታጠብ” ይላል። በጾም እና በጸሎት ሰው ራሱን አዋርዶ የሚቀርበው በስውር ባለው አባት ፊት ለመታየት እና እሱን ለመፈለግ እንጂ በሰዎች ፊት ለመታየት አይደለም። ለታይታ የሚደረግ ጾም አላማውን ፈጽሞ ስቷል። ይህ እንዳይሆን ግን ጌታ  ሰው በጾም ምክኒያት ፊቱ በርሃብ የተጎዳ እና አመዳም  መስሎ ሰው እንዳይቀርብ ያሳስባል። ነገር ግን ከላይ እንዳየናቸው ሌሎቹ መልካም ሥራዎች ሁሉ፣ ጌታ ይህንን ሲያሳስብ፣ ሰው ጾም ጸሎትን በድብቅ መለማመድ አለበት ለማለት ሳይሆን ከበተጀርባው ያለው የጿሚው አላማ ታይታ አይሁን ነው። ለታይታ ከተደረገ ግን፣ ሰውነትን በራብ ከመጉዳት እና ራስን ከማቆሳቆል በቀር በጌታ ፊት ዋጋ አይኖረውም።

በቅንነት የጌታን ፊት በጾም የሚፈልገውን ሰው እግዚአብሔር ከማየቱም ባሻገር፣ እግዚአብሔር ዋጋ ይከፍላል። ሰው በጾም ጊዜ የሰውን ከበሬታ ከሆነ የሚፈልገው፣ የፍላጎቱን ያገኛል። ግን የሚፈልገው እግዚአብሔርን ከሆነ፣ በእርግጥም እግዚአብሔርን ያገኛል (ኤር 29፥13)። ስለዚህም አማኝ ሲጾም በእውነት የእግዚአብሔርን ፊት ይሻ።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ማቴ 6፥1 ላይ የተጠቀሰው ምጽዋት የሚለው ቃል በቁ 2 እና 4 ላይ ከሚጠቅሰው ምጽዋት ማድረግ የሚለየው በምንድን ነው?
2. ማቴ 6፥ 1-18 ከተጠቀሱት ሦስቱ መንፈሳዊ ልምምዶች በዝርዝር ተነጋገሩባቸው።
3. ምጽዋት ማድረግ መጸለይ እና መጾም በመንፈሳዊ ህይወታችን ላይ ሚጨምረው ፋይዳ ምንድን ነው ትላለህ?
4. ማቴ 6፥1-6 የታይታ ፍጅታን ብቻ አስበን ማድረግ የሌለብንን ለምንድን ነው ትላለህ?
    - ይህ ክፍል የምናደርገውን መልካም ነገር ሰው ቢያየው ችግር ይኖረዋል ብሎ ነው የሚያስተምረን?
    - ከማቴ 5፥13-16  ካለው ሃሳብ ጋርስ እንዴት ነው ሊስማማ የሚችለው ?
5. ይህ ክፍል በመደጋገም ስለ ግብዞች ይናገራል።
    - ግብዝ ማለት ምን ማለት ነው?
    - በማቴ 23፡27-28 ያለው ክፍል ስለ ግብዝነት ባህርይ ምን ይነግረናል?

- ግብዝነት በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ የማይኖረው ለምድን ነው?

6. ለምንድን አንዳድ ሰዎች የሚያደርጉትን ነገር ለታይታ የሚያደርጉት ትላለህ?
7. በማቴ 6፡7 ላይ ጸሎትን እንደ አሕዛብ እንዳንደግም ታዘናል? ለምን?

   - ጸሎትን እንደ አሕዛብ ብንደጋግም ችግሩ ምንድን ነው?
   - ጸሎት ማለት ራሱ ምንድን ነው?

8. ጌታ ምሳሌውን እንድንከተለው ያስተማረን የሐዋሪያት ጸሎት የሚያስተምረን ምንድን ነው?
9. በዳን 9፡3 ላይ ዳንኤል በጾመበት ጊዜ ያደርገውን ያንብቡ። ለታይታ የሚጾም ሰው ከዳንኤል ጋር ሲነጻጸር እንዴት ነው የሚለየው?

***መደምደሚያ***

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን ሰውን ያዳነው የዘላለምን ሕይወት እንዲቀበል ብቻ ሳይሆን **በዚህ የምድር ላይ ኑሮው መልካምን ሥራ እንዲሰራም ጭምር ነው** (ኤፌ 2፡2-10)። ሆኖም ግን አማኝ መልካም ሥራ የሚሰራው ለእግዚአብሔር ክብር፣ በቅንነት እና እግዚአብሔርን ከመውደድ የተነሳ እንጂ ለግል ክብር፣ ወይንም ሌላውን ሰው “ድንቅ ነው” ለማስባል አይደለም (1ኛ ቆሮ 10፡31)። እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ፣ በውስጣችን እና በአጠገባችን ቢኖርም አናየውም። እኛ ባናየውም ግን እሱ በስውር ያየናል (ማቴ 6፡4፣ 6 እና 18)። እግዚአብሔር ሲያይ ግን እንደሰው ከውጭ መመጽወታችንን፣ ወይንም መጸለያችንን እና መጾማችንን ብቻ ሳይሆን፣ ከበስተጀርባ ያለውንም አላማችንን ያውቃል፤ እሱ “የልብንም ስሜት እና አሳብ ይመረምራልና” (ዕብ 4፡12)። ስለዚህ ለምናደርገው መልካም ነገር ሁሉ ከጌታ ዘንድ ዋጋ እንድናገኝበት ነገሮችን የምናደርግበትን ምክኒያት ወይንም ዓላማ ልንመረምር ይገባናል።

# ጥናት አራት

## ማቴ 6፡19-34

## ጌታን እና የጌታ የሆነውን እንጂ ዓለምን እና የዓለም የሆነውን አትውደዱ (ለጌታ ወይንስ ለገንዘብ?)

**ዓላማ፡-** ጌታን ያመነ ሰው በዓለም ላይ ብዙ ፈተናዎች እንዳሉት አውቆ ነፍሱን ከሚያደክሙ ከተላያዩ ነገሮች ራሱን መጠበቅ እንዳለበት ማስገንዘብ (በተለይም በዚህ ክፍል መሠረት ከገንዘብ ፍቅር ራሱን እንዲጠብቅ ማሳሰብ)

***መግቢያ***

በማቴ 6፡24 ላይ የተዘገበው እውነት ሙሉውን የዛሬውን ጥናታችንን ሊጠቀልልልን ይችላል። **"ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፤ ወይ አንዱን ይንቃል ሁለተኛውንም ይወዳል፤ ወይ ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል፤ ለእግዚአብሔር እና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።"** በዚህ ጥቅስ ውስጥ ጌታ የሚያሳስበን ሁለት ነጥቦች አሉ። አንደኛው የቅደም ተከተል ወይንም የማበላለጥ ጉዳይ ነው። ሰው በአንድ ጊዜ ልቡን በእኩል ደረጃ ለእግዚአብሔር እና ለገንዘብ መስጠት አይችልም። ወይ ገንዘብ ከእግዚአብሔር በልጦበት፣ ለእግዚአብሔር እና ለሥራው ግድ የለሽ ሆኖ፣ ለገንዘብ ሲሯሯጥ ራሱን ያገኘዋል፣ አልያም እግዚአብሔር በልጦበት ገንዘብን ንቆት ይኖራል። ስለዚህ ሰው ቅደም ተከተሉን ሊያስተካክለው ይገባል። በክርስቲያን ዘንድ ግን፣ ገንዘብ ጌታ ሳይሆን ሊሆን የሚገባው መገልገያ (ባርያ) ነው። ለአማኝ እግዚአብሔር ብቻ ነው ጌታው ሊሆን የሚገባው። ሁለተኛው፣ እግዚአብሔር ሙሉ ልባችንን ሊገዛው እንደሚፈልገው ሁሉ፣ ገንዘብ፣ ሀብት፣ ንብረት የሚባለው ነገር፣ ሙሉ

ልባችንን ገዝቶ ከእግዚአብሔር ሊነጥለን የሚችል አደገኛ ወጥመድ ነው። ሰው ልቡን ከሰጠው፣ ገንዘብ ሰውን ከእግዚአብሔር ያርቃል።

ሀብት ማካበት፣ ገንዘብ ማጠራቀም፣ መድከም እና ደሞዝ ማግኘት ኃጢአት አይደለም ወይንም በመጽሐፍ ቅዱስ አልተከለከለም። እንዲያውም እንዲህ ያለው ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ የተደገፈ ጤነኛ ነገር ነው። ይህ ነገር ችግር የሚሆነው፣ ሰው የሚኖረው ገንዘብ ለማካበት ሲሆን፣ የየዕለት መሻት እና ጥማቱ ባለው ላይ መጨመር ብቻ ሲሆን፣ ለእግዚአብሔ መንግስት መስራት እና መድከም የሚባል ነገር መኖሩ ጠፍቶበት፣ ድካሙ ለራሱ ብቻ ለማጠራቀም ሲሆን፣ ካገኘው ሃብት ለጌታ የሚገባውን አስረኛ ለመስጠት መሰሰት ሲጀመር፣ ያለው በረከት በልጦበት ልቡን ለጌታ ማስገዛት ሲያቅተው ያኔ ችግር ይሆናል። ያኔ ገንዘብ ጌታ ሆነ ማለት ይሆናል፤ ሰውየም የገንዘብ ባሪያ ሆነ ማለት ይሆናል (ሉቃ 18፥18-30 ያለውን ታሪክ ያወዳድሩ)።

ታዲያ አማኝ እንዴት ነው ራሱ ለእግዚአብሔር ተገዝቶ፣ ገንዘብን ግን ተገዢ አድርጎ መኖር የሚችለው? በዛሬ ጥናታችን፣ የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 6 ከቁ 19-24 ባለው ክፍል በመደገፍ፣ ለዚህ ጥያቄ ክፍሉ የሚነገረንን ሦስት እውነቶች እንመለከታለን። አማኝ የእግዚአብሔር እና የገንዘብ ትክክለኛ ቦታ ሳይዛባበት መኖር የሚችለው አንደኛ ሀብቱ እና ልቡ በሰማይ ሲሆን፣ ሁለተኛ፣ ገንዘብን እና እግዚአብሔርን የሚመለከትበት አስተያየት ጤነኛ ሲሆን እና በሦስተኛ ደረጃ አስቀድሞ የሚፈልገው የእግዚአብሔርን መንግስት እና ጽድቅ ሲሆን ነው።

## ፩. መዝገባችን እና ልባችን በሰማይ ሲሆን (19-21)

በማቴ 6፡19-20 ባለው ክፍል “መዝገብ አትሰብስቡ” እና “መዝገብ ሰብስቡ” የሚሉ ሁለት ትዕዛዛቶችን እናገናለን። “**መዝገብ**” የሚለው ቃል በአሁኑ ጊዜ አማርኛ ሀብት ማለት ነው (አዲሱ መደበኛ ትርጉምን ያነጻጽሩ)። ስለዚህ ትዕዛዙ ሀብትን ስለመሰብሰብ እና ስለ አለመሰብሰብ ነው።

የመጀመሪያው ትዕዛዝ የአታድርጉ ትዕዛዝ ነው፤ “በምድር መዝገብ አትሰብስቡ።” በጌታ አስተምህሮ መሰረት በምድር ሀብት የመሰብሰቡ ችግር ዘለቄታ የሌለው መሆኑ ነው። የምድር ላይ ሀብት፣ ብል እና ዝገት ይበላዋል፣ ሌባ ይሰረቀዋል። ሰው ብል ያልነካው፣ ዝገት ያልሰረሰበት፣ ሌባ ያልደረሰበት ሀብት እንኳ ቢኖረው፣ አንድ ቀን ጥሎት ለስከወዲያኛው ያሸልባል። በምድር ላይ የሚዘልቅም ሆነ የሚያዛልቅ ምድራዊ ሀብት መሰብሰብ የሚችል ማንም የለም። በዚህ ዓለም ላይ ሀብት ማካበት እየከሰረ ባለ ድርጅት ላይ ኢንቨስት እንደ ማድረግ ነው። ለዚህ ነው ጌታ በዚህ አለም ላይ ለራሳችሁ ሀብትን አትሰብስቡ ማለቱ።

በእርግጥ ይህ ሲባል፣ ገንዘብ ማጠራቅም፣ ባለ ሀብት መሆን ኃጢአት ነው ወይ የሚል ጥያቄ ይፈጥራል። ሆኖም ግን ጌታ እየከለከለ ያለው ያንን አይደለም። እንዲያውም አማኝ ሰርቶ የሚያገኝ፣ የሚይያጠራቅም፣ ቤተሰቡን እና ሌሎች ችግረኞችን የሚረዳ እንዲሆን ይገባል። በዚህ ክፍል ላይ እየተናገረ ያለው ሰለ ሰማያዊው ነገር እረስቶ፣ ድካሙ እና ጥረቱ ሀብት ማካበት እና ራስን በምድራዊ ነገር ማስደሰት ብቻ አላማ አድርጎ መኖር ተገቢ አለመሆኑን ነው። እንዲህ ያለው ሰው ብል እና ዝገት ሀብቱን የበሉት እለት፣ ሌባ ንብረቱን የሰረቀበት ቀን፣ የተፈጥሮ አደጋ ያለውን ያወደመበት ጊዜ ወይንም የምድር ኑሮው ያበቃ ሰዓት፣ ሌላ የለውም እና ባዶውን ይቀራል። በሉቃ 12፡16-21 ባለው ክፍል ለዚህ ጥሩ ድጋፍ የሚሆን ምሳሌ ጌታ ይሰጣል። በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ባለ ጠጋ፣ በዚህ ምድር ላይ ሀብት አከማችቷል። ሳያስበው ግን ያለውን ሁሉ ጥሎት የሚሄድበት ቀን ደርሷል። ችግሩ ይህ ባለጠጋ ምንም በምድራዊ ነገር ሀብታም ቢሆን፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ባለጠጋ አልነበረም (ቁ. 21)። ያለውን ሁሉ ጥሎ ወደ እግዚአብሔር በሚሰበሰብበት ሰዓት፣ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠራቀመ

ሀብት የለውም። “አንቺ ነፍሴ፣ ለብዙ ዘመን የሚቀር ብዙ በረከት አለሽ” የተባለው ሀብት ለምንም ይሆናል። ስለዚህ ችግሩ ሀብት ማጠራቀሙ ሳይሆን በጌታ ዘንድ የሚጠራቀም ሀብት ሳይኖር፣በምድራዊ ሀብት ብቻ መመካቱ ነው።

ሁለተኛው ትዕዛዝ የአድርጉ ትዕዛዝ ነው፤ “በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ”። በሰማይ መዝገብ የመሰብሰቡ ጥቅም፣ ከላይኛው በተለየ ብል፣ ዝገት፣ ሌባ፣ የተፈጥሮ አደጋ፣ ኪሳራ ወይንም ሞት አያጠፋውም። ስለዚህ በሰማይ ሀብት ያለው፣ ወደ ጌታው መሰብሰቢያው የደረሰ እለት እንደ ሞኙ ባለጠጋ፣ ባዶውን አይቀርም፤ የሚሔደው ወደ ሌላኛው በረከቱ ነውና።

ይህ ሲባል፣ እንዴት ነው በሰማይ ሀብት የሚሰበሰበው የሚል ጥያቄ ይነሳል። ሰው በጌታ ዘንድ ባለጠጋ የሚሆነው፣ ዛሬ ባለው ጊዜ እና ሀብት እግዚአብሔርን፣ እያገለገለ፣ መንግስቱን እያሰፋ፣ ችግረኞችን እየረዳ ሲኖር ነው። ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ ክሬዲት የሚያስቀምጠው ዛሬ በዚህ ምድር ለእግዚአብሔር ብሎ በሚያደገው ሥራ ነው። ለዚህ አሳብ ጳውሎስ ስለ ባለጠጋዎች ለጢሞቴዎስ የሰጠውን ትዕዛዝ ከ1ኛ ጢሞ 6፡17-19 በማንበብ የነጻጽሩ።

ጌታ እነዚህን ሁለት ትዕዛዛት ከሰጠ በኃላ ጌታ፣ ሰው ለምን መዝገቡ በሰማይ መሆን እንዳለበት ያስረዳል። “መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና” (ማቴ 6፡21) ። ሰው ልቡን የሚጥለው ሃብቴ፣ ጥሪቴ በሚለው ቦታ ነው። ምድራዊ ሃብት ብቻ ለማካብት የሚኖር ሰው ልቡ ምድራዊ ነው፤ እንዲሁ ለእግዚአብሔር መንግት የሚደክመው እና ሰማያዊ ሃብት የሚያካብተው ሰው፣ የሚጥረው ልቡ በሰማይ ስለሆነ ነው። እንግዲህ በመግቢያችን ላይ ሰው እንዴት ነው ለእግዚአብሔር ተገዝቶ፣ ገንዘብን ግን ገዝቶ መኖር የሚችለው ላልነው ጥያቄ መልሱ መዝገባችን እና ልባችን በሰማይ ሲሆን ነው።

## ፪. እይታችን (አመለካከታችን) ጤነኛ ሲሆን (22-25)

ከቁ 22-23 ባለው ሰው ለእግዚአብሔር እና ለገንዘብ የሚገባቸውን ትክክለኛ ቦታ ሰጥቶ መኖር የሚችለው ጤነኛ አይን ሲኖረው እንደሆነ ጌታ

ያስተምራል። በዚህ ክፍል ላይ “አይን” ሲል የሚናገረው፣ በሥጋዊ አይን ምሳሌ ስለ አስተያየት፣ አመለካከት (attitude) ነው። አይን “የሰውነት መብራት ናት።” በዚህች የአይን ብርሃን እየተገዘ ሰው ጤነኛ አካሄድ ይሄዳል። ይህች አይን ጤነኛ ከሆነች፣ ሰው ሰውነቱ (አካሄዱ) የቀና፣ መንገዱ የሰላም ይሆናል። ልክ እንዲሁ፣ ይህች አይን ጤነኛ ካልሆነች፣ መንገዱ እንቅፋት የበዛበት፣ አካሄዱ የተዛባ እና ያላማረ ይሆናል። ልክ እንዲሁ፣ ስለገንዘብ እና ስለ እግዚአብሔር ያለን አመለካከት ጤነኛ ከሆነ ኑሮአችን እንደ እግዚአብሔር ቃል ይሆናል፣ አመለካከታችን የተዛባ ከሆነ ግን፣ ለእግዚአብሔር እና ለገንዘብ የምንሰጠው ቦታ ይዛባ እና ኑሮአችንም ይዛባል።

ከላይ የጠቀስነውን ባለ ጠጋ ብናነሳ፣ ለእግዚአብሔር ተገቢውን ቦታ ሳይሰጥ፣ በጌታም ዘንድ መዝገብ ሳይሰበስብ፣ ምድራዊ ሃብትን ብቻ ሲያካብት እንዲኖር ያደረገው አመለካከቱ ጤነኛ ስላልነበረ ነው። አመለካከት ለነገሮች የምንሰጠውን ዋጋ ያሳያል። ይህም ሰው  ትልቅ ዋጋ የሰጠው ጥሪቱን ማዳበር ነበረና የሚታየው እግዚአብሔር እና መንግስቱ ሳይሆን፣ ነዋይን መሰብሰብ ነበር። ምድራዊ በረከት አይኑን አሳወረው፣ ጭፍን አመለካከቱ ነዋይን ከእግዚአብሔር አስበለጠበት። ፍጻሜው ባዶነት ሆነ።

እንግዲህ ስለ አመለካከት ከተናገረ በኍዋላ ነው ጌታ ሰው ለገንዘብ እና ለእግዚአብሔ መገዛት እንደማይቻል ያሳሰበው። ሰው ወደፊት የሚታየው፣ እግዚአብሔርን ማገልገል እና ለእሱ መገዛት፣ በሚያገነው እና በሚያካብተው እግዚአብሔርን ማክበር ከሆነ ጤነኛ ነገር ነው። ግን ሰው የሚታየው ባለጠጋ መሆን፣ መክበር፣  በሀብት ላይ ሌላ ሀብት ብቻ ከሆነ፣ ሳያውቀው ገንዘብን ጌታው አድርጓል ማለት ነው። ስለዚህ እንደገና አማኝ እንዴት ነው ራሱ ለእግዚአብሔር ተገዝቶ፣ ገንዘብን ግን ተገዢ አድርጎ መኖር የሚችለው ለሚለው ጥያቄአችን መልሱ አመለካከታችንን ወይንም ዋጋ የምንሰጠውን ነገር ማስተካከል ነው።

## ፫. መሻታችን የእግዚአብሔር መንግስት እና ጽድቅ ሲሆን (25-34)

ሰው ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ተሰጥቶ እንዳያገለግል እና ልቡን በምድራዊ ነገር ላይ እንዲጥል የሚያደርገው፣ ጭንቀት ነው - ምን እበላለሁ፣ ምን እጠጣለሁ፣ ምን እሰራለሁ፣ ምን እለብሳለሁ እና ምን እሆናለሁ? የሚል ጭንቀት። አንድኛውም ሰው ምድራዊ መዝገብ ለመሰብሰብ እንዲሯሯጥ የሚያደርገው፣ ለዚህ ጭንቀቱ መፍትሔ የሚሰጠው ገንዘብ እንደሆነ ስለሚያስብ ነው። ሆኖም ግን ከላይ እንዳየነው ገንዘብ ለሰው ልጅ ዘላቂ መፍትሔ አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር ሰው ለሚጨነቅበት ነገር እውነተኛ መፍትሔ ነው። ስለዚህ ጌታ በማቴ 6፡25-34 ባለው አማኝ በመጨነቅ ፈንታ፣ መሻቱ እና ጥማቱ የእግዚአብሔር መንግስት መሆን እንዳለበት ያሳስባል።

ይህ ክፍል ሰፋ ስለሚል ጌታ በትክክ እየሰጠ ያለውን ትዕዛዝ (መመሪያ) በግልጽ ለመለየት የሚያስቸግር ቢመስልም ግን በክፍሉ ያሉት ሁለት ትዕዛዞች ናቸው - “አትጨነቁ” (ቁ. 25፣ 31 እና 34) የሚል እና “አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግስት … ፈልጉ” (ቁ. 33)። የመጀመሪያውን አትጨነቁ የሚለውን አሳብ ስናነሳ፣ ጌታ ለምን ሰው በምድራዊ ኑሮ ስለሚገጥመው መጨነቅ እንደሌለበት ያስረዳል።

በመጀመሪያ፣ ለነፍሳችን ለምንበላው፣ ለሰውነታችን ለምንለብሰው የምንጨነቅ ከሆነ፣ በእግዚአብሔር ላይ አለመታመናችንን ያሳያል። ጌታም በዚህ ክፍል የሚጠይቀው ጥያቄ ስለምን ስለነዚህ ትጨነቃላችሁ፤ “ነፍስ ከመብል ሰውነትም ከልብስ አይበልጥምን?” (ማቴ 6፡25) የሚል ነው። እግዚአብሔር ለሰው ነፍስ እና ሰውነትን ከሰጠ፣ መብል እና ልብስ ለማግኘት ሰው ሊጨነቅ አይገባም። ከመብል እና ከልብስ የሚበልጠውን ነፍስ እና ሰውነትን የሰጠ እግዚአብሔር ትንሹን ለመስጠት አይሰስትም። የሰማይ ወፎችን እና የሜዳ አበቦች የሚያስተምሩን ይህንን ነው። ወፎች ሳይጨነቁ፣ የዕለት እንጀራቸውን አግኝተው ያድራሉ፤ ምክኒያቱም ነፍስ እና ሥጋ ያበጀላቸው አምላክ ይመግባቸዋልና (ማቴ 6፡26)። ልክ እንዲሁ እግዚአብሔር አባታችን ነፍስ እና ሰውነት ከሰጠን፣ ለነፍስ እና ለሥጋ የሚያስፈልገውን እንዲሁ አብሮ ይሰጣል።

ሁለተኛ፣ ጭንቀት በሰው ሕይወት ውስጥ ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት የማይችል ነገር ነው (27)። ሰው ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አይጨምርንም፣ የጸጉሩን ቀለም አይለውጥም ወይንም ለሰውነቱ ልብስ፣ ለሆዱም ምግብ ማምጣት አይችልም። መጨነቅ በራሱ ራስን የሚጎዳ ከመሆኑ ሌላ፣ ለውጥ ላያመጡ መጨነቅ ግን ትርጉም የለሽ ነገር ነው።

ሦስተኛ፣ ለሰው የሚያስፈልገውንእግዚአብሔር ስለሚሰጥ ሰው ሊጨነቅ አይገባም(28-32)። ጌታ ይህንን አሳብ ለማስጨበጥ የሜዳ አበቦችን እና የሜዳ ሣርን እንደ ምሳሌ ያነሳል። እነዚህ እጽዋት የሜዳ እንደመሆናቸው ተንከባባቢ የሌላቸው ከመሆናቸው ሌላ ነገ የሚጠፉ (ወደ እቶን) የሚጣሉ ናቸው። ግን እግዚአብሔር ይንከባከባቸዋል። ሰው ግን በሁሉም መንገድ ከሜዳ አበባ እና ሣር ይበልጣል። እግዚአብሔር እነዚህን ከተንከባከበማ፣ በእርሱ የሚያምኑበትን ልጆቹንማ እንዴት እንደሚንከባከባቸው ማሰብ አይከብድም (ቁ. 30 -31)። እግዚአብሔር ለሰው የሚያስፈልገውን አስቦ ከመስጠቱ ሌላ፣ እግዚአብሔር ለሰው የሚያስፈልገውን ያውቃል። እግዚአብሔር የሚያስፍልገንን ገና ከአፋችን አውጥተን ሳንናገር በፊት እንኳ ያውቃል (ማቴ 6፡8)። ሰው ሲጨነቅ፣ አንዳንዴ የሚጨነቀው ነገ ሊጎዳው እና ሊያጠፋው ስለሚችል ነገር ሊሆን ይችላል። ሰው በራሱ የሚያስፈልገውን ላያውቅ ይችላል። እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ከማወቅ በላይ፣ የሚያስፈልገንን ይሰጣል። ስለዚህ ሰው ሊጨነቅ በማይገባው ነገር ተጨንቆ፣ ለጭንቀ መፍትሔ ይሆናል በሚለው ሀብት እና ነዋይ ጎዶሎውን ሊሞላ ሲጣጣር፣ ራሱን ለገንዘብ ሲገዛ እና ከአምላኩ ሲርቅ እንዳያገኘው ሊጠነቀቅ ይገባል።

ከቁ 25-32 ሰው መጨነቅ እንደማይገባው አስረግጦ ከተናገረ በኋላ፣ በመጨነቅ ፈንታ ምን ማድረግ እንዳለበት በቁ.33 ላይ ያስረዳል። “ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግስት ጽድቁንም ፈልጉ፣ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።” ስለዚህ ክርስቲያን ለጭንቀቱ መፍትሔ ይሆናል የሚለውን ምድራዊ መዝገብ ለራሱ ለመሰብሰብ ከመጣር ይልቅ በመጀመሪያ የእግዚአብሔር መንግስት ሊፈልግ ነው የሚገባው። ከላይ እንዳልነው፣ ገንዘብ ማግኘት፣ ባለጠጋ መሆን ነውርም፣ ኃጢአትም አይደለም። ግን

በመጀመሪያ የእግዚአብሔር መንግስት ሊቀድም ይገባል - ያለ እግዚአብሔር የተጠራቀመ ሁሉ ይበተናልና።

እንግዲህ ሰው ለእግዚአብሔር ባሪያ ሆኖ ገንዘብን ግን ባሪያ አድርጎ እንዴት ነው መኖር የሚችለው ካልን መልሱ እግዚአብሔርን እና መንግስቱን በመጀመሪያ ሲያስቀድም ነው።

## ለውይይት የተዘጋጁ ጥያቄዎች

1. በማቴ 6፡19 -20 ባለው ክፍል መዝገብ ተብሎ የተጠቀሰው የሚያመለክተው ምንድነው?
2. በቁ. 19 "ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ" ሲል ምን ማለት ነው? ሀብትን ማዳበር፣ ገንዘብ ለነገ ማስቀመጥ ኃጢአት ነው ማለት ነው?
3. ሰው በሰማይ መዝገብ የሚሰበስበው እንዴት ነው? በምድር ላይ ከሚሰበሰበው መዝገብስ ጋር ልዩነቱ ምንድን ነው?
4. ማቴ 6፡.24 ለሁለት ጌቶች መገዛት አትችሉም የተባለው ለምድን ነው? እንዴት ነው ገንዘብ ጌታ የሚሆነው?
5. ሰው በህይወቱ እግዚአብሔርን እና መንግስቱን አስቀድሞ መኖር የሚችለው እንዴት ነው? በምሳሌ ማስረዳት ትችላላችሁ?
6. በማቴ 6፡25-31 አትጨነቁ የሚለን ለምንድን ነው? ጭንቀታችንንስ የምናስወግደው እንዴት ነው? ማሰብ እና ጭንቀት ልዩነቱ ምንድ ነው? ከ 1ጴጥ 5፡7 በማስተያየት ተወያዩበት።

7. ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፣ ሳይጨነቁ እግዚአብሔር በቸርነቱ እየመገበ ያኖራቸውን እነማንን ታስታውሳለህ?
8. በአጠቃላይ ከዛሬው ትምህርታችን ምን ተማርክ?

***መደምደሚያ***

ከላይ የዘረዘርነውን በሌላ አባባል ለመጠቅለል፣ ሰውን ከእግዚአብሔር የሚነጥል ወጥመድ እና መሻት ዓለማዊ ምኞት ይባላል። ገንዘብን መውደድ አንደኛው እና አደገኛው ዓለማዊ ምኞት ነው። ገንዘብ በራሱ ምንም ችግር ባይኖረውም፣ ግን እሱን መውደድ የእግዚአብሔርን ቦታ እና **<u>አምላክነት የሚሻማ ነገር ነው።</u>** ስለዚህ ሰው ዓለምን ሊጠላ፣ በምድር ላይ ሀብትን ማካበት ብቻ ትቶ አስቀድሞ ሰማያዊ መዝገብ ሊሰበስብ ይገባል። የእግዚአብሔርም ቃል ዓለምን እንድንጠላ እና ፈቃዱን ግን እንድናደርግ ይመክረናል። 1 ዮሐ 3፡15~17 "ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም ... ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል።"

## የማቴዎስ ወንጌል ማቴ 7፡1-29

የምዕራፉ ዓላማ

ለአማኝ እጅግ የላቀ ሥነ ምግባር አስፈላጊ እንደሆነ ማስገንዘብና መፍረድንና ከፍርድ ጋር የተያያዙ የሥነ ምግባር ጉዳዮችን ማጥናት

አጠቃላይ የክፍሉ መግቢያ ሀሳብ

አማኝ በሕግ አቅም መንፈሳዊ ህይወት እንኖራለን ከሚሉት የተሻለ ህይወት መኖር አለበት። ስለ ፍርድ ስናይ ፈረደ የሚለው ቃል ፈረጀ ከሚለው የመጣ ሲሆን፡ ፈረጀ ማለት ፡ነገርን ከተመለከተ ወይንም ካየ በኃላ መልክ መልኩን አስያዘ ወይንም በመልክ በመልኩ ለየ፡ ሲሆን ነገርን በመልክ በመልኩ መለየት ወይንም መፈረጅን ያመለክታል።

ፈረደ፡ በከሳሽ እና በተከሳሽ መካከል ያለውን ክርክር ተመልክቶ ውሳኔ በመስጠት ጥፋተኛውን ከተበዳዩ መለየት፡ አንዱን በዳይ ሌላኛውን ተበዳይ የሚያደርግ ብያኔ ማሳለፍ። ፈረደ ወይንም ኮነነ አንዱን በመኮነን ሌላውን በማጽደቅ ፍርድ ወይንም ብያኔ ማስተላለፍ

ፈራጅ፡ የዳኝነትን ሥራ የሚያመለክት ሲሆን፡ በበዳይ እና ተበዳይ መካከል ያለውን ጉዳይ መርምሮ በተበዳዩ ላይ እና ለተበዳዩ መፍረድ ወይንም ብያኔ ማስተላለፍን ያመለክታል፡ፍርደ ገምድል መሆን፡ ጉዳይን ወይንም እውነታን በትክክል ሳይመረምሩ ወይንም ሳያጤኑ፡ በእውነታ ላይ ሳይመሰረቱ እና ሳያመዛዝኑ በጭፍን ወይንም በግምት ፍትህን ባጎደለ መልኩ፡ ወደ አንድ ወገን ያዳላ ድምዳሜ ላይ መድረስን ያመለክታል

እውነተኛ ወይንም ጻድቅ ፈራጅ፡ በሚታየው እውነታ ላይ ብቻ ተመርኩዞ ሳይሆን የማይታይ የተሰወረውን ልብን እና ኩላሊትንም ጭምር መርምሮ ፍትህን ማዕከላዊ ከማድረግ ያለፈ ጽድቅን መግለጥ ነው። ፍርዱ የማይዛባ እንከን የማይወጣለት ይሄ ይቀረዋል የማይባል ጻድቅ ፈራጅ የሆነ የሚኮንን የሚያጽድቅም አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

የዚህን ክፍል ሀሳብ ለማግኘት በጥቂቱም ቢሆን ጌታ ኢየሱስ ያስተማረበትን አውድ መመልከቱ በጣም አስፈላጊ ይሆናል፡ በዚያን ዘመን የነበሩት ጸሀፍትና ፈርሳዊያን  ወግ እና ልማድቸው፡ አንድ ሰው በሌሎች ሰዎች ፊት የሚኖረው ገጽታው ከሌሎች የተሻለ እና የበለጠ በመሆኑ ላይ ያተኮረ ነበር፡ ከዚህ የተነሳም ሰው ለራሱ ገጽታ የሚሰጠው ስፍራ ከእውነታ ጋራ መራራቅ እና መጣረሱ የተለመደ የዕለት ተዕለት ተግባር ነው። ከዚህ ሁሉ በላይም  የሌላውን ሰው ገጽታ ዝቅ አድርጎ በማሳየት ወይንም በሌሎች በማስገመት የእራስን የተሻለ ገጽታ መሳል እና መካብ ወይንም እራስን  ክፍ አድርጎ ማሳየት የተለመድ ጉዳይ ነበር። እራስን ከሌላው ጋር አነጻጽሮ የተሻሉ ሆኖ በመገኘት ላይ የተመሰረተ ጽድቅ እኔ እንደ እከሌ ወይንም እንከሊት አይደለሁ ይህ አደርጋለሁ ያንን አላደርግም እያሉ በንጽጽሮሽ የራስን ጽድቅ ለማቆም መሞከር ነው። ሉቃ 18፡11-12

በተለይም ከምዕራፍ አምስት ጀምሮ በዚህ ሁኔታ መካከል ተገኝቶ ነበር ጌታ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ለብቻቸው በመውስድ   ከፈሪሳዊያን እርሾ እንዲጠበቁ በመደጋገም ሲያስተምራቸው እና ሲያስጠነቀቃቸው የነበረው። በዚህ በተከታታይ ትምህርቱ ውስጥ ጌታ ኢየሱስም የውጫዊ ገጽታን በማሳመር እና የራስን ጽድቅ ለማቆም በመፈለግ ላይ ያተኮረውን የጻሐፍት እና የፈርሳዊያንን  አስተምህሮት እና አስተሳሰብ በማረም ወይንም በማስተካከል፡ እውነተኛ  የጽድቅ መለከያ ሊሆን የሚገባውን የተሻለውን እና የሚበልጠውን መንገድ ለማሳየት ዓላማ ያደረገ ትምህርት እየሰጠ መሆኑን ማጤን ይኖርብናል።

ጌታ ኢየሱስን በአስተምህሮቱ ሐዋሪያቱም በመልዕክቶቻቸው ከዳር እስከ ዳር በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሰው ለራሱ የሚሰጠውን ስፍራ እና እራሱን የሚመለከትበትን ዕይታ ለውጦታል። ይኸም ብቻ አይደለም አንዱ ለሌላው ሰው ሊሰጠው የሚገባውን ስፍራም ሆነ አንዱ ሌላውን ሰው የሚመለከትበትን መንገድ ሙሉ በሙሉ አስታካክሎታል። በዚህ በተለወጠ አስተሳሰብና እይታ ካልሆነ በስተቀር ሰው እራሱንም ሆነ ሌሌላውን ሰው ሊያይበት የሚችለው የተፈወሰ ጤናም እይታ በፍጹም ሊኖረው አይችልም ነበር። ጻድቅ የለም አንድም እንኮን ሁሉም ኃጢያትን ሰርተዋል

የእግዚአብሔርም ክብር ጎላቸዋል ሮሜ3፡19-23 ከዚህ በኃላ አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፡ ባሪያ ወይንም ጨዋ ሰው የለም፡ ወንድም ሴትም የለም፡ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁ፡ ገላ3፡28 በዚያም የተገረዘም ፡ ያልተገረዘ አረማዊም እስኩቴስም መሆን አልተቻለም ቆላ3፡11 ። ሰው ራሱን ሆነ ሌላውን በስጋ እንደሆነ ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሱስ እንደሆነ ማየት እንዳለበት አበክሮ ያስተምራል 2ቆሮ5፡16-17 ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው አሮጌው ነገር አልፎል ሁሉም አዲስ ሆኖል ይላል፡ በመቀጥልም ስለዚህ እኛ ከአሁን ጀምሮ ማንንም በስጋ እንደሚሆን አናውቅም በማለት በውጫዊ ገጽታ ላይ እንዳናተኩር ይልቁም የተሰውረ ውስጠኛው ገጽታችን ወይንም ማንነት ላይ ማተኮር ያለብን እንደሆነ ያስተምረናል። ስለ እራሳችንም ሆነ ስለሌላው ማሰብ ከሚገባን አልፍን እንዳናስብ ያስጠነቅቀናል ሮሜ 14፡12 እንግዲህ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንድንሰጥ ይገባል እንጂ የሌላው ሰው አስተሳሰብ እና ድርጊት ልንኮንን እንደማይገባ። ይልቁንም ሰው ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል የሚቆጥርበት የትህትና ልብ እና መንፈስ ከኢየሱስ ክርስቶም እንድንማር ያሳስበናል፡ ፊሊ2፡3 በአጠቃላይ ጌታ ኢየሱስ በነዚህ ምዕራፎች ትምህርቱ ጽድቃችን ከጻፎችና ከፈርሳዊን ጽድቅ በልጦ መገኘት እንዳለበት በማያሻማ መንገድ አስምሮበታል፡ እርሱ ብቻ አይደለም በዚያን ዘመን ከነበሩት ጻፎችና ከፈርሳውያንም እርሾ (ከግብዝነት) መጠበቅ እንዳለብን በመደጋገም አስትምሮል።

## ምዕራፍ 7 ፥1-29

## ክፍል ፩
## ጥናት  አምስት
## የንባብ ክፍል ማቴ 7፥1-5

የጥናቱ ዓላማ፥

በዚህ ጥናት በሌሎች ሰዎች ላይ ከመፍረድ እንድንቆጠብ እና እንድንጠነቀቅ የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረንን ማየት ነው።

መግቢያ፥

የእግዚአብሔር ቃል በብዙ ስፍራ በሌላ ሰው ላይ ፍርድ ከማስተላለፋችን በፊት መጠንቀቅ እንዳሚገባን ያስተምረናል። በተለይም በዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያዎቹ አምስት ቁጥሮች ላይ ጌታ እየሱስ በሌሎች ላይ ከመፍረዳችን አስቀድመን ስለ እራሳችን ህይመው እና ስለ ጉድለታችን ሚዛናዊ እና ጤናማ ግንዛቤ ወይንም እይታ እንዲኖረን ያሳስበናል። ስለ እራሳችን ሚዛናዊ እና ጤናማ ግንዛቤ የሚኖረን ከሆነ በሌሎች ላይ በትንሹም ሆነ በትልቁ  ፈጥነን የምንፈርድባቸው ከመሆን ያድነናል፥እርሱም ብቻ አይደለም በአጸፋውም ሌሎች በእኛ ላይ  ከሚሰነዝሩብን ፍርድ እናመልጣለን ።

### አጭር የምዕራፉ ማብራሪያ

**ማቴ 7፡1-2** ጌታ በማንም ሰው ላይ በግብዝነት ወይንም በመመጻደቅ መፍረድ እንደማይገባን ያስተምረበት ክፍል ነው፥ ምክኒያቱም በግብዝነት የምናደርገው ፍርድ ሚዛን የጠበቀ  እንደማይሆን ሁላችንም እማናውቀው ጉዳይ ነው፤ ይህም ብቻ አይደለም የእራሳችንንም ጉድለት ወይም ድካም በግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም፥ በሌላው ሰው ጉድለት እና ድካም ላይ ብቻ ያነጣጠር  ስለሆነም ሌሎች ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ቀላል አይሆንም፥ ስለዚህም የምንፈርድባቸው ሰዎች አጸፋ ወይንም ምላሽ እንዲሰጡ ስለሚገደዱ በፈረድነው ፍርድ መልሰን በሌሎች እንዲፈረድብን

እናደርጋለን ማለት ነው። ግብዝነት እና ትምክህት በሌለበት እውነት እና ጽድቅ በሆነ ጉዳይ ግን ይሄ ልክ ነው ወይንም ይሄኛው ልክ አይደለም ለማለት እንችላለን።በሌሎች ላይ ከመፍረዳችንም ሆነ ሌሎች በእኛ ላይ ከመፍረዳቸው በፊት የሁላችንም ህሊና ትክክለኛውን ሚዛን እንደሚያቅ መዘንጋት የለብንም ስለዚህ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ህሊናችንም እንዳይፈርድብን መጠንቀቅ ያስፈልገናል።

**ማቴ 7፡ 3** በዚህ ቁጥር መሰረት በሌላው ሰው ላይ ያለውን ጉድፍ ወይም ጉድለት ማየት በራሱ ምንም ችግር ያለበት ነገር አይደለም፥ ይሁን እንጂ ታዲያ በሌላው ሰው ላይ ያለውን ጉድፍ ወይም ጉድለት የምናይበት እይታ ጤናማ መሆን አለመሆኑ ላይ ነው ችግሩ ያለው፤ አንድ ሰው ወንድሙን የተሻለ እንዲሆን ፈልጎ ወይንም አስቦ ከሆነ የሚበረታታ እና ሊደረግ የሚገባ ጉዳይ ነው፥ በአንጻሩ ግን በወንድሙ ላይ ስላየው ጉድለት ወንድሙን ለመኮነን ወይም ለማሳጣት የሚደረግ ከሆነ እንዲህ ዓይነት የሚደገፍ የሚበረታታ አይደለም።

**ማቴ 7፡4** በዚህ ቁጥር መሰረት በሌላው ሰው ላይ የሚፈረድ ሰው ዋናው ሊያስተውለው የሚገባው ጉዳይ መሰረታዊ ጉዳይ የእይታው ሚዛናዊ ወይንም ጤነኛ መሆን አለመሆኑ ጉዳይ ነው።

**ማቴ 7፡ 5** ስለዚህ በዚህ ክፍል ጌታ ያስተማረው አንድ ሰው በሌላው ሰው ላይ ከመፍረዱ አስቀድሞ ወይንም በሌላው ሰው ውስጥ ያለው ጉድፍ ለማውጣት ከመሞከሩ በፊት ስለ እራሱ ህይወት እና ጉድለት በቅድሚያ በቂ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖረው ያሳስባል፥ ምክኒያቱም ሰው ስለ እርሱ ህይወት እና ጉድለት በቂ ግንዛቤ ሳይኖረው በሌላው ሰው ላያ ስላለው ጉድለት ትክክለኛ እና ሚዛናዊ ነገር ይኖረዋል ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ነው።

እንደ እግዚአብሔር ቃል ስለእራሳችንም ሆነ ለሌሎች ያለን አመለካከት ጤናማ ከሆነ ከላይ እንደተጠቀሰው ይሄ ትክክል ነው ይሄኛው ግን ትክክል አይደለም የምንልበት ድፍረቱም ሊኖረን ይገባል። በዚህ ክፍል መሰረት እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ ነው ስንል እርሱ ሁሉን በትክክለኛ ሚዛን

የሚያይ እና ትክክለኛው ፍርድ የሚሰጥ ነው ማለታችን ነው በ1ቆሮ5፥1-5 እና 6፥1-5 ስንመለከት ሐዋሪያው ጳውሎስ በቅዱሳን መካከል በምግባረ ብልሹነት ስለተመላለሱት ሰዎች ላይ ስላስተላለፈው ፍርድ እንዲሁም ቅዱሳን በመካከላቸው ስለሚፈጠሩ አለመግባባቶች በመካከላቸው እንዲፈቱ ያሳሰበት እና ያስተማረበት ክፍል ነው።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ማቴ 7፡1-2 አትፍረዱ የሚለውን ሀሳብ እንዴት ትረዱታላችሁ? በምንም መልኩ መፍረድ አንችልም ማለት ነው? ይብራራ።
2. ይፈረድባችኃል የሚለውን ሃሳብ እንዴት ትረዱታላችሁ? የሚፈርድብንስ ማን ነው? ህሊናችን ምን ሚና ይኖረዋል ትላለህ?
3. ማቴ 7፡ 3 መሰረት በወንድም ወይንም በእህት አለያም በሌላ ሰው ላይ ያለውን ጉድፍ ማየት በራሱ ምን ችግር አለበት?
4. ማቴ 7፡4 በሌላው ሰው ላይ የሚፈርድው ሰው መሰረታዊው ችግር ምን መሆኑን ነው የሚያመለክተን? መክ 2፡14 ስለ ጠቢብ ዓይኖች ምን ይናገረል?
5. ማቴ 7፡ 5፡ መሰረት አንድ ሰው በሌላ ሰው ላይ ያለውን ጉድፍ ከማውጣቱ በፊት እራሱ እንዲያደርግ የተመከረው ምንድነው?
6. ቁ. 5 የራስ ስህተት እያለ ሌላውን ለማረም አስቸጋሪ የሚያደርገው ምንድን ነው? አጥርቶ ማየት ማለት ምን ማለት ነው?
7. እንደ እግዚአብሔር ቃል እይታችን የተስተካከለ ቢሆን ትክክል በሆነና ባልሆነ ጉዳይ ላይ መፍረድ እንችላለን ወይንስ አንችልም? ከዚህ ክፍል አንጻር እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው?

8. በ ፲ቆሮ፭፥ ፲-፭ እና ፮፥፲-፭ በማንበብ በክፍሉ ስለለው ሃሳብ በስፋት ተነጋገሩበት። ከዚህ ጥናት ጋር እንዴት ይገናኛል።
9. ከዛሬው ጥናት ውስጥህን በተለየ መንገድ የነካው ነገር ካለ ወይንም ጥያቄ ካለ አካፍል።

**መደምደሚያ፥**

በሌላው ሰው ላይ የምናየውን ጉድለት ማጉላት በጣም ቀላል እና ምንም ጥረት ወይንም መንፈሳዊነት የማይጠይቅ ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ በሌላው ሰው ላይ ስንፈርድ ሌሎች በአጻፋው በፈረድንባችው ፍርድ እንዲፈርዱብን ከማድረጉም ባሻገር መንፈሳዊ ህይወትችንን የሚጎዳው መሆኑ መታሰብ ይኖርበታል። የእግዚአሔር ቃል እንደሚያስተምረን በሌላው ሰው ላይ ከመፍረዳችን አስቀድመን እራሳችንን ብንመለከት ወይንም ብናይ በቂ የሆነ ልናስተካክለው እና ልንሻሻልበት የሚገባን ክፍተት ወይንም ጉድለት ይኖረናል። ስለዚህ እንደ ጠቢብ ዓይኖች እራሳችንን የምንመለከትበት እና ዓይኖቻችንም አጥርተው በትክክል እንዲያዩ ጌታ እንዲረዳን መጸለይ ያስፈልገናል።

# ማቴ 7፡1-29
# ክፍል ፪
# ጥናት ስድስት
# የንባብ ክፍል ማቴ 7፡6-29

**የጥናቱ ዓላማ፥**

ጌታ ኢየሱስ በህይወት ዙሪያ ያስትማራቸውን እውነታዎችን  እና የአማኝ ሥነ ምግባሮችን በማየት በሥራ ላይ እንድናውል ለማገዝ ነው።

***መግቢያ፥***

ጌታ ኢየሱስ ከደቀመዛሙርት ጋር በነበረበት ጊዜ በብዙ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ትምህርት እና ማብራሪያ ይሰጣቸው እንደነበር ግልጽ ነው። በዚህ ምዕራፍ ከቁጥር ስድስት እስከ ቁጥር ሃያ ዘጠኝ ድርስ ጌታ ስለ ተለያዩ ጉዳዮች  ለደቀ መዛሙርት እና ይሰሙት ለነበሩት ህዝብ ያስተማረውን በመመልከት፥ ለመንፈሳዊ ህይወታችንም ሆነ በዚህ በምድር ላይ በምንኖርበት ዘመን በተግባር ላይ ብናውላቸው ብዙ ፍሬ የምናፈራበት እና ሌሎችንም የምንጠቅምበት እንደሚሆን ምንም ጥያቄ አይኖረውም።

**ማቴ 7፡** 6. ለተቀደሰው ለእግዚአብሔር ነገር ወይንም ለከበረው መንፈሳዊ ጉዳይ በህይወታቸው ስፍራ ስለማይሰጡ ሰዎች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ሲሆን ፥ መንፈሳዊ ትምህርት የሰሚዎቹን የመስማት እና የመቀበላቸውን አቅም የሚጠይቅ ጉዳይ ስለሆነ በዚህ ዙሪያ ጥንቃቄ የሚያስፈልግ መሆኑንም ሊሰመርበት ይገባል። በዚህ ስፍራ የመቀደስ ፍላጎት የሌላቸው ሰዎችም የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

**ማቴ 7፡7-11**. ሀ. በዚህ ክፍል ጌታ ስለ ጸሎት መሰረታዊ እውነታን አስተምሮል፤ 'ለምኑ' 'ፈልጉ' 'አንኩኩ' የሚሉት ትእዛዝን የሚያመልክቱ ያለማቋረጥ ሊፈጽሙት የሚገባ መሆኑን ነው።

ለ. እግዚአብሔርም ለምንጸልየው ጸሎት ሁሉ መልስን የሚሰጥ መሆኑን ያመለክታል፤ ይሁን እንጂ ታዲያ የለመነውን ሁሉ እንቀበላለን ማለት ሳይሆን ለጸለይነው ሁሉ መልስ መኖሩ አስረግጦ የሚያስረዳን ክፍል ነው።

**ማቴ 7፡12**. 'ኦሪትም ነቢያትም በዚህ ይጠቃለላሉን' በማለት ጌታ በብሉይ ኪዳን ህግ በኩልም ሆነ በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠው ሰው ከአምላኩ እና ከባልጀራው ጋር ሊኖረው ስለሚገባ የፍቅር ህብረት እና ትስስር የሚያመለከት ነው።

**ማቴ 7፡13-14** ጌታ 'በጠባቡ' እና 'በሰፊው' በር ምሳሌ ሊያስተምር የፈለገው ሰው የህይወትን እና የጽድቅን መንግድ ሊመርጥ እንሚገባ ለማሳየት ሲሆን፤ የሰዎች ውሳኔ በምርጫው ከክብደት እና ቅለት ላይ መመስርት እንደሌለበት  ይልቁንም ምርጫቸው በሚያስከትለው ውጤት ወይንም ከፍጻሜው አንጻር መሆን እንደሚገባው ያሳያል።

**ማቴ 7፡15-23** ጌታ በመጨረሻው ዘመን ስለሚነሱ ሐሰተኛ ነቢያት ያስጠነቀቀበት ክፍል ነው ሲሆን፤ በውስጣቸው ክፉት እና የጨለማን ስራ ይዘው ነገር ግን በውጫዊ ገጽታቸው የጽድቅ አገልጋይ መስለው በመታየት ሊያስቱ የሚችሉ ሐሰተኞች ነቢያት እንደሚነሱ ያሳያል፥ እንደዚህም ያሉት ተንኮለኛ ሰራተኞች የሚታወቁበት አንዱ በፍሬቸው እንደሆነ በመገንዘብ በሚያመጡት ትንቢት ወይን ትምህርት ብቻ አይተን መወሰድ እንደሌለብን ያመለክታል።

**ማቴ 7፡24-27** ጌታ በዓለት ላይ ወይንም በአሸዋ ላይ የተሰራ ቤትን በምሳሌ ያስተማረበት ክፍል ነው፤ በዚህ ምሳሌም ሰው የጌታን ትምህርት ሰምቶ በተግባር ላይ በማዋል ከሚመጣበት የትምህርት ማዕበል ወይንም ወጀብ ማምለጥ የሚችል እንደሆነ በማሳየት፤ በአንጻሩ ግን የጌታ ትምህርት እና ቃል ሰምቶ በማይታዘዘው ወይንም በማይፈጽመው ግን በቀላሉ በሚነሱ

የትምህርት ነፋሳት ሊገፋና ከእውነተኛው ትምህርት ሊሰናከል እንደሚችል ያመለክታል።

**ማቴ 7፡28-29** የጌታ ኢየሱስ በዚያ ዘመን ከነበሩ የአይሁድ ሃይማኖት አስተማሪዎች የተለየ የሚያደርገው አንዱ እና ዋናው በስልጣን እኔ ግን እላችሃለሁ በማለት በስልጣን ያስተምራቸው ስለነበር ሲሆን፤ የሚሰሙትም ህዝብ በትምህርቱ ብቻ ሳይሆን በሚያስተምርበት ስልጣን ጭምር ይገረሙ ነበር።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1.በማቴ 7፡6. ጌታ ኢየሱስ የሚያስጠነቅቀው እውነት ምንድነው?

2. በማቴ 7፡7-11 ጌታ ኢየሱስ ስለ ጸሎት ያስተማራቸውን እውነቶች በዝርዝር ተነጋገሩበት፡

3. በዚህ መሰረት የምንለምነውን ሁሉ እንቀበላለን ማለት ነው? ቁ.11 ስለ ጸሎታችን መልስ ምን ያስረዳናል?

4. በማቴ 7፡12 መሠረት ህግም ነቢያትም ይህ ነውና የሚለውን ትምህርት እንዴት ትረዱታላችሁ? ተወያዩ

5. ማቴ 7፡ 13-14 በጠበበው እና በፊው ደጅ ምሳሌ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? የተጓዦቹ ቁጥር ማነስና መብዛት ከምን የተነሳ?

6. ማቴ 7፡15-23 ጌታ የሰጠው ማስጠንቀቂያ ዓይነት ችግር በዚህ ዘመን አለ? እንግዲያውስ ማድረግ ያለብን ምድነው?

7. ማቴ 7፡.24-27 ስለ ቤተሰሪው የተሰጠውን ምሳሌ ተወያዩበት። ለእኛ ምን ይጠቅማል።

8. ማቴ 7፡ 28-29 የጌታ ኢየሱስ አሰተምህሮት ከጻፎቹ የሚለይበት እንዴት እንደነበር የተረዳችሁትን አካፍሉ?

9. ከዛሬ ጥናት ምን ተረዳን?

***መደምደሚያ፡-***

ጌታ ኢየሱስ በምድር ለሶስት ዓመት ተኩል ከደቀመዛሙርቱ ጋር በመሆን አብዛኛውን ጊዜውን ያሳለፈው ደቀመዛሙርቱንና ህዝቡን በማስተማር ነበር። በዚህም ጌታ ለትምህርት የሰጠውን ከፍ ያለ ስፍራ ከመገንዘብ ባሻገር፥ ጌታ በአብዛኛው ትኩረት በመስጠት ያስተማረባቸው ርዕሶች ስንመለከት ስለ እግዚአብሔር መንግስት፣ ስለ ጸሎት፣ ስለ መጨረሻው ዘመን፣ ስለ ሐሰተኛ ነቢያት፣ ስለ እውነተኛ መንፈሳዊ ህይወት ሆኖ እናያለን። ስለዚህ በዛሬው ጥናት የተመለከትናቸው ሃሳቦች ጌታ በምድረ በነበረበት ያተኮረባቸው ርዕሶች ስለሆኑ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ በህይወታችን ላይ ሊያመጡ የሚችሉት ተጽዖኖ በቀላሉ መታየት ስለሌለበት፥ በዚህ ክፍል በተመለከትናቸው የጌታ ትምህርቶች የእራሳችንን መንፈሳዊ ህይወት የዘመናችንን ሁኔታን ልንመረምርበት እና ልንመዝንበት የምንችል መሆኑን ልናስምርበት ያስፈልገናል።

## ጥናት ሰባት

የንባብ ክፍል: - ማቴ 10:1-15

## የመከሩ ጌታ አገልጋዮችና የተሰጣቸው መመሪያ

**ዓላማ:-**

የወንጌል ሥርጭት ከመከሩ ጌታ ከኢየሱስ የተሰጠ ትዕዛዝ መሆኑን ተገንዝበን ድርሻችንን እንድንወጣ ለማሳሰብ

**መግቢያ:-**

ይህ ክፍል በማቴዎስ ወንጌል ሁለተኛው የትምህርት ክፍል ነው። በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 9:37-38 ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በዛ ያሉ የመከሩ ሰራተኞች እንደሚያስፈልጉና ለዚህም ደግሞ መጸለይ እንዳለባቸው ሲያሳስባቸው እንመለከታለን፥፥ይህ ክፍል ለማቴዎሰ ወንጌል ምዕራፍ 10 እንደ መሸጋገሪያ ሆኖ እናየዋለን። በዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያው ክፍል ጥናት አስራ አምስት ቁጥሮችን እናያለን

**የምዕራፉ አጭር ማብራሪያ**

በማቴዎስ 10:1-4 ውስጥ አስራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ለመጀመሪያ ጊዜ በስም ተጠቅሰውና የአገልግሎት ሥልጣን ተሰጥቷቸው የምንመለከት ሲሆን ፤ በዚሁ ክፍል ከቁጥር 5-15 ደግሞ የአገልግሎታቸውን ይዘትና የተሰጣቸውን መመሪያ እናያለን።

በማቴዎስ 10:5-42 ያለው የወንጌል አገልግሎት ባላደራነት የተወሰደው ከብዙ የተለያዩ ሥፍራዎች እንደሆነ በሥነ መለኮት ሰዎች ዘንድ የታመነ ሲሆን ለተልዕኮ ትምህርቱ ተስማሚነት ሲባል ባንድ ላይ ተቀነባብሯል። ማር 6:8-11 ፤ ሉቃ 9:1-5 ፤ 10:1-12 ይመሳሰላሉ።

በዚህ ክፍል በስም የተዘረዘሩት አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት (ተማሪዎች) ሐዋርያት በመባልም ተሰይመዋል። ይህም ቃል ኢየሱስ ከሥልጣን ጋር የላካቸው መለዕክተኞች መሆናቸውን ያሳያል። ሁለት ሁለት ሆነውም ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተመድበዋል።

**የሐዋርያቱ ሥም:-**

1. ጴጥሮስ (ስምዖን)ና እንድርያስ
2. ያዕቆብ (የዘብዲዎስ ልጅ)ና ዮሐንስ (የዘብዲዎስ ልጅ)
3. ፊልጶስና በርተሎሜዎስ
4. ቶማስና ማቴዎስ (ቀራጩ)
5. ያዕቆብ (የእልፍዮስ ልጅ)ና ታዴዎስ (ልብድዮስ)
6. ስምዖን (ቀነናዊው/ቀናተኛው)ና ይሁዳ (የአስቆረቱ)

ስምዖን መጀመሪያ ከተጠሩት ሲሆን በቤተሰብ የዘር ግንድ አሰያዬም ጴጥሮስ መባሉ በማቴ 16:13-20 ተብራርቷል። "… የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ … አንተ ጴጥሮስ ነህ …"

ማቴዎስ ቀራጩ ተብሎ መሰዬሙ ከምን ዓይነት ሕይወት እንደመጣ ለማሳዬት ይመስላል(ማቴ:- 9:9-13)።

ስምዖ ቀናተኛው የመባሉ ምክንያት አንድም ከብሉይ ኪዳኑ ሕግ አኳያ ይሆናል ተብሎ ሲገመት በሌላ በኩል ደግሞ አገር ወዳጅ የቀናተኞች ማሕበር የሚባል የአይሁዳዊያን ቡድን ስለነበር የስሙ ትርጉም ከዚያ የመጣ ሊሆን ይችላል ተብሎ ይገመታል።

የአስቆረቱ ይሁዳ የሚለው አባባል ደግሞ ኬሪዮት ማለትም በአማርኛው ትርጉም አስቆረቶስ ከሚባል ቦታ የመጣ ሊሆን እንደሚችል ይታሰባል።

ተልዕኳቸው በቀደምትነት በአስራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ላይ ያተኮረ ለመሆኑ:- "… ወደ አሕዛብ አት ሂዱ፤ ወደ ሳምራውያንም ከተማ አትግቡ ይልቁን የእስራኤል ቤት ወደ ሆኑት ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ …" (ማቴ 10:5-6) ከሚለው የጌታ ኢየሱስ ትዕዛዝ መገንዘብ ይቻላል። ከትንሳኤ በኋላ ግን ከ ኢየሩሳሌም ጀምሮ እስከ ምድር ዳርቻ መሰበክ እንዳለበት በሐዋርያት ስራ ከተሰጠው ትዕዛዝ (የሐዋ:- 1:8) መገንዘብ ይቻላል።

የወንጌል አገልግሎቱ ይዘት መዳንን አስቀድሞ ፈውስን በማስከተል ከጠላት እስራት መፈታትንም ይጨምራል (10: 7-9)። ይህም ወንጌል ሁለንተናዊ አገልግሎት መሆኑን ያሳዬናል። አስራ ሁለቱን ጠርቶ ሥልጣን የሰጣቸው ራሱ ነው። የታምራቱ መንጭ እርሱ እንደመሆኑ በእነርሱም አገልግሎት

ሊከናወን ያለው ተዓምር ሁሉ ለእርሱ ክበር የሚያመጣ መሆን አለበት። ከሁሉ የሚበልጠው አገልግሎት ግን ሰዎችን ወደ ጌታ ማምጣቱ ነው።

ከቁ 9-10 ያለው ክፍል የወንጌል ሰራተኛ በእምነት መኖርና ካስፈላጊው በላይ ንብረት ይዞ ለመጓዝ መፈተን እንደሌለበት የሚያመለክት ይመስላል። በተጨማሪም ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች ስንቅና ትጥቃቸውን የእግዚአብሔር ከሆኑ ሰዎች ስለሚያገኙ መጨነቅ እንደሌለባቸው ያመለክታል። ማለትም አገልጋይ (የወንጌል ሰባኪ) ስለ ምግቡና ልብሱ ሳያስብና ሳይጨነቅ ወንጌልን ማሰራጨት ሲኖርበት የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች በዚህ ሊረዱት እንደሚገባ የሚያስረዳ ነው። እግዚአብሔር የሚያስፍልጋቸውን ነገር እንደሚያዝላቸው ይገነዘቡ ዘንድ ገንዘብም ሆነ ትርፍ ልብስ እንዳይዙ ተባለ። በጉዟቸው ምንም እንዳልጎደለባቸው ራሳቸው በሉቃስ 22: 35-36 መስክረዋል። ለቋሚ አገልግሎት የምንሄድ ከሆነ ግን ያለንን ሁሉ ይዘን መሄድ እንዳለብን በ 1ቆር 9:7-14 ተገልጿል።

ሐዋርያት የሰላም ወንጌል አብሳሪዎች እንደመሆናችው መጠን በሚገቡበት ቤት ሁሉ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ሰላምታ ማቅረብእንደሚኖርባቸው ቀጣዩ ክፍል (ቁጥር 11-13) ይጠቁማል። ሆኖም ቁ:- 11 "... የሚገባው ማን እንደሆነ በጥንቃቄ መርምሩ ..." የሚለው አባባል ማግኘት ከቻልን በወንጌሉ ስራ ሊተባበሩን የሚችሉት ላይ እንድናተኩር የሚያስገነዝበን ነው። እንደ የሰላም ሰዎች ወደ ማንኛውም ቤት ስንገባ ሰላምታ መስጠትና ስንወጣም ቤቱን ባርከን መሄድ አስፈላጊና የሚጠበቅብን ነው።

ከቁ 14-15 ያለው ክፍል የእግዚአብሔርን መልእክት አልቀበልም ላሉት እንደከባድ ማስጠንቀቂያ ሲሆን ሐዋርያ ጳውሎስ በተመሳሳይ ሁኔታ በሐዋርያት ስራ 18:6 ላይ ልብሱን እንዳራገፈው ማለት ነው። ዛሬም የመከሩ ጌታ የሆነው እግዚአብሔር መልዕክተኞቹን በተመሳሳይ መንገድ ይመራቸዋል።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በመግቢያው መሰረት ከማቴዎስ ምዕራፍ 9 ቁጥር 37-38 ምን እንረዳለን?
2. በማቴዎስ 10:1ና 10:8 መሰረት ለደቀ መዛሙርቱ የተሰጠው ሥልጣን በዝርዝር ያብራሩ?
3. ከአስራ ሁለቱ ሐዋርያት መሃል የምታስታውስቱን ስም ይጥቀሱ?
4. በማቴ 10፡5-15 ለደቀ መዛሙርቱ የተሰጣቸውን ትዕዛዝ በዝርዝር ያብራሩ
5. በማቴዎስ 10:5 መሰረት፡- "በአሕዛብ መንገድ አትሂዱ ፤ወደ ሳምራውያንም ከተማ አትግቡ" የሚለውን እንዴት ትረዳዋለህ?
6. በማቴ10:8-10 ያለውን የስንቅና ትጥቅ ማግኛ መመሪያ ከሉቃስ 22:35-36 ጋር በማነጻጸር ያብራሩ
7. በሐዋርያት ዘመን ወንጌል በመጀመሪያ ቀጥሎ  በመጨረሻም የተነገረው ለማን ነበር ? (ማቴ። 10:6፣ ሮሜ 1:16)
8. የወንጌል ስብከት በዋጋ ሳይሆን በነጻ የሚሰጥ ቢሆንም ፥ለሰራተኛ ምግቡ ይገባዋላና (ማቴ:-10:10) ሲል ግን ምን ማለቱ ነው፤
9. በዚህ ጥቅስ መሰረት ጓዝ መያዝ/ማብዛት የተከለከለበት ምክንያት ለምንድን ነው ይላሉ፤ (ማቴ:- 10:9-10፣ ማር:- 6:8-9)
10. በማቴ 10:12-14 መሰረት የሚከተሉትን ምን ማለት እንደሆነ አብራሩ?
    - ሰላምታ ስጡ
    - የእግራችሁን ትቢያ አራግፉ

11. ቁ. 15 ሰዶምና ጎመራ ለርኩሰት የታጠቁና የእግዚአብሔርንም መልዕክተኞች ላለመስማት የቆሙ ምሳሌዎች ነበሩ። ለመሆኑ ኃጢአታቸው ምን ነበር? (ዘፍ:- 19:4-9፣ ሕዝ:- 16: 48-50)
12. ቁ. 15 "በፍርድ ቀን" የተባለው የትኛው ቀን ነው፧

***መደምደሚያ***

*እግዚአብሔር ለመንግሥቱ ሥራ ሠራተኞችን ጥሪ ያደርጋል። ለዚህም ደግሞ ትክክለኛ ሰዎች እንዲገኙ ቤተ ክርስቲያን መጸለይ አለባት። የመከሩ ጌታ አብሮን የሚሠራ አምላክ ስለሆነ ራሳችንን መስጠት እንደ ታላቅ እድልም መቁጠር አለብን።*

## ጥናት ስምንት
## የወንጌል መልዕክተኛና ለመከራ የሚጠበቅበት ምላሽ
## የንባብ ክፍል:- ማቴ 10:16-42

**ዓላማ:-**

በወንጌል ስብከት ምክንያት የሚደርስብንን መከራ እንዴት መወጣት እንዳለብን ለማስገንዘብ።

***መግቢያ:-***

የመንግስቱን ወንጌል ስናሰራጭ ለሚያጋጥሙን ተግዳሮቶች ከጅምሩ ምላሻችን ምን ሊሆን እንደሚገባው ማቴ:- 10:16 እንደ እባብ ልባሞች፤ እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ በማለት ይመክረናል። ስለሆነም ባንድ በኩል ራሳችንን ከጉዳት ለመጠበቅ እንደ እባብ ብልህ መሆን ሲኖርብን በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር ሊያደርግልን ባለው ጥበቃና እንክብካቤ ተስፋ በማድረግ በየዋህነት ልንታዘዘው እንደሚገባ ይጠቁመናል። በጥቅሉ ራሳችንን በመግዛት በአግባብ እንድንኖር ጥበብ ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔርን መጠየቅ እንዳለበን የሚያስገነዝበን ነው።

## የክፍሉ ማብራሪያ

ዘርዘር ባለ መልኩ ለሚደርስብን ተግዳሮት ሁሉ ምላሻችን ምን መሆን እንደሚኖርበት እንደሚከተለው እናያለን።

| ቁጥር | ተግዳሮት | ምላሽ |
|---|---|---|
| 16 | በተኩላዎች መካከል መላክ | ልባምና የዋህ መሆን |
| 17 | በሸንጎና በምኩራብ ፊት | ከሰዎች መጠበቅ |
| 18 | ወደ ገዥዎችና ነገስታት መወሰድ | ለእስራኤልና ለአህዛብ ምስክር መሆን |
| 19 | ታልፎ መሰጠት | ስለምንሰጠው መልስ አለመጨነቅ (ቁ. 20) |

| | | |
|---|---|---|
| 21 | ቤተሰብ ሲነሳብን | እስከመጨረሻ መጽናት |
| 22 | ስለ ስሙ ስንጠላ | እስከመጨረሻ መጽናት |
| 23 | ስንሰደድ | መሸሽ |
| 24-25 | ስንሰደብ | አለመፍራት (ቁ 26) |
| 28 | ስጋችንን መግደል ሲያስቡ | አለመፍራት (ጌታን ብቻ መፍራት) |
| 34-36 | ቤተሰብ ጠላት ሲሆን | ከቤተሰብ በላይ ጌታን መውደድ (ቁ 37-39) |

በዚህ ክፍል መጨረሻ ላይ (ማቴ 10:40-42) እንደምናስተውለው ከተገዳዳሪዎቹ በአንጻራዊነት መከራን ሳይፈሩ ከእኛ ጋር የሚወግኑ እንዳሉም ጭምር ነው።

ቁጥ 16 ስንላክ እንደ በግ ተንኮል የሌለብን ፀባዬ መልካም ሆነን እንደ ርግብም የዋህና ነገር ግን እንደ እባብ ደግሞ ብልህና ጥበበኞች መሆን እንዳለብን የሚጠቁም ነው። መቼም ብልህነት ሳይኖር የዋህነት ሞኝነት ነው። ለዚህም ነው እንደ እባብ ብልጥ እንደ ርግብ የዋህ መሆን ያለብን።

ማቴ 10፡16-33 ያለው ክፍል በጥቅሉ አደገኛ የሆነውን ነገር እንድንመለከትና ዝግጁ ሆነን ምላሽ መስጠት እንድንችል የሚያስገነዝብ ነው። ጌታ ኢየሱስ በግልጥ ሐዋርያቱ ስለ ወንጌል ስደት እንደሚያጋጥማቸውና የሚከላከልላቸውም ሰራዊት እንደሌለ "... እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል..." በሚለው አባባሉ ገልጾታል። የምንሰደደውም ስለ ጌታ እንደሆነ ሲያስገነዝበን ቁጥ:- 18 "ስለ እኔ..." ይላል።

በቁጥር 19 መሰረት በትክክል የእግዚአብሔር አገልጋዮች ከሆንን የመንፈስ ቅዱስ አምባሳደሮች ስለሆንን በውክልና የምንናገር እንጅ የርሳችንን ሃሳብ ስለማንናገር መጨነቅ የለብንም። ጌታ መንፈስ ቅዱስ ራሱ በጊዜው የሚያስፈልገውን ምላሽ በልባችንና በአፋችን ያስቀምጣል።

እነዚህ በተኩላነት የተመሰሉ ነገስታት፤የሐይማኖት መሪዎች፤ ከዘመዶቻችንም ከፉዎች ሰዎች ዘወትር ስለሚገዳደሩንና ስለሚያሳድዱን

በተከሰስንና ወደ ዳኛ በቀረብን ጊዜ እንደ እንግዳ ነገር ሊሆንብን አይገባም። ባጠቃላይ እግዚአብሔርን ከማይወዱትም ሆነ ከማይረዱት ለእኛ መልካም ነገርን መጠበቅ አይኖርብንም። ከቅርብ ዘመዶቻችን ጀምሮ እስከ የማያውቁን ሰዎች ድረስ ስለ ወንጌል ጠላትን ልናፈራ እንችላለን። በወንጌል ምክንያት የቀርብ ዘመዶቻችን ስንኳ ሳይቀር ሊያሳድ ዱንና አሳልፈው ሊሰጡን እንደሚችሉ በቁጥር 21 ተብራርቷል። ቀአጥሎም በቁጥ 22 በሁሉም ስለ ስሙ የተጠላን እንደምንሆን በግልጽ ተነግሮናልና ነገሩን በጸጋ መቀበልም ሆነ እስከ መጨረሻ መጽናት ይኖርብናል።

ወንጌል የሰላም መልዕክት ስለሆነ በአንዲቱ ከተማ ሲቃወሙን ወደ ሌላይቱ በመሄድ እንመሰክራለን እንጂ በጉልበት ለማሳመን እየጣርን ሰዎች ጋር መጣላትም ሆነ አላስፈላጊ ስደት በራሳችን ላይ ማምጣት የለብንም (ቁጥር 23)። “... የእስራኤልን ከተማዎች አትዘልቁም...” የሚለው አባባል በተሰጠን የምህረት ጊዜ በተለያየ መልኩና ጊዜ ከሚመጣው ፍርድ ሰዎች ያመልጡ ዘንድ እንዴት በፍጥነት መመስከር እንዳለብን የሚያስረዳ ሃቅ ነው።

**ማቴ 10፡24-25** ላይ “ደቀ መዝሙር ከመምህሩ አይበልጥም “የሚለው አባባል መመህሩን በተቀበሉበት አቀባበል ይቀበሏችኋል ማለት ነው። ማለትም እሱን አሳደውት ከሆነ እናንተንም ያሳዷችኋል መሆኑ ነው። እርሱን ቤል ዜቡል ያለበት ብለው ከሆነ እናንተንም ልዩ ልዩ ስድብ ቢያዘንቡባችሁ አትደነቁ ለማለት ነው። የተለያዬ ስድብ ሊያወርዱብን ይችላሉ ግን ደስ የሚለው ነገር መጥፎ ሰው  አድርገው ሊለውጡን አይችሉም። መስቀሉን ከጀርባችን ላይ ለማውረድ ከመጣር ይልቅ ለንጉሳችን ክብር ስንል በትዕግስት  መሸከም እንዳለብን የሚያመላክት ነው።

በዚህ ሁሉ ስደት መካከል ሐዋርያቱ ያለምንም ፍርሃት የወንጌል ምስክርነቱን መቀጠል እንደነበረባቸው ቁጥ 26-31 ያልው ሃሳብ ያብራራል። በተጨማሪም ቁጥሩ ምንም እንኳን ለጊዜው እውነቱን ሊደባብቁትና ሊሸፍኑት ቢሞከሩም እውነቱ በቅርቡም ይሁን ዘግይቶ መገለጡ አይቀሬ

ነውና ማስፈራራታቸውን አትፍሩ የሚል ሃሳብን ያዘለ ነው። በአንጻሩም በዚሁ ክፍል መፍራት ያለብን ጌታን ብቻ መሆን እንዳለብት ተተንትኗል።

**ማቴ 10፡26-27፡-** በግልና በሚስጥራዊ የጽሞና ቦታችንና ጊዜያችን ከጌታ ጠብቀን በማግኘት በይፋ መስማትና መዳን ለሚገባቸው መናገር እንደሚያስፈልግ የሚጠቁም ክፍል ነው።

ይህ ስብከት (ቁጥር፡- 29-31) ፍርሃትን በማስወገድ ላይ የተሰበከ መሆኑ ግልጽ ነው። ድንቢጦች እምብዛም እርባና የሌላቸው የወፍ ዝርያዎች ቢሆኑም ግዚአብሔር ለእነርሱ ከገደደውና በእነርሱ ሕይወት ያለ እርሱ ፈቃድ የሚሆን ነገር ከሌለ ለሰው ልጆችማ እጅግ በጣም እንደሚገድው ግልጽ ነው። ለዚህም ነው የራሳቸው ጸጉር እንኳን እንደሚታወቅ የሚናገረው። በዚህም መሰረት ያለ እምላካችን ፈቃድ ምንም ዓይነት በደል ሊደርስብን ስለማይችል በምንሰማው ዛቻ ሁሉ መደናገጥ እንደሌለብን ያስገነዝበናል።

**ማቴ 10፡32-33** የሚያስረዳን በሰዎች ሁሉ ፊት ስለ ጌታ አዳኝነት እንደንመሰክር ነው። ይህንን ባናደርግ ጌታም አንድ ቀን በአብ ፊት እንደሚያፍርብን ተገልጿል።

ጌታ ኢየሱስ የሰላም አምላክ ቢሆንም እርሱን በመቀበላችን መጀመሪያ የሚያጋጥመን ማለትም ስለ ወንጌል የሚደርስብን የመጀመሪያው ነገር ሰይፍ ነው። እውነት ውሸትን ያበሳጫል፤ ቅድስና እርኩሰትን ያጋልጣል፤ጽድቅ ኃጢአትን ይኮንናል ስለሆነም ሰዎች ይጣሉናል። (ቁጥር፡- 34-36)

**ማቴ 10፡37-39** በሁሉም አቅጣጫና ሁኔታ ማስቀደም ያለብን ጌታን ስለመሆኑ አበክሮ የሚናገር ክፍል ነው። ክርስቶስን ሊወዳደርብን የሚገባው ነገር መኖር እንደሌለበት በግልጽ የሚያሳየን ክፍል ነው። መስቀሉን ተሸክመን ለሕይወታችን ሳንሰስት ለጌታ ብንኖር ዋጋችን እጅግ ትልቅ እንደሆነ በክፍሉ እንገነዘባለን።

**ማቴ 10፡40-42** ያለው ሀስብ የክርስቶስ የሆኑትን የሚቀበሉና ነቢይን በነቢይነቱ የሚቀበል አንድ ቀን ዋጋ እንደሚያገኝ በግልጽ የሚያሳይ ነው

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በመግቢያው መሰረት እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል ስንላክ እንደ እባብና እንደ እርግብ መሆን ያለብን ለምንድን ነው? (ቁ.16 ይመልከቱ)።
2. ቁ.17-19, 21 ወንጌልን ስናሰራጭ ሰዎች ሊያደርሱብን የሚችሉትን መከራ በዝርዝር ተነጋገሩበት
3. በቁ. 22 "እስከ መጨረሻ የሚጸና" ሲል ምን ማለት ነው?
4. ቁ. 23 ....ወደ ሌላይቱ ሽሹ፤ እውነት እላችኋለሁና፥ የሰው ልጅ እስኪመጣ ድረስ የእስራኤልን ከተማዎች አትዘልቁም። ይህን ጥቅስ በዝርዝር ተነጋገሩበት::
5. ቁ. 18 " እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል..." "ስለ እኔ"..." የሚሉትን አባባሎች ተነጋገሩባቸው።
6. ቁ.19-20 መንፈስ ቅዱስ ራሱ በጊዜው የሚያስፈልገውን ምላሽ በልባችንና በአፉችን ያስቀምጣል ሲል ምን ማለቱ ነው?
7. በ**ማቴ 10:** 24-25 የተገለጸውን ሃሳብ እንዴት ትረዳዋልህ?
8. በ**ማቴ 10:** 27 "በጨለማ የምነግራችሁን በብርሃን ተናገሩ፤ በጆሮም የምትሰሙትን በሰገነት ላይ ስበኩ" የሚለው ሃሳብ ምንድን ነው?
9. በ**ማቴ 10:** 29-31 ሁለት ድንቢጦች ከእኛ ጋር የተመሳሰሉበትን አባባል እንዴት ትረዳዋለህ?
10. ከቁ. 34-36 የሰላሙ አለቃ ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ማለቱ ለምንድን ነው?

11. ማቴ 10፥ 38-39 መስቀል መሸከም ማለት ምን ማለት ነው ?

12. ማቴዎስ 10:40-42 ያለውን ክፍል በዝርዝር ተነጋገሩበት።

## መደምደሚያ

ወንጌል በዚህ ዓለም ላይ ያለውን የጠላታችንን የዲያቢሎስን ምሽግ ሰባሪ መሳሪያ ስለሆነ ምሽጉ ሲሰበርበት እጅግ ይበሳጫል። ስለዚህ ባይችልም እንኳን ይህንን ወንጌል ለማስቆም ያለውን ሁሉ ኃይል ይጠቀማል። ሰዎችም ከፉውን የሥጋቸውን ፍላጎቶችን ለመፈጸም ሲጥሩ በሌሎች ላይ መከራን ሊያመጡ ይችላሉ። በዚህም ምክንያት ወንጌልን ስንሰብክ የተለያዩ መከራዎች ቢገጥሙን እንኳን ጌታ በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ብሎ ስለ ተናገረ ተስፋ ሳንቆርጥ ይህንን የምስራች ማወጅ አለብን። ታላቅ ተስፋ እንደተሰጠን ልንረሳ አያስፈልልግም። የእርሱ አብርሆት ከእኛ ጋር እንደሆነ መርሳት አያስፈልገንም። ይህ ታላቅ ተስፋ ነው።

## ጥናት ዘጠኝ
## የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 13
## የእግዚአብሔር መንግስት ትምህርቶች በምሳሌ

### አጠቃላይ መግቢያ

ምሳሌ ማለት ምን ማለት ነው? ምሳሌ ማለት ለአንድ ትምህርት ወይም መግባቢያ ዓላማ በአጠገብ ወይም በጎን ማስቀመጥ ማለት ነው። ዋናው ዓላማውም ትምህርትን በማመሳሰል ለማስተማር ይሆናል። ይህ ክፍል ከአምስቱ ትምህርቶች ሶስተኛው ክፍል ነው። በምሳሌ ማስተማር ሰሚዎች በቀላሉ ትምህርትን መያዝ እንዲችሉ በብዙ ይረዳል። በብዙ ባህሎች በምሳሌ ማሳወቅና ማስተማር የታወቀ ነገር ነው። ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግስት  በብዙ ምሳሌ ያስተምርና ይገልጥ ነበር። ምሳሌ የሚታወቀውን ነገር በመጠቀም ስለማይታወቀው ነገር ሚስጥር ወይም ትምህርት የማስተማሪያ ዘዴ ነው። በወንጌላት ወደ 46 የሚሆኑ ምሳሌዎች ተጠቅሰው ይገኛል። ምሳሌን በትክክል ለመተርጎም ሙሉውን ክፍል ማንበብ አለብን። በማቴዎስ ወንጌል 13 ስምንት የሚሆኑ ምሳሌዎች ከትርጉማቸው ጋር ተጠቀሰው ይገኛሉ። የአይሁድ ጥላቻ በጌታ ላይ እየጨመረ እንደመጣ ከምዕራፍ 11-12 ያሳያል። ስለዚህ በማቴ 13 ላይ የተቀበሉት ማለትም በእርሱ ላይ ጥላቻ የሌላቸው ደቀ መዛሙርት ሚስጢሩ ስለሚገባቸው የእግዚአብሔርን መንግሥት ትምህርት ጌታ በምሳሌ ማስተማር ጀመረ።

# ክፍል ፩
# የዘሪ ምሳሌ (የማቴ 13፡1-23)

## የክፍሉ መግቢያ

የዘሪ ምሳሌ ለደቀ መዛሙርት ብቻ የተነገረ ሳይሆን በጊዜው ለነበሩት ህዝብ ሁሉ የተነገረ ትምህርት ነው። ማብራሪያው ግን የተነገረው ለደቀ መዛሙርት ብቻ ነው። የዚህ ምሳሌ ዋና መልዕክቱ ስለ ሰሚዎች የልብ ምላሽ ነው። ልባቸው የተቀበለ ጥሩ ምላሽ ሲሰጡ ሌሎች ደግሞ ፍሬ አልባ ምላሽ የሚሰጡ ናቸው። ልባቸው በቅንነት ለመስማት የተዘጋጀ ስላልሆነ አይገባቸውም። በማቴ 13፡1-23 ባለው ክፍል ከ1-9 የምሳሌው መግቢያ፣ ከ10-17 የምሳሌ ዓላማ ሲሆን ከ18-23 ያለው ክፍል ደግሞ የምሳሌው ትርጉም ቀርቦ ይገኛል።

ዘሮቹ የወደቁት አራት ዓይነት መሬት ላይ ነው። እንደዚሁም ፍሬያቸውም አራት ዓይነት ነው። መሬቱ እንደተቀበለው ፍሬ አላፈራም። የመሬቱ ዝግጅት እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። በዛሬው የጥናታችን የመጀመሪያውን ምሳሌ እንመለከታለን።

### የዘሪ ምሳሌ (የማቴ 13፡1-23

፩. የመጀመሪያው ዘር  “በመንገድ ዳር ወደቀ፥ ወፎችም መጥተው በሉት”። ተዛማጅነቱ ወይም ትርጉሙ በቁ.19 እንዲህ ይላል “የመንግሥትን ቃል ሰምቶ በማያስተውል ሁሉ፥ ክፉው ይመጣል፥ በልቡ የተዘራውንም ይነጥቃል፤ በመንገድ ዳር የተዘራው ይህ ነው”። የጌታን ቃል የሚሰማ ሁሉ በማስተወል ካልሰማ ወፎች/ክፉው የተለያዩ ምክንያቶችን እያመጣ ቃሉን ያጠፋ፤ያስረሳል ደግሞም ይነጥቃል። ይህ ባላመኑ ሰዎች ብቻ ሳይሆን በአማኞችም መካከል የሚሆን ነው። ብዙዎቻችን እንደምናውቀው ክፉ አጋንንት ነው። አጋንንት በውስጥም ይሁን በውጪ ሆኖ አማኞች በመዋጋት የሰሙትን ይለቅማል።

፪. ሁለተኛው ዘር **"ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫ** ላይ ወደቀ፤ ጥልቅ መሬትም ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፥ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ፥ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ" ተዛማጅነቱ ወይም ትርጉሙ በቁ.20-21 እንዲህ ይላል "በጭንጫ ላይ የተዘራውም ይህ ቃሉን ሰምቶ ወዲያው በደስታ የሚቀበለው ነው ነገር ግን ለጊዜው ነው እንጂ በእርሱ ሥር የለውም፥ በቃሉ ምክንያትም መከራ ወይም ስደት በሆነ ጊዜ ወዲያው ይሰናከላል"። ይህ ክፍል ሰው ልቡን ከፍቶ ወንጌል ስምቶ ከዳነ በኋላ በተለለዩ መንገዶች የተለያዩ መከራዎች ሲመጡበት ክርስቶስን የሚተው ወይም በጌታ የሚደግም ነው።

፫. ሶስተኛው ዘር "በእሾህ መካከል ወደቀ፥ እሾህም ወጣና አነቀው" የዚህ ትርጉሙ በቁ.22 ላይ እንዲህ ይላል "በእሾህ መካከል የተዘራውም ይህ ቃሉን የሚሰማ ነው፥ **የዚህም ዓለም አሳብና** የባለጠግነት መታለል ቃሉን ያንቃል፥ የማያፈራም ይሆናል"። ብዙ ሰዎችን የዓለም ብልጥግና ምኞት አንቋቸው ጌታን መከተል ከባድ እንደሆነባቸው ብዙዎቻችን እናውቃለን። ለዚህ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲሆን ሉቃስ 16፥12-22 "እነሆም፥ አንድ ሰው ቀርቦ፡- መምህር ሆይ፥ የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ? አለው።እርሱም፡- ስለመልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንድ ነው፤ ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ አለው ።እርሱም፡- የትኞችን? አለው። ኢየሱስም፡- አትግደል፥ አታመንዝር፥ አትስረቅ፥ በሐሰት አትመስክር፥አባትህንና እናትህን አክብር፥ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ አለው ጐበዙም፡- ይህንማ ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄአለሁ፥ ደግሞስ የሚጐድለኝ ምንድር ነው? አለው፡፡ኢየሱስም፡- ፍጹም ልትሆን ብትወድ፥ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ፥ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፥ መጥተህም ተከተለኝ አለው።ጐበዙም ይህን ቃል በሰማ ጊዜ ብዙ ንብረት ነበረውና እያዘነ ሄደ"።

፬. አራተኛው ዘር በመልካም መሬት ወደቀ፤ አንዱም መቶ፥ አንዱም ስድሳ፥ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ ተዛማጅነቱ ወይም ትርጉሙ "በመልካም መሬት የተዘራውም ይህ ቃሉን ሰምቶ የሚያስተውል ነው፤ እርሱም ፍሬ ያፈራል አንዱም መቶ አንዱም ስድሳ አንዱም ሠላሳ ያደርጋል"። ይህ ዘር

በተለያየ ደረጃ ያለ የህይወት ምስክርነት ነው ማለት ምሉህ የሆነ ህይወት ነው።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ምሳሌ ማለት ምን ማለት ነው? በምሳሌ ማስተማር ከሌላው የማስተማር ዘዴ ልዩነቱ ምንድ ነው?
2. ምሳሌ የሚታወቀውን ነገር በመጠቀም የማይታወቀውን ነገር ሚስጥር ወይም ትምህርት የማስተማሪያ ዘዴ ነው። ይህንን አባባል አብራሩ?
3. የመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌዎችን ስናነብ ሙሉውን ክፍል ማንበብ እጅግ እስፈላጊ ነው። ለምን? ተወያዩ። ማቴ 13፡1-23 ጠቅለል ያለ መልዕክቱ ምንድ ነው?
4. በማቴ 13፡10-17 መሠረት ጌታ በምሳሌ ለምን እንዳስተማራቸው አብራሩ። የሰሚዎቹ ችግር ምን ነበር?
5. በማቴ 13፡18-23 እና በ 13፡1-10 መካከል ያለው ግንኙነት ምንድ ነው?
6. ከ18-23 ጊዜ ወስዳችሁ ተነጋገሩ፣በክፍሉ የተጠቀሱትን ምሳሌያዊ ንግግሮች ምንን ያመለክታሉ።

ሀ. ዘር ለ. ዘር ዘሪ/ገበሬ ሐ. ወፍ መ. መሬት ሠ. ፍሬ

7. በዚህ ምሳሌ ውስጥ የተጠቀሱት ሰሚዎች ችግራቸው ምን ነበር?
8. ማቴ 13፡11-15 ይህን ክፍል ዛሬ ከማን ጋር ልናመሳስል እንችላለን ብላችሁ ታስባላችሁ?
9. ከዚህ ትምህርት ምን እንማራለን? ከየትኛው ምድብ ይሆን ያለሁት (ፍሬ 30፣60፣100)?

# መደምደሚያ

የህይወትን ቃል ወደ ህዝቡ ጆሮ ለማስተላለፍ ክርስቶስ የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሟል። አንዱና ዋነኛው ዘዴ ማስተማር ነበር። በዚህ ክፍል ዘር የእግዚአብሔርን ቃል፣ ዘሪ ወንጌልን ወደ ሰው ልብ የሚናገረውን፣ መሬት የሰውን ልብ እና ፍሬ ደግሞ ድነትንና መንፈሳዊ ፍሬዎቹ ያመለክታል። ፍሬ ድነትን (ማቴ 7፡16) በመቀጠል ድነት ቅድስናን፣ክርስቲያናዊ ባህርይን ሥነ ምግባርንና መልካም ሥራን የሚያጠቃልል ነገር ነው (ሮሜ 6፡22፣ ገላ 5፡22-23፣ ሉቃ 10፡30)። የተዘራው ዘር በቅሎ ፍሬ ማፍራት ይጠበቅበታል። የሚገርመው በማቴ ወንገል 13 በተጠቀሰው የዘሪ ምሳሌ ሶስት አራተኛው (3/4ኛው) ዘር ፍሬ እንዳላፈራ እናያለን። ይህ አስደንጋጭ ነው። ወደ ጌታ ቤት ስንሄድ ወይም የጌታን ቃል በግላችን ስናነብ ልባችንን አዘጋጅተን መቅረብ አለብን። ጌታም እርሱን እና ሰውን በመውደድ ፍሬ ማፍራት አለብን። ለሌሎችም ይህ ዘር መብቀል እና ማፍራት እንዳለበት መንገር አለብን። ዕብራ 4፡12 እንደሚነግረን የጌታ ቃል የሚሰራና ህያው ነው።

## **ጥናት አሥር**

የእግዚአብሔር መንግስት ትምህርቶች በምሳሌ

ክፍል ፪

የንባብ ክፍል

ማቴዎስ 13፡24-30 እና 36- 43

## **የእንክርዳድ ምሳሌ**

***ዓላማ***

የዓለም መጨረሻ እስኪደርስ ድረስ በሰይጣን አሠራር ምክንያት ቤተ ክርስቲያን በመካከሏ የተለያዩ ዓይነት ሰዎች እንደሚመላለሱ አውቀን በግላችን ከተለያዩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካልሆኑ ማታለሎች እና የሀሰት ትምህርቶች እየተጠበቀን መኖር እንድንችል ማሳሰብ።

***መግቢያ***

በማቴ 13፡1-23 ጥናት እንዳየነው ሰይጣን የመጀመሪያ ጥረቱ ሰዎች ካላስተዋሉ ከልባቸው የጌታን ቃል መልቀምና በተለያዩ ዘዴዎች ፍሬ እንዳያፈሩ ማድረግ ነው። ይህ ባይሳካለት በአማኞች መካከል እንክርዳድ መዝራት ይጀምራል። ማለትም ከልብ ያላመኑ ወይም በህይወታቸው ክርስቶስን ያልመሰከሩ **<u>አማኝ መሰሎችን</u>** በቤተ ክርስቲያን መካካል ያስቀምጣል። እነዚህ ሰዎች ብዙዎችን ያሰናክላሉ። ሰዎች ጠማማ መንገድንና የተጣመመ የእድገት መስመር እንዲከተሉም ያደርጋል። ጥልቅ በመሆነ መንገድ የሀሰት ትምህርትን ያሰራጫል። እነዚህ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግስት የሚገቡ ሳይሆኑ ከእውነተኛ አማኞች ጋር ተመሳስለው የሚኖሩና ህይወትን የማያገኙ ናቸው (ማቴ 7፡21-23)። ምክንያቱም በእንክርዳድ የተመሰሉ ስለሆኑ በመጨረሻ ከንጽህ ዘር ወይም ከምርት ጋር አይቀመጥም። ስለዚህ በዚህ ጥናት ይህንን ትምህርት እናያለን።

ማቴ 13፡24-30 እና ከቁ.36- 43

ይህ ክፍል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እግዚአብሔር መንግስት በእንክርዳድ ምሳሌ ያስተማረበት ቦታ ነው። እንክርዳድ በእህል መካካል የሚበቅል የማይፍለግ ፍሬ አልባ የሆነ እጽዋዕት ነው። ማቴ 13፡24-30 ስናነብ ሁለት አይነት ዘር ዘሪዎችን እናያለን። እነርሱም የሰው ልጅ እና ዲያብሎስ ናቸው። ዘሩ የተዘራው መሬት የሰዎችን ልብ ሳይሆን የሚያመለከተው ይህን ዓለም ነው። መልካም ዘር በጌታ ድነው በዚህ ዓለም ያሉትን አማኞችን ይወክላል። ጌታም ደግሞ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች እውነተኛ የሆኑትን የራሱን ልጆች እየዘራ ይገኛል። “እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች። ነፍሱን የሚወድ ያጠፋታል፥ ነፍሱንም በዚህ ዓለም የሚጠላ ለዘላለም ሕይወት ይጠብቃታል” (ዮሐ 12፡23-25)።

ዲያብሎስ ደግሞ የራሱን ዘር በዓለም ላይ ይዘራል። እነዚህ ሀሰተኛ ወንድሞችንም ያጠቃልላል። በሌላ ቦታ ደግሞ የጌታ ቃል እንዲህ ይላል “ብዙ ጊዜ በመንገድ ሄድሁ፤ በወንዝ ፍርሃት፥ በወንበዴዎች ፍርሃት፥ በወገኔ በኩል ፍርሃት፥ በአሕዛብ በኩል ፍርሃት፥ በከተማ ፍርሃት፥ በምድረ በዳ ፍርሃት፥ በባሕር ፍርሃት፥ **በውሸተኞች ወንድሞች** በኩል ፍርሃት ነበረብኝ” ( 2 ቆሮ 11፡26)። ውሸተኛ ወንድሞች ትክክለኛ እና እውነተኛ ያልሆነ ወንጌል አስተማሪዎች እና የሰይጣን እንክርዳድ ዘር ናቸው። ጠላት በዓለም ቤተ ክርስቲያንም ጭምር (ባንቀላፉት) እንክርዳድ የሆነ ዘሩን ይዘራል።

> “በዚያን ጊዜ ሕዝቡን ትቶ ወደ ቤት ገባ። ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ ቀርበው። የእርሻውን እንክርዳድ ምሳሌ ተርጉምልን አሉት። እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፡- መልካምን ዘር የዘራው የሰው ልጅ

ነው፤ እርሻውም ዓለም ነው፤ መልካሙም ዘር የመንግሥት ልጆች ናቸው፤ እንክርዳዱም የክፉው ልጆች ናቸው፥ የዘራውም ጠላት ዲያብሎስ ነው፤ መከሩም የዓለም መጨረሻ ነው፥ አጫጆችም መላእክት ናቸው። እንግዲህ እንክርዳድ ተለቅሞ በእሳት እንደሚቃጠል፥ በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል" (ማቴ 13፡36-40)።

በመጨረሻም ዳግም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣ እንክርዳዶቹ ወደ እሳት ጻዲቃን ደግሞ ወደ እረፍት እንደሚገቡ የጌታ ቃል ያስተምረናል። ብዙ ሰዎች በአማኞች መካከል ይሁን ውጭ ብዙ የተለያዩ ታዓምራቶችን ቢያደርጉም መመዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በድጋሚ የስህተትና የእውነት ትምህርት መለኪያው የእግዚአብሔር ቃል ነው ስለሆነ ለይተን ማወቅ አለብን። ዕለት ዕለትም በጌታም ልናድግ ይገባናል።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በማቴ 13፡23-30 የተጻፈው ምሳሌ ዋና ነገር ምንድ ነው? በዚህ ክፍል ጌታ ሊያተምራቸው የፈለገው ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?
2. በማቴ 13፡36-43 መሠረት
    - የጥሩ ዘር ዘሪ ማን ነበር
    - እርሻው የምን ምሳሌ ነው
    - ጥሩ ዘር የምን ምሳሌ ነው
    - እንክርዳዱስ?
    - በዚህ ክፍል ዲያብሎስ በምን ተመስሎ ይገኛል?
    - መከሩና አጫጆቹስ?

3. ማቴ 13፥25 ጠላት ዘሩን የዘራው መቼ ነው? ለመዝራቱስ ምክንያት ምን ነበር?
4. በዚህ ክፍል ሁለት ዓይነት ሰዎች በምሳሌው ተተርጉመው ይገኛሉ። እነማን ናቸው? በማብራራት ተወያዩ።
5. ማቴ 13፥39-43 ባለው ክፍል የሚያሳዝነውና የሚያስደስተው ነገር ምንድ ነው? ምን ሃላፊነት አለብን?
6. በዚህ ጥናት መሠረት ትክክለኛ እና ትክክለኛ ያልሆነውን በምን እናውቃለን? አብረውን የሚኖሩ ሀሰተኞች አሉ ማለት ነው? የሚያሳዝነው ነገር ምንድ ነው (ማቴ 7፥21-23)?
7. ማቴ 7፥21-23 ከዚህ ጥናት ጋር ምን ግንኙነት አለው?
8. ከዚህ ክፍል ስለ መጨረሻ ዘመን ምን እንማራለን?
9. ከዛሬው ጥናት ለህይወታችን የቀረልን ቁልፍ ነገር ምንድ ነው?

***መደምደሚያ***

ክፉ በየቀኑ በእግዚአብሔር መንግስት መካከል እንክርዳድ ይዘራል። እንክርዳዱም በቅሎ ሊያድግ ሁሉ ይችላል። ነገር ግን ፍሬ ስለሌለው በመጨረሻ ዋናው እህል ሲሰበሰብ ተለይቶ ወደ እሳት ይገባል። ሠይጣን በተለያዩ መንገዶች ማለትም በውስጥና በውጭ ሰውን በማሳመጽና ሀሰትን በማስተማር ወንጌልን ለማዳፈን ቢሞክርም የጌታ ሥራ ሊያጠፋ አይችልም። በተጨማሪም ጌታ ዳግም ሲመጣ ሁሉም ነገር ይገለጣል። ልብን እና ተግባርን በግልጽ የሚያውቅ አምላክ በመጨረሸ ዋጋ ይከፍላል። ሰዎች ቤተ ክርስቲያን ስለተመላለሱ ብቻ ልድኑ አይችሉም። ፍሬያማ ልንሆን ይገባናል። የሀሰት ትምህርትን ለይተን ለማወቅ በጌታ ቃል እውቀት ልንሞላ ያስፈልገናል።

# ጥናት አሥራ አንድ
# የንባብ ክፍል
# ማቴዎስ 13፡31-35
# የእግዚአብሔር መንግስት ትምህርቶች (በምሳሌ)
# ክፍል ፫
# <u>የሰናፍንጭና የእርሾ ምሳሌ</u>

**ዓላማ፡-**

የእግዚአብሔር መንግስት ማለትም ቤተ ክርስቲያን ከጥቂት ተጀምሮ ያደገና የሚያድግ መሆኑንና ሰይጣንም ይሁን ሰው ሊያቆመው የማይችል ግዛት እንደሆነ ማስገንዘብ።

**መግቢያ**

ከዚህ በፊት ባለፉት ምሳሌዎች ጌታ ስዎችን ለማዳን ዘሩን ሲዘራ ሠይጣንም የራሱ እንክርዳድ እንደሚዘራ አጥንተናል። ይህም ብቻ ሳይሆን ቃሉን የሚሰሙት ሰዎችም እንደሚገባ የህይወት ምላሽ እንዳይሰጡ ማስተዋልን እንደሚሰርቅባቸውም አይተናል። በተጨማሪም ፍሬ አልባና እውነተኛ ያልሆነ ወንጌል በማሰራጨት የእግዚአብሔርን መንግስት/ቤተ ክርስቲያንን እንደሚዋጋም ተረድተናል። ነገር ግን አሁን በዚህ ክፍል ያለው ጥናት እንደሚያስተምረን የእግዚአብሔርን መንግስት ወይም ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ክፉ በብዙ መንገድ ቢታገልም ወንጌል ጥሶ እንደሚሰፋ ጌታ <u>የሰናፍንጭና የእርሾ ምሳሌዎችን በመጠቀም</u> አስተማረ ። በግል ህይወታችንም እንደዚሁ ነን። ምንም ቢታገል አያሸንፈንም።

ማሳሰቢያ፡- ሌሎች አስተማሪዎች ይህን ምሳሌ በተቃራኒው ይተረጉሙታል ማለትም የሰናፍጭ ቅንጣት ምሳሌ በውጭ ያለ አግባብ

በሌለ መንገድ የሚያድገውን የሀሰት ትምህርት የሚያመለክት ነው ሲሉ እርሾ ደግሞ በውስጥ ማለትም በአማኞች መካከል የሚሠራጭ የስህተት ትምህርት ነው ይላሉ። **ነገር ግን በዚህ ጥናት ዝግጅት የሰናፍጭ ቅንጣትም ይሁን የእርሾ ምሳሌዎች ከሁኔታዎች በላይ የሚያድገውን የእግዚአብሔር መንግስት እንደሚያድግ የሚያሳይ ምሳሌ እንደሆነ እናምናለን። ይህ ጥናት ይህን ትምህርት እያብራራ ይሄዳል።**

> "ሌላ ምሳሌ አቀረበላቸው እንዲህም አለ፡- መንግሥተ ሰማያት ሰው ወስዶ በእርሻው የዘራትን የሰናፍጭ ቅንጣት ትመስላለች። 32 እርስዋም ከዘር ሁሉ ታንሳለች፥ በአደገች ጊዜ ግን፥ ከአታክልቶች ትበልጣለች የሰማይም ወፎች መጥተው በቅርንጫፎችዋ እስኪሰፍሩ ድረስ ዛፍ ትሆናለች።33 ሌላ ምሳሌ ነገራቸው እንዲህም አለ፡- መንግሥተ ሰማያት ሁሉ እስኪቦካ ድረስ ሴት ወስዳ በሦስት መስፈሪያ ዱቄት የሸሸገችውን **እርሾ** ትመስላለች። 34-35 ኢየሱስም ለሕዝቡ ይህን ሁሉ በምሳሌ ተናገረ፤ በነቢዩም፡- በምሳሌ አፌን እከፍታለሁ፥ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወረውንም እናገራለሁ የተባለው ይፈጸም ዘንድ ያለ ምሳሌ አልተናገራቸውም" (ማቴ 13፡31-35) ።

የሰናፍጭ ዘር በወቅቱ በአከባቢው ከነበሩ ዘሮች ትንሹ ዘር ነበር። ነገር ግን ትልቅ ዛፍ እና ለተለያዩ ተፈጥሮዎች እረፍት ሆኖ በምሳሌው እናያለን። እርሾም እንደዚሁ የመስፋት ባህርይ አለው። እርሾ ሳይታይ የሚሰራጭ ነገር ነው። እርሾ ውስጥ ለውስጥ ሳይታይ ሲሰፋ ማንም ሊከለክለው አይችልም። በእርግጥ በመጽሐፍ ቅዱስ እርሾ ብዙ ቦታ የጥሩ ነገር ምሳሌ አይደለም ነገር ግን በዚህ ክፍል የጌታ መንግስት የመስፋት ምሳሌ ተደርጎ ቀርቧል። እግዚአብሔር አብርሃምን ሲጠራው አንድ ቤተሰብ ብቻ እና የእራሱም ልጅ ያልነበረው ሰው ነበር (ዘፍ 12፡1-3 ይነበብ) ። እግዚአብሔር ግን ብዙ ህዝብ በእርሱ ዘር እንደሚበዛ ቃል ገባለት።

"አባታችሁንም አብርሃምን ከወንዝ ማዶ ወሰጄ በከነዓን ምድር ሁሉ መራሁት ዘሩንም አበዛሁ፥ ይስሐቅንም ሰጠሁት" (ኢያሱ 24፥3፣ ተጨማሪ ዘፍ 17፡1-2)።

ዘጸ 1፥5 "ከያዕቆብ ጕልበት የወጡት ሰዎች ሁሉ ሰባ ነፍሶች ነበሩ ዮሴፍም አስቀድሞ በግብፅ ነበረ" ።

"አባቶችህ ሰባ ነፍስ ሆነው ወደ ግብፅ ወረዱ አሁንም አምላክህ እግዚአብሔር ብዛትህን እንደ ሰማይ ከዋክብት አደረገ" ( ዘዳ 10፥22)

በዚህ ቃል መሠረት ህዝቡ ግብፅን ለቀው ሲወጡ 600 000ሺ እግረኛ ነበሩ። ልጆችና ሴቶች ይህ ቁ. እስከ 2.5 ሚሊዮን ይገመታል። ዘጸ 12፥37 "የእስራኤልም ልጆች ከራምሴ ተነሥተው ወደ ሱኮት ሄዱ ከሕፃናቱም ሌላ ስድስት መቶ ሺህ ሰው የሚያህል እግረኛ ነበረ" ። ይህ ህዝብ ከነዓን ከገቡ በኋላ የራሳቸው ህግ ያላቸው ሀገር እንደሆኑ ይታወቃል። ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ የምንማረው ነገር ቢኖር ወንጌልን ለማጥፋት ሞክሮ ማንም እንዳልቻለ ነው። ይልቁኑ እየበዛ ሄደ። ዛሬ በዓለም ከሁለት ቢልዮን ህዝብ በላይ አማኞች በዓለም ላይ እንዳሉ ይገመታል።

"15 እርሱም፡- እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው። 16 ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፡- አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ። 17 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ። 18 እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም (በማቴ ወንጌል 16፡18))።

በዚህ ተስፋ መሠረት ጌታ በአዲስ ኪዳንም ህዝቡን ማለትም ቤተ ክርስቲያንን ይከላከላል። የሐዋርያት ሥራ መጽሀፍ ታሪክ እንደሚያስተምረን መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን ከሠይጣንና ከሰዎች ተግዳሮት አስመልጦ አሳድጓታል። ዛሬም በግላችን እና በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ጌታ ብዙ ዛቻዎችን እልፎ ይሰራል።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ይህ ጥናት ከዘሪ እና ከእንከርዳድ ምሳሌ ጋር ምና ግንኙነት ይኖረዋል ብላችሁ ታስባላችሁ።
2. እግዚአብሔር ለአብርሃም አንዱ የገባለት ቃል ኪድን ምንድ ነበር (ዘፍ 12፡1-3፣ ዘፍ 17፡1-2፣ ኢያሱ 24፡3)።
3. የእስራኤል ህዝብ ከየት ተነስተው እንደበዙ ተነጋገሩ (ዘጸ 1፡5፣ ዘጸ 12፡37)
4. እግዚአብሔር የእስራኤልን ህዝብ ቢያበዛም ህዝቡ እንዳይበዛ ሠይጣን የሞከረበትን መንገድ ተነጋገሩ።
5. ጌታ ቤተ ክርስቲያንን ማብዛት ሲጀምር ከስንት እንደጀመረ ተወያዩ።
6. ሠይጣን ከመጀመሪያ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ምን ምን እንደተቀመ ተወያዩ (ኢትዮጵያና ኤርትራ ስነበረው ስደት የሚታውቁ ነገር ካለ ተወያዩ)።
7. የሰናፍጭ ቅንጣት ዘር ምሳሌ ከእስራዔል እና ከቤተ ክርስቲያን ታርክ ጋር እንዴት እንደሚገናኝ በአጭሩ ተነጋጋሩ።
8. ከዚህ ጥናት ምን እንማራለን?

***መደምደሚያ***

የሰናፍጭ ቅንጣት ዘርና የእርሾ ምሳሌ የእግዚአብሔርን መንግሥት/የቤተ ክርስቲያንን ወይም የህዝቡን መሥፋትን ያስተምራል። ከአብርሃም ጀምሮ ህዝብ ለመመሥረት እግዚአብሔርን የከለከለው ኃይል አልነበረም። ጌታ ወደ ምድር መጥቶ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያሰፋ የገሀነም ደጆችም ሊከለክሉት አልቻሉትም። በቤተ ክርስቲያን ታሪክም መንፈስ ቅዱስ ሥራውን ሊሠራ ማንም አልከለከለውም። ብዙዎች ሞከረው አልቻሉትም። ዛሬም በግላችንም ይሁን በማህበር ጌታ ሥራውን ሊሰራ ማንም አይከለክለውም።

## ጥናት አሥራ ሁለት

### የእግዚአብሔር መንግስት ትምህርቶች

### <u>የተደበቀ ሀብትና የዕንቁ ምሳሌ</u>

ክፍል ፩

ማቴዎስ 13፥44-46

**ዓላማ፡-**

መንግስተ ሰማይ ዋጋ አለው ብለን ከምንገምተውና ከምናስበው ነገር ሁሉ በላይ የከበረ መሆኑን ለማስገንዘብ እና ለዚህም በዚህ ምድር ይህን ጸጋ ለመቀበል መክፍል ያለብንን ዋጋ ሁሉ እንድንከፍል ማሳሰብ፤

**መግቢያ**

ከዚህ በፊት በነበሩ ጥናቶች ሰው ልቡን ቢሰጥ የእግዚአብሔርን መንግስት (የዘላለምን ህይወት) ሊያገኝ እንደሚችል፤ ሠይጣን በተለያዩ መንገዶች ይህንን መንግስት ለማጥፋት ቢሞክርም እንደማይችል እና መንግሥቱ ትንሽ ጅማሬ ቢመስልም ፍጻሜው የሚሰፋ እንደሆነ አይተናል። በዚህ ጥናት ደግሞ ይህ መንግስት (የዘላለም ህይወት) ከሚገመተው በላይ እጅግ ውድ ስለሆነ ውድ ዋጋ መክፈል እንዳለብን ያስተምረናል። በዚህ ጥናት የተደበቀ ሀብትና የዕንቁ ምሳሌን እናጠናለን።

**ማብራሪያ**

<u>የዕንቁ ነጋዴ (ማቴ 13፥44-46፣ ማቴ 19፥16-21)</u>

በምድር ላይ ስመ ጥር እና ገናና ከሚባሉት የከበሩ ማዕድናት መሃል ዕንቁ አንዱ ነው። ይህ ማዕድን የከበረ ከመሆኑ የተነሳ ለሰውም ሆነ ለነገሮች ስያሜ ሲሆን እንሰማለን፤ በዋናነት ግን ለሃገራት የብልጥግና ምንጭ ነው (በዓለማችን ሩስያና ቦትስዋና ይህንን ማዕድን በማከማቸትየመሪነትን ስፍራ ይዘዋል)፡፡ መንግስተ ሰማይ እጅግ የከበረ ዋጋ ስላላት ያገኛት ዘንድ ማንም ያለውን ሁሉ ለመተው ፈቃደኛ ሊሆን ይገባል። ቁጥር 23፡- ለሁሉም

እንዲህ አላቸው፡- በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ። 24 ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና፤ ስለ እኔ ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን እርሱ ያድናታል። 25 ሰው ዓለሙን ሁሉ አትርፎ ራሱን ቢያጠፋ ወይም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል? 26 በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ፥ የሰው ልጅ በክብሩ በአባቱና በቅዱሳን መላእክቱ ክብርም ሲመጣ በእርሱ ያፍርበታል (ሉቃ 9፡23-26 ተመሳሳይ ጥቅስ ማር 8፡36-38)። ለተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሆን ዕብ 11፡23-26 እና ማቴ 19፡16-21 አንብቡ። ጌታ ኢየሱስ እንዲህ ማለቱ መንግሥተ ሰማያትን በገንዘብ ኃይል ወይም በመልካም ሥራ ብርታትእናገኛለን ማለት አይደለም።

### መንግስተ ሰማይ

እግዚአብሔር ለሚወዳቸው ከዚህ ከከበረው ዕንቁ በላይ ለልጆቹ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያዘጋጀው ስፍራ መንግስተ ሰማይ ይባላል። ይህንንም ስፍራ መውረስ የሚቻለው የየትኛውንም ያህል የጽድቅ ስራ በመስራት አይደለም፥ ወይንም በዓለማችን ብዙ ህዝብ የሚከተለውን ሃይማኖት በመከተል አይደለም፤ ነገር ግን ይህን መንግስት መውረስ የምንችለው ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን ብቻ ነው። የህይወታችንን መስዋዕትነት ይጠይቃል።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በምድር ላይ ያለውን የዕንቁን የከበረ ዋጋ ተወያዩበት? ከዘላለም ህይወት ጋር እንዴት ይገናኛል?
2. በክፍሉ ውስጥ የተጠቀሰውን የነጋዴውን ብልህነት እንዴት ተረዳህው? ለእኛ ምን ይጠቅማል?
3. ይህ ምሳሌ ሉቃ 9፡23-26፣ ማር 8፡36-38 ካለው መል ዕክት ጋር ምን ይገናኛል?

4. ማቴ 19፡16-21 ከዚህ ጥናት ጋር በምን ይገናኛል? ተወያዩ። ምንድ ነው ከባዱ ነገር ብላችሁ ታስባላችሁ።
5. በዚህ መንግስት ውስጥ ማን ሊኖርባት ይችላል? የተረዳህውን ለጥናት ቡድንህ አስረዳ?
6. ዕብ 11፡23-28 በማንበብ የሙሴ ህይወት ለዚህ ጥናት እንዴት ማብራሪያ ሊሆን ይችላል? ተነጋገሩ።
7. በአሁኑ ዘመን እንደዚህ ዓይነት የህይወት ፈተና ያለባቸው ሰዎች አሉ ባልችሁ ታምናላችሁ? እንዴት መርዳት እንችላለን?
8. የጌታ መንግስት እጅግ ውድ ነው! ምን ዋጋ እየከፈልን እንደሆነ እያሰብን ዛሬ ራሳችንን በመጠየቅ ዛሬ እንጸልያለን።

**መደምደሚያ**

በክፍሉ ላይ እንደምንረዳው ይህ የዕንቁን ዋጋ እና የክብርን ነገር የተረዳ ነጋዴ ይህን ዕንቁን ባገኘ ጊዜ ያለውን ሁሉ የንብረት ዋጋ ዕንቁ ላይ በማዋል የራሱ እንዳደረገ እንመለከታለን። በዚህ ክፍል ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ በምሳሌ እያስተማረ ያለው ስለ ከበረው፣ምትክ ስለሌለው እና ሁሉን ስለሚገዛው መንግስተ ሰማይ ውድነት ነው። መንግስተ ሰማይ ሰው በምድር ላይ ሊያገኘው ከሚችለው ማናቸውም የከበረ ነገር በላይ ከፍ ያለ ዋጋ እንዳለው ያስረዳል። ይህ መንግስት እንደ ምድራዊ መንግስት የማይሸረሸር፤ የማይፈርስ እና የማይሻር ለዘላለም የጸና መንግስት ነው (ዳን 4፡3)። እንግዲህ ወደ ዚህ ወደ ከበረው መንግስት እንድንገባ ከዚህ ሊጠፋ ካለው የዓለም ክብር ሁሉ አብልጠን ህይወታችንን ለኢየሱስ ሙሉ ለሙሉ መስጠት እና ማስገዛት አለብን (ሉቃ 9፡23-26)። ልንከፍል የምንችለውን ሁሉ መክፈል አለብን። ሁሉም ከንቱ የከንቱ ከንቱ ነው (መክ 1፡1)!!!

# አሥራ ሶስት
# የእግዚአብሔር መንግስት ትምህርቶች - በምሳሌዎች
# ክፍል ፫
# የመረብ ምሳሌ እና ከልብ ያለማመን ውጤት

ማቴዎስ 13፡47-58

**ዓላማ፡-**

የመንግስተ ሰማያት ነዋሪዎች እነማን እንደሆኑ መመልከት፤

## *መግቢያ*

የመረቡ ምሳሌ በማቴ 13፡37-43 እንደተጠቀሰው እንደ እንክርዳዱ ምሳሌ ተመሳሳይ የሆነ ትምህርትን ያስተላልፋል፤ ማለትም በጌታ ዳግም ምጽዓት ወይም በዚህ ዓለም መጨረሻ ኃጢአተኞች ከጻድቃን ተለይተው ወደ ዘላለም ሞትና ወደ ዘላለም ህይወት እንደሚገቡ ይናገራል። አንድ ዓሳ አጥማጅ ሰው መረቡን በባህር ላይ በሚጥልበት ጊዜ አንዳንዴ ምን እንዳጠመደ በውል ለይቶ ማወቅ አይችልም፤ ወደ ባህር የተጣለው መረብ መልካምና መልካም ያልሆኑ ዓሶችን ይይዛል። ስለዚህ የመለየት ሥራው የሚሰራው መረቡ ወደ ባህሩ ዳርቻ ተጎትቶ ከወጣ በኋላ ነው።

## *ማብራሪያ*

መረብ የሰበሰባቸው ሁሉ ዓሳዎች እንዳልሆኑ ሁሉ በቤተ ክርስቲያን የተሰበሰቡ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚገቡ እንዳልሆኑ ያስተምረናል። በማቴዎስ ወንጌል 13፡49-50 እንደሚናገረው በዘመኑ ፍጻሜ፥ በዓለም መጨረሻ፥ እንዲሁ ይሆናል፤ ማለትም መላዕክት መጥተው ኃጢአተኞችን ከጻድቃን መካከል ይለዩአቸዋል። በጥቅሉ የጌታ ፍርድ አለ ማለት ነው። የዚህ ሰማያዊ መንግስት ዜጋና ነዋሪ ለመሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቸኛ መንገድ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐ 14፡6 ላይ በግልጽ ያስተምረናል። በዮሐንስ ምዕራፍ አስራ አምስት ደግሞ መንፈሳዊ ፍሬ ማፍራት እንዳለብን ያሳስባል።

ማቴ 13፡53-58 ጌታችን በምሳሌ ያስተምር የነበረውን ትምህርቱን ጨርሶ ወደ ገዛ ሀገሩ እንደሄደና ማስተማሩን እንደቀጠለ ይናገራል። በዚህ ክፍል የቅርብ ቤተ ሰዎቹም የታወቁ እንደሆኑ ይናገራል ማለትም እህቶችና ወንድሞች እንደነበሩት ያረጋግጣል። በቅርብ ያሉት ባለመቀበላቸው ምክንያት እንዳላመኑ ይገልጻል፤ የምሳሌዎቹም ትርጉም በእነርሱ ላይ እንደተፈጸመ እናያለን።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. የመረብን አገልግሎት በግልጽ ለጥናት ቡድንህ አስረዳ?
2. ማቴ 13፡47 ደግሞ መንግሥተ ሰማያት ወደ ባሕር የተጣለች ከሁሉም ዓይነት የሰበሰበች መረብን ትመስላለች በዚህ ክፍል ባህርና መረብ ምንን እንደሚያመለክቱ ተነጋገሩ።
3. የመረቡ ምሳሌ ከእንክርዳዱ ምሳሌ ጋር በምን ይገናኛል?
4. ዓሳው ከተጠመደ በኋላ መልካሙንና መጥፎውን የመለየት ሥራ የሚከናወነው መቼ ነው? ምሳሌው ምንን እንደሚያስተምር ተወያዩ?
5. በቁጥር 48 ላይ "ውጭ" ተብሎ ለተጠቀሰው ቃል እኩል ወይም ተመሳሳይ ትርጉም ያለው ቃል በቁጥር 49 ላይ የትኛው ነው? ምንን ያስተምራል?
6. ሁሉም ሰው መንግስተ ሰማይ የመግባት እድሉ ተሰጥቶታል? አልተሰጠውም ካላችሁ ለምን?
7. ማቴ 13፡53-58 ከምሳሌዎቹ ጋር እንዴት ይገናኛል?
8. ይህ ጥናት ከማቴ 25፡31-33
9. ስለ ዓለም መጨረሻ ከዚህ ምሳሌ ምን እንማራለን?

## *መደምደምያ*

**“. . . ፤ የተጠሩ ብዙዎች፥ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና።”**

የዚህ ጥናት ዋና መልዕክት የሚከተለው ጥቅስ ነው፡- *እንዲሁ ኋለኞች ፊተኞች፥ ፊተኞችም ኋለኞች ይሆናሉ፤ የተጠሩ ብዙዎች፥ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና* (ማቴ 20፥16)። እንዲሁም በማቴ 22፡14 ተመሳሳይ ነገር ይናገራል፥ *የተጠሩ ብዙዎች፥ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና* ። መንፈሳዊ ፍሬ እያፈራን፥ ማለትም ለጌታና ለህዝቡ ሸንገላ የሌለበትን የወንጌሉን ፍቅር የምናሳይ ከሆንን በመረቡ ውስጥ እንዳሉት ዓሶች ምሳሌ እንሆናለን፤ ካልሆነ ግን በመረቡ ውስጥ እንዳልተፈለጉ ተፈጥሮዎች ምሳሌ እንሆናለን። ወንጌልን እንስበክ! ሰውን ሁሉ እንውደድ! ከስህተት ትምህርት እንጠበቅ! ለጌታ ክብር እንኑር! አሜን!

# ጥናት አሥራ አራት

## የትልቅነት ባሕሪያት

የንባብ ክፍል:- ማቴዎስ 18:1-35

**ዓላማ:-**

በጥናቱ አውድ መሰረት ለትልቅነት የሚያበቁ ባሕሪያትን ለማወቅና ወደዚያም ስለማደግ አስፈላጊነት ማስገንዘብ፤

**መግቢያ:-**

ይህ ክፍል በእግዚአብሔር ቃል መስፈርት መሰረት በክርስቲያን ወንድማማቾች (እህትማማቾች) መካከል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት የሚያብራራ ሲሆን፥ በተለይም በሁለት ዋና ዋና ባህሪያት ማለትም **በትሕትናና በይቅርታ** አስፈላጊነት ላይ ያተኩራል። ከቁጥር 1-14 ባለው ክፍል ላይ የተገለጠው ትምህርት ሰው በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ሆኖ ለመገኘት ራሱን ትሁት ማድረግ እንደሚገባው ያሳያል። ከቁጥር 16-35 ባለው ክፍል ደግሞ በችኮላና በጥድፊያ በሌሎች ላይ ከመፍረድ ይልቅ ለደካሞችና ለወደቁት ብንጸልይላቸው ይቅርታን ሊያገኙ እንደሚችሉ ያስተምረናል።

በማቴዎስ 18:4 ላይ ኢየሱስ ስለ ታላቅነት ባስተማረውና ሰዎች (ማቴዎስ 20:25-28) ባስተማሩት መካከል ያለውን ልዩነት ያሳያል። ከቁጥር 1-5 ያለው ከማርቆስ 9:33-37 ጋርና ከሉቃስ 9:46-48 ጋር ይመሳሰላል። ከቁጥር 6-9 ያለው ከማርቆስ 9:42-48 ጋርና ከሉቃስ 17:1-3 ጋር ይመሳሰላል። ከቁጥር 10-14 ያለው ከሉቃስ 15:1-10 ጋር ይመሳሰላል። **ከቁጥር 23-25 የሚገኘው ሃሳብ በማቴዎስ ውስጥ ብቻ የሚገኝ ነው።**

ታላቅነትን በተመለከተ ለተጠየቀው ጥያቄ **ካልተመለሳችሁ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ ወደ መንግስተ ሰማያት ከቶ አትገቡም** የሚል መልስ የተሰጠው ሲሆን ይህም ሕይወታችሁን በሙሉ ለእግዚአብሔር ካላደረጋችሁ፤

እራሳችሁን (ማንነታችሁን) በእግዚአብሔር ላይ ካልጣላችሁና እንደ ሕጻን በትህትና ካልተመላለሳችሁ የሚልን ሃሳብ ይዟል። **ከሁሉ የሚበልጥ ማነው?** የሰዎችን ለማነስ (ዝቅ ዝቅ ለማለት) አለመፈለግን የሚያሳይ ሲሆን ጌታ ኢየሱስ ሕጻን አምጥቶ በፊታቸው ማቆሙ በአንጻሩ **ማደግ በማነስ** እንደሆነ የሚያሳይ ነው። መጥምቁ ዮሐንስ *እኔ ላንስ እርሱ ሊልቅ ያስፈልጋል* እንዳለው ማለት ነው። እንደ ሕፃን የመሆን ባሕሪ በክርስቶስ መንግስት የሚያስፈልገው ታላቅ ለመሆን ብቻ ሳይሆን ወደ ውስጡም ለመግባት ነው (ማር 10:15)። ትሕትናና ፍቅር የተሞላ ባሕሪ ደካማ የሚመስለውንም ሆነ ደካማ የሆነውን ሰው በትህትናና በፍቅር የሚይዝ ነው።

“ወንድምህ ቢበድልህ” (ቁጥር 15) ለሚለው ሐረግ ደረጃ በደረጃ የምንወስደው እርምጃ ትህትና የተሞላበትን ብስለት የሚያሳይ ሲሆን “ሰባ ጊዜ ሰባት” (ቁጥር 22) የሚለው ደግሞ ይቅርታ ሰፊ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ነው።

ከቁጥር 15-20 ባለው ክፍል ላይ ደግሞ ዘር-ዘር ባለ መልኩ በኃጢአት የወደቁት እግዚአብሔር ወደ ንስሃ ያቀርባቸው ዘንድ፥ እንዲሁም በፈቃዳቸው ይመለሱ ዘንድ ልንፀልይላቸው የሚገባ መሆኑን እንገነዘባለን።

ከቁጥር 21-35፦ ራሳችንን ከሌሎች አልቀን እንዳንገምት የሚያስተምረን ሲሆን ይህም የሆነበት ምክንያት ሁላችንም ኃጢአተኞች ስለሆንና ከእግዚአብሔር ምህረትና ይቅርታ ስለሚያስፈልገን ነው። በተጨማሪም የበደሉንን ሁሉ ይቅር ማለት እንደሚገባን ያሳየናል።

በአጠቃላይ :-

- ዝቅ ብሎ በማገልገል በመንግስተ ሰማያት ትልቅ መሆን እንደሚቻል (ቁጥር 4-5)፥
- ሌሎችም ሆኑ ራሳችን ማሰናከያ ልንሆን እንደምንችል አውቀን መጠንቀቅ እንደሚኖርብን ያሳየናል (ቁጥር 6-9)፥
- የተሰናከለን ማፅናናት፣ መጠገንና ማደስ አስፈላጊ እንደሆነ እንረዳለን (ቁጥር 10-20)።

- ገደብ የለሽ ይቅርታም ማድረግ እንዳለብን (ቁጥር 21-35) በዚህ ጥናት ውስጥ በዝርዝር ተመልክተናል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ማቴ 18፡1-3 መሰረት መንግስተ ሰማያትም ሊገባ የሚችለውና በመንግስተ ሰማያት ታላቅ የሆነ ማን ነው?
2. በማቴ 18፡4 ላይ ኢየሱስ ስለ ታላቅነት ባስተማረውና በማቴ 20:25-28 መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
3. "እንደነዚህ ያለውን አንድ ሕጻን" የሚለውና "ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን" የሚለው ሀሳብ የሚያመለክተው ምን ዓይነት ክርስቲያኖችን ነው? ለምን?
4. እግዚአብሔር በሕጻን የመሰላቸውን አዲስ አማኞች ጠባቂ መላዕክት እንዳደረገላቸው/እንዳላቸው በማቴ 18፡10 ላይ ተገልጾልናል። ይህ ምንን ያመለክተናል?
5. ከቁጥር 1-14 ባለው ክፍል ምን እናስተውላለን?
6. ከቁጥር 15-18 እኛም ሰዎች ስለሆንን በችኮላና በኩሩ ልብ በሌሎች ላይ ከመፍረድ ይልቅ ማድረግ ያለብን ምንድን ነው?
7. ከቁጥር 23-35 የበደሉንን ሁሉ በትህትና ይቅር ማለት ያለብን በምን ምክንያት ነው?
8. በማቴዎስ 18:24 መሰረት በሰማያት ያለው የአባታችን ፈቃድ ምንድን ነው?
9. ከቁጥር 15-20 ላይ በተገለፀው መሰረት ከበደለን ወንድም ጋር በምን ዓይነት መንገድ ነው ሰላምን እንድንፈጥር የታዘዝነው ?
10. ከቁጥር 32-35 እኛ የበደሉንን ይቅር ባንል እግዚአብሔር በዚህ ነገር እንደሚጠይቀን የተገለጸው እንዴት ነው?

## መደምደምያ

በአጭሩ ከዚህ ጥናት የሚከተሉትን ነጥቦች በዋናነት ተመልክተናል፡-

- በማንም ላይ ሳንፈርድ ዝቅ ብሎ በማገልገል በመንግስተ ሰማያት ትልቅ መሆን እንደሚቻል (ቁጥር 4-5)፥
- ለሌሎችም ሆነ ለራሳችን ማሰናከያ ልንሆን እንደምንችል አውቀን መጠንቀቅ እንደሚኖርብን  (ቁጥር 6-9)፥
- የተሰናከለን ማፅናናት፣ መጠገንና ማደስ አስፈላጊ እንደሆነ (ቁጥር 10-20)፥
- **ገደብ የለሽ** ይቅርታም ማድረግ እንዳለብን (ቁጥር 21-35) አይተናል።

የተማርነውን በተግባር መግለጥ እንችል ዘንድ ጌታ ጸጋውን ያብዛልን።

## የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 23-25
## ጥናት አሥራ አምስት

የንባብ ክፍል ማቴ 23፥1-22

**ዓላማ:-**

ከግብዝነት እና የራስን ክብር ከመፈለግ ሩጫ ህይወታችንን በመጠበቅ እውነተኛ የጌታ ተከታዮች እና አገልጋዮች ለመሆን እንድንነቃቃ ለማሳሰብ ነው።

**መግቢያ:-**

በጥናቱ አጠቃላይ መግቢያ ላይ እንደተጠቀሰው አንዳንድ ሰዎች አምስተኛውን የትምህርት ክፍል ከማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24-25 ብለው ቢያስተምሩም የዚህ ጥትናት ዝግጅት ክፍል ማቴ 23-25 እንደሆነ ያምናል። ይህ ደግሞ የአስተምህሮ ችግር ስላልሆነ አይለያይንም፤ እንደተረዳነው ከፋፍለን ማጥናት እንችላለን። ፈሪሳውያን እና የኦሪት ሕግ መምህራን የሚባሉት አምስቱን የብሉይ ኪዳን የሙሴ መጽሐፍት ወይንም በሌላው መጠሪያቸው የሕግ መጽሐፍት የሚባሉትን ሙሉ በሙሉ የሚቀበሉ ሲሆን በትምህርታቸው ውስጥም ከፍተኛውን ስፍራ ይሰጡታል፤ ቢሆንም ግን የትምህርታቸው ጭብጥ ሲታይ በሥነ መለኮት ላይ ሳይሆን በሥነ ምግባር ላይ ያተኮረ ነው። ከዚህ ጎን ለጎንም የትውፊት መጽሐፍት የሚባሉትን (ከአምስቱ የሙሴ መጽሐፍት ውጭ ያሉትን በትውፊት መልክ የጻፉትና ያዘጋጇቸውንም ጨምረው) የእምነታቸው እና የትምህርታቸው መሰረት አድርገው የሚቀበሉ መሆናቸው ሊሰመርበት ያስፈልጋል። ከዚህ የተነሳ ነው ፈሪሳውያን እና የኦሪት ሕግ መምህራን በጸጋ ተሞልቶ እንደ ሰው ያውም የባሪያን መልክ ይዞ ሊታደጋቸው የመጣውን ጌታን በመንገድ ሊያልፉት የበቁት።

ከዚህ ቀጥሎ ባለው ክፍል ስለ ህይወት እና በትህትና ስለሚሆን አገልግሎት ከማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 23 እናጠናለን (ክፍሉ ከማቴ 24 እና 25 ጥናት ጋር ተያያዥነት አለው)።

## የምዕራፉ አጭር ማብራሪያ

### ማቴ 23፡1-4

ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት እና ህዝቡን ሰብስቦ ማስተማር የቀጠለበት ክፍል ሲሆን በቁጥር 2 መሠረት የኦሪት ሕግ መምህራን እና ፈሪሳውያን የህግ መምህርነት ሥልጣንን ተቀብለው በሙሴ እግር የተተኩ እንደሆኑ የሚያመለክት ነው። በዚህ ምዕራፍ ብቻ “እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን” የሚለው ሐረግ ሰባት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል። ቁጥር 3፡- እነዚህ የህግ መምህራን እና ፈሪሳውያን ስለ ሕጉ የሚያስተምሩት የከፋ ነገር የሌለበት ቢሆንም በተግባራቸው ግን የሚያስተምሩትን የሚጠብቁ ወይንም የሚያደርጉ እንዳይደሉ ያሳያል። ይህ ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ በእነርሱ ላይ አጠንክሮ እንዲናገር አድርጎታል። ቁጥር 4፡- እንደሚነግረን እነዚህ መምህራን እና ፈሪሳውያን ትምርታቸው እውቀት እንጂ ህይወት ስላልሆነላቸው ለሚያስተምሯቸው የቱንም ያህል የሚከብድ ትእዛዝን ለመስጠት አይፀፅታቸውም ነበር።

ማቴ 23፡5-8፡- እነዚህ መምህራን እና ፈሪሳውያን የሚያደርጉትንም ሆነ የሚሆኑትን የሚሆኑበት ምክንያት በሰዎች ፊት ለመታየት፣ ስለሚያገኙት የከበሬታ ስም እና ስፍራ መሆኑን የሚያብራራ ክፍል ነው።

ማቴ 23፡9-13 ደግሞ ጌታ ለደቀመዛሙርቱ እና ለህዝቡ በሰዎች ዘንድ የከበሬታ ስምንም ሆነ የከበሬታ ስፍራን ከመፈለግ እንዲጠበቁ የመከረበት እና ያስጠነቀቀበትን ክፍል እናገኛለን። እንዲሁም በመካከላቸው ትልቅ የሆነ ሌሎችን ማገልገል እንደሚገባው እና ታዛዥ መሆን እንዳለበት ያሳያቸዋል። በመፈሳዊው እይታ ከፍ ለማለት ዝቅ ማለት እንደሚገባ፤ በአንጻሩ ግን በምድራዊ እይታ ከፍ ያለ ስፍራን መፈለግ በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ የማይኖረው መሆኑን እና ዝቅ ማለት እንደሆነ አድርጎ ያብራራላቸዋል።

ማቴ 23፡13-15፡- ሁለተኛው ‘ወዮላችሁ’ የእነዚህ መምህራን እና ፈሪሳውያን ዋና ችግራቸው ግብዝነት (ተዋናይነት) መሆኑን በመጥቀስ በዚህ ሳቢያ በሰው ህይወት ላይ የሚያደርሱት ጉዳት እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ

ያሳያል። በዚህም ምክንያት ከሚጠብቃቸው የከፋ ፍርድ ጋር አያይዞ ያቀርበዋል፤ እንዲሁም ከዚሁ ጋር አያይዞ ሌሎችን ከእነሱ ለሚብሰው ክፋት ማዘጋጀታቸውን ከሦስተኛው 'ወዮላችሁ' ጋር ያቀርበዋል።

ማቴ 23፡16-24 ላይ አራተኛው እና አምስተኛው 'ወዮላችሁ' ጌታ እነዚህን መምህራን እና ፈሪሳውያን መንፈሳዊ ዓይኖቻቸው ከመታወራቸው የተነሳ ጊዜያዊውን ከዘለዓለማዊው፣ ምድራዊውን ከሰማያዊው፣ ያልከበረውን ከከበረው፣ የማይበልጠውን ከሚበልጠው ለይተው ለማየት አለመቻላቸውን በወቀሳ ይነግራቸዋል።

ማቴ 23፡25-28 ላይ ስድስተኛው፣ ሰባተኛው እና ስምንተኛው 'ወዮላችሁ' አሁንም ጌታ በእነዚህ ቁጥሮች እነዚህን መምህራን እና ፈሪሳውያን ከዚህ በላይ በተመለከትናቸው ቁጥሮች በመደጋገም እንደወቀሳቸው ሁሉ ከግብዝነታቸው የተነሳ ለውስጣዊ ማንነታቸው ሳይሆን በውጭ ለሚታየው ገጽታቸው ይበልጥ ቦታ የሚሰጡ በመሆናቸው ይወቅሳቸዋል። ስለዚህም ለመንፈሳዊውም ሆነ ለራሳቸው ህይወትና ማንነት የሚገዳቸው፤ የውጭ ማንነታቸው ወይም ገጽታቸው ሌሎች ተመልክተው የሚሰጧቸው ስፍራ ነው። እውነተኛው ማንነታቸው ምንም ዓይነት ቢሆን ግድ የሚላቸው ወይንም የሚያስጨንቃቸው ጉዳይ እንዳልሆነ መገንዘብ እንችላለን።

በማቴ 23፡29-36 በመቀጠልም መምህራን እና ፈሪሳውያን ዘጠነኛው 'ወዮላችሁ' ከአቤል እስከ ዘካሪያስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተገለጸውን የሰማዕት ታሪክ አጠቃሎ በማቅረብ እንዴት ከእነሱ እና ከቀደሙት አባቶቻቸው ይልቅ እጅግ በጣም የከፉ መሆናቸውን ሲያመለክታቸው፥ ለፈጸሙት ክፋትና በደልም ተጠያቂ መሆናቸውን በማያወላዳ ሁኔታ ይናገራቸዋል።

ማቴ 23፡37-39 ጌታ ኢየሱስ ለእስራኤል የተሰጠውን በርካታ የሆነ ዕዳሎት በማውሳት፤ እስራኤል ግን ከተሰጣቸው ዕዳሎት አንዱንም ሳይጠቀሙበት የቀሩ መሆናቸውን በምዕራፉ የመጨረሻ ሁለት ቁጥሮች ላይ አሳይቷል። ይህም እስራኤል ለታዳጊዋ እውቅና እስክትሰጥ ድረስ የሚቀጥል

መሆኑን የእስራኤልን ዕጣ ፋንታ አሳዛኝም በሌላ ጎን ደግሞ ተስፋ ያዘለም ያደርገዋል።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በማቴ 23፡1 መሠረት ጌታ ኢየሱስ እያስተማራቸው ስለነበሩት ታዳሚዎች ተወያዩ? ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው?
2. በቁጥር ሁለት ኢየሱስ ይናገርበት እና ያስተምርበት የነበረው ርዕስ ምንድን ነበር?
3. ቁጥር ሶስት ላይ ጌታ ለደቀመዛሙርትና ለህዝቡ ይነግራቸው የነበረው ምንድን ነው?
4. የሚያስተምሩትን ማድረግ እና ተግባራቸውን መከተል የለባችሁም ያለበት ምክንያት ምንድን ነው?
5. በማቴ 23፡3-8 እንደተገለጸው የህግ መምህራን እና የፈሪሳዊያን ዋና መለያ ወይንም ባህሪያቸው ምንድን ነው? በዝርዝር ተወያዩበት።
6. እነዚህ መምህራን እና ፈሪሳዊያን በህይወታቸው በቀዳሚነት የሚፈልጉት ዋነኛ ነገር ምንድን ነው? በዚያ ፈንታ መፈለግ ወይንም ማድረግ የነበረባቸውስ ምን ነበር?
7. በቁጥር 9-13 ለደቀመዛሙርቱ እና ለህዝቡ ጌታ የሰጠው ምክር እና ትእዛዝ ምንድን ነው? በዝርዝር ተመልከቱት።
8. ቁጥር አስራ አንድ ላይ **"ከመካከላችሁ ከሁላችሁ የሚበልጠው አገልጋያችሁ ይሁን"** የሚለውን ሀሳብ እንዴት ትረዱታላችሁ?
9. ግብዝነት እና የክብር ስም ለማግኘት የሚደረግ ሩጫ እስካለ ድረስ እውነተኛ የጌታ አገልጋይ መሆን የማይቻለው ለምንድን ነው ትላለህ?
10. በቁጥር አስራ ሁለት 'ከፍ የሚለው የሚዋረደው' እና 'ዝቅ የሚለው ደግሞ የሚከብረው' እንዴት ባለ መንገድ ነው ትላላችሁ?
11. በማቴ 23፡13-15 ጌታ ኢየሱስ "ወዮላችሁ!" የሚለውን አስፈሪ ማስጠንቀቂያ የሰጠበት ምክንያት ምንድን ነው ትላለህ? ፍርዳቸው አስከፊ የሚሆንበትስ ምክንያት ምንድን ነው?

**(ቀጥለው ያሉትን ጥያቄዎች በሚቀጥለው የጥናት ጊዜ ልትወያዩባቸው ትችላላችሁ)**

12. በማቴ 23፡16-22 ጌታ በትምህርቱ መካከል ሁለተኛውን "ወዮላችሁ!" ያቀረበው እንዴት ባለ መንገድ ነበር? የእነዚህ ሰዎች ዋና ችግራቸው ምንድን ነበር?
13. በዚሁ ክፍል እነዚህ ሰዎች ማየት የተሳናቸው ዋና ነገር ምንድን ነው? ሰው የነገሮችን ትክክለኛ ዋጋ ማየትና መረዳት የሚችልበት ፀጋ እንዴት ማግኘት እንደሚችል ተነጋገሩ?

14. በማቴ 23፡23-24 ላይ ፈሪሳውያን "ወዮላችሁ!" የተባሉበትን ምክንያት ተወያዩበት።
15. በእነዚሁ ቁጥሮች መሰረት መንፈሳዊ ዓይኖቻቸው አጥርተው ማየት ስለተሳናቸው የተደባለቀባቸው እና የተምታታባቸው በሌላ አባባል የገጠማቸው የዕይታ ዝብርቅርቆሽ ምንድን ነበር? ይሄ ትክክለኛ የሆነ የመንፈሳዊ እውቀት መሰረት አለማግኘት ወደ ምን እንዳመራቸው ተመልከቱ?
16. በእግዚአብሔር ዕይታ ቀዳሚ ሊሆን የተገባው ነገር ምንድን ነበር? እንዴት ነው ቅደም ተከተሉን ማስተካከል የሚችሉት?
17. በማቴ 23፡25-28 መሰረት ሌላው "ወዮላችሁ!" የተባሉበት ችግራቸው ምንድን ነበር? የችግራቸውስ መንስኤው ምንድን ነው ትላላችሁ?
18. ለሌሎች ዕይታ ሲባል ውጫዊውን ማንነት መገንባት የሚያስከትለው ችግር ምንድን ነው?
19. ከቁጥር ሃያ ዘጠኝ እስከ መጨረሻ ቁጥሮች ያለውን ሀሳብ እንዴት ነው የምትረዱት? የነቢያት ገዳይ ከነበሩት አባቶቻቸው ያላቸው የጋራ ነገር ምንድን ነው?
20. በእነዚሁ ቁጥሮች መሰረት ከሚመጣባቸው ፍርድ ሊያመልጡ የሚችሉበት አንድ እና ብቸኛ መንገድስ ምንድን ነው? የተሰጣቸውን ዕድል ያልተጠቀሙበት ምክንያትስ ምንድን ነው?
21. ለእራሳቸው የከበረ ስፍራ እና ስምን መፈላለጋቸው ሌሎችን እንዳይቀበሉ ምን ያህል እንቅፋት ሊሆን እንደሚችል ታያላችሁ? ምን ያስተምረናል?

22. የማቴ 23 ዋና መልዕክት ለምትወዱት አገልጋይ የማካፈል ዕድል ቢገጥማችሁ እንዴት ታስረዱታላችሁ?
23. በኑሮአችንና በአገልግሎታችን 'የታይታ' ፈተና እንዳይጥለን ራሳችንን እያየን እንጸልያለን?

## መደምደምያ

ጌታን እየተከተልንና እርሱን እያገለገልን ነው እያልን ሳናውቀው በግብዝነት እና የእራሳችንን ክብር በመፈለግ ወጥመድ ልንጠላለፍ የምንችልባቸው አጋጣሚዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ስለዚህ ቆም ብለን ህይወታችንን ከግብዝነት እርሾ እና የእራስን ክብር ከመፈለግ ወጥመድ የጸዳን እንደሆንን መመርመር ያስፈልገናል። እንድንታረምበትና እንድንማርበት እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ እንደሚናገረን እናምናለን። በማቴ 23 ጥናት እንዲህ ዓይነቱን ምክርና እና ተግሳጽ እግዚአብሔር ሲሰጠን ለጥቅማችን ስለሆነ በትህትና እራሳችንን እንድናይበት እና መንገዳችንን እንድናስተካከልበት ይገባል። 'እንዲህ ዓይነቱ ችግር የለብኝም' በማለት ፈንታ እራሳችንንም ሆነ ሌሎችን በጌታ ፊት በጸሎት ማቅረብ ተገቢ ነው።

የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 - 25

## መንደርደሪያ ሃሳብ፤

ይህ ጥናት የማቴ 24 እና 25 ጥናት መነሻ ከምዕራፍ 16 ከቁጥር 13-21 ካለው ክፍል ተነስቶ አንዳንድ ሃሳቦችን መዳሰስ ያስፈልጋል። በምዕራፍ 16 ከቁጥር 13-21 ባለው ክፍል ውስጥ ንጉሡ አዳኝ የሆነው ጌታችን ከደቀመዛሙርቱ ጋር ፊልጶስ ቂሳርያ በተባለ ስፍራ፤ ሰዎች ስለ እርሱ ማንነት ምን እንደሚሉና ደቀ መዛሙርቱም እራሳቸው ስለ ማንነቱ ምን እንደሚሉ ሲጠይቅና ሲወያይ እንመለከታለን። በወቅቱ ሰዎች ስለ እርሱ ማንነት ብዙ ይሉ ነበር። የጌታ ሃሳብ ግን የደቀ መዛሙርቱ ምላሽ ላይ ያተኮረ እንደነበር ማሰብና መገመት ስህተት አይሆንም። ለምን ግን ጌታ እንዲህ ያለውን ወሳኝ ጥያቂ በፊልጶስ ቂሳርያ ማቅረብ ፈለገ? የሚለውን ጥያቄ ለግል ጥናቶቻችን

በልቦናችን ጭረን፤ ለጥያቄው የተሰጠው ምላሽ ያስከተለውን የመልዕክት ሂደት እንመልከት። "አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ" ከሚለው የጴጥሮስ መልስ በኋላ የሚከተለውን ሃሳብ እናገኛለን፤

> *ኢየሱስ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ በዚያም በሽማግሌዎች፣ በካህናት አለቆችና በአሪት ሕግ መምህራን እጅ መከራን ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛው ቀን ከሞት ይነሣ ዘንድ እንደሚገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጽላቸው ጀመር* (ማቴ 16:21)።

"ከዚያ ጊዜ ጀምሮ..'' የሚለው ጅምር ዓረፍተ ነገር፤ እግዚአብሔር በመንፈሱ የልጁን ማንነት ለደቀ መዛሙርቱ ከገለጠ በኋላ መሆኑን ከአውዱ እንረዳለን። ይህ ከላይ ያነሳነው ጥቅስ ንጉሡ (የዳዊት ልጅ) ክርስቶስ የሚጠብቀውን መከራ የሚያሳይ፤ በተጨማሪም በታሪኩ ሂደት ውስጥ ቀጣዩ ጉዞ ወደ ኢየሩሳሌም መሆኑን የሚያመለክት ነበር። ክርስቶስ መከራ እንደሚቀበል ማወቅ፤ ደቀ መዛሙርቱ ሊሰሙት የሚፈልጉት ዜና ስላልነበር በተደጋጋሚ ሊነግራቸውና ሊያዘጋጃቸው ከሚፈልገው ሃሳብ ይሸሹ ነበር። እንደዚያ እንዲሆኑ ካደረጋቸው ምክንያቶች አንዱ ስለ እግዚአብሔር መንግስት የነበራቸው መረዳት ሚዛን የጠበቀ ስላልነበር እንደሆነ ከቀጣዮቹ ምዕራፎች መገንዘብ እንችላለን።

በወቅቱ የነበረውን የሮም ቀንበር ሰብሮ፣ የእስራኤልን መንግስት መልሶ መስርቶ፣ ሲነግሥና እነርሱን ከስሩ ሲሾማቸው ማየት ነበርና ሃሳባቸው፤ እኔ እበልጥ ይሆን ይባባሉም ነበር። ጌታም በተደጋጋሚ ወደ መከራው ጉዳይ ይመልሳቸው ነበር። ከፊልጶስ ቂሳርያ ከስድስት ቀን በኋላ "በመገለጥ" ተራራ ላይ የነበረውም ክስተት ከመከራው ጋር የተያያዘ እንደነበር ክፍሉን ከሌላ የወንጌል ክፍል ጋር አመሳክረን ስናነበው እንረዳለን። በተራራው ላይ ከጌታ ጋር የነበሩት የሶስቱ የደቀ መዛሙርት ፍላጎትና ምላሽ ከላይ ያነሳነውን ሃሳብ የሚያጠናክር ይመስላል። በምዕራፍ 18 ላይ የሚታየው "ማን ይበልጣል?" ጥያቄና ሙግት፥ በተጨማሪም በምዕራፍ 20 ቁጥር 20 የነዘብዴዎስ እናት

ሁለቱ ልጆቿ እንዲሾሙላት ያቀረበችው የተሳሳተ ጥያቄ የደቀ መዛሙርቱን መረዳትና ፍላጎት የሚያሳዩ መለኪያዎች ናቸው።

> *ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ላይ ሳለ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ለብቻቸው ወስዶ እንዲህ አላቸው፡- እንግዲህ ወደ ኢየሩሳሌም መሄዳችን ነው፤ የሰው ልጅ ለካህናት አለቆች ለኦሪት ሕግ መምህራን አልፎ ይሰጣል እነርሱም እንዲሞት ይፈርዱበታል፤ እንዲያላግጡበት፣ እንዲገርፉትና እንዲሰቅሉት ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታል በሦስተኛውም ቀን ከሞት ይነሳል* (ምዕራፍ 20፥17-19)

ከፊልጶስ ቂሳርያ የተነሳውን ንጉሥ፤ "ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ፤ በጌታ ሥም የሚመጣ የተባረከ ነው ..." እየተባለለት በታላቅ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ በምዕራፍ 21 ከቁጥር 1-11 ላይ እንመለከታለን።

ምዕራፍ 23 ላይ ያጠናነውን ሃሳብ ሳንዘነጋ፤ አሁን ለመንደርደሪያ ያነሳናቸውን ነጥቦች ቋጭተን ምዕራፍ 24 እና ምዕራፍ 25ን ወደ መመልከት እንለፍ። ሁለቱም ምዕራፎች በርካታ ቁጥሮችን የያዙና ብዙ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ስለሆኑ የተረፉትን ምዕራፎች ለመመልከት ጊዜ እንዳያጥረን በማሰብ እያንዳንዱን ምዕራፍ ቢያንስ በሶስት ቦታ ከፍለን ለማጥናት እንሞክራለን።

## ጥናት አሥራ ስድስት

## ማቴዎስ ምዕራፍ 24

ክፍል ፩

## የንባብ ክፍል ማቴ 24፡1-14

## ማቴ 24፡1-3

**ዓላማ፡-**

በክፍሉ ውስጥ ጌታ ስለ ዓለም መጨረሻና ዳግም ስለ መምጣቱ የሰጣቸውን ምልክቶች ማስተዋል፤ ምልክቶቹ በሚፈጸሙበት ዘመንና ጊዜ ከአማኝ የሚጠበቀው ምን እንደ ሆነ አውቆና ተረድቶ የጌታን መገለጥ በመናፈቅ መኖርን ማነሳሳት።

**መግቢያ፡-**

በዚህ ጥናት ውስጥ የምዕራፍ 24ን መግቢያ፣ የምጡንና የመጨረሻውን ዘመን መጀመሪያ ምልክቶች እንመለከታለን።

**አጭር ማብራሪያ**

ከቤተ መቅደሱ ወጥቶ መሄዱ፤ "በጌታ ሥም የሚመጣ የተባረከ ነው እስከምትሉ ድረስ ዳግመኛ አታዩኝም" ከሚለው ሃሳብ ጋር የሚያያዝ በመሆኑ ማቴዎስ ምዕራፍ 23ን ማንበብና ማስታወስ ጥሩ ይሆናል። በአጭሩ ምዕራፍ 23 ጌታ ፈሪሳውያንንና የኦሪት ሕግ መምህራንን የነቀፈበት ክፍል ነው። "መሪዎች" እንደመሆናቸው መጠን የእግዚአብሔርን ልጅ ሊያውቁና ሊቀበሉት ይጠበቅባቸው ነበር፤ ነገር ግን ልባቸው ከእውነት የራቀ ስለ ነበር፤ አለማመናቸውንና አለመቀበላቸውን በብዙ አይነት ተቃውሞ ይገልጹ ነበር። በምዕራፍ 21 ቁጥር 12 ጌታ ወደ መቅደሱ ገብቶ ያየውንና ያደረገውን መለስ ብሎ ማሰብ፤ ምን ያህል ኢየሩሳሌም (የእምነት መዲና) ለጌታዋ የተዘጋጀች እንዳልነበረች ያስረዳናል። ለዚህ ሁሉ አለማመንና አለመታዘዝ፥ የጌታም ተቃውሞ ከቤተ መቅደሱ ወጥቶ በመሄድ የተገለጸ ይመስላል።

ከታሪካዊ መረጃዎች ባሻገር፤ የደቀ መዛሙርቱ መደነቅና መሳብ፤ ስለ ቤተ መቅደሱ ወበትና ታላቅነት ብዙ ሊነግረን ይችል ይሆናል። "ሆሳዕና ለዳዊት

ልጅ፤ በጌታ ሥም የሚመጣ የተባረከ ነው" ተብሎ በታላቅ አጀብ ኢየሩሳሌም የገባው ንጉሥ፤ ከአለቆችና ከመሪዎች ከደረሰበት ተቃውሞና እርሱም ስለ እነርሱ በስፋትና በግልጽ ካስቀመጠው ነቀፋ አንጻር፤ ነገሮች የከረሩበት ወቅት እንደ ነበር ግልጽ ነው። አስቀድመን እንዳየነው፤ ጌታ በኢየሩሳሌም ምን ሊጠብቀው እንደሚችል ያውቅ ነበር። ደጋግሞ ነግሯቸው ስለ ነበር  ደቀ መዛሙርቱም ቢሆኑ ስለሚጠብቀው መከራ ያውቃሉ። ታዲያ በዚህ ሁሉ ሁኔታ ወስጥ በመቅደሱ ውበት መሳባቸው፤ አልፎም የሕንጻውን ውበት ለጌታ ለማሳየት መቅረባቸው የሚያስገርም ሃሳብ ይመስላል። የዚህ ምዕራፍ ንጽጽር የሆኑት ማርቆስ 13:1-2 እና ሉቃስ 21:5-6 ስለዚህ ጉዳይ ጥቂት ገለጥ አድርገው ይነግሩናል። የሕንጻውን ወበት ለማድነቅ የጋበዙት ጌታ፤ "እውነት እላችኋለሁ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ተከቦ የምታዮት ሳይፈርስ እንዲሁ እንዳለ የሚቀር አንድ ድንጋይ እንኳ አይኖርም" በማለት የመቅደሱን የወደፊት ዕጣ ፈንታ ነገራቸው። ይህም በ70 ዓ.ም ከኢሩሳሌም መፈረስ ጋር አብሮ መፈጸሙን በታሪክ የታየ የምናነበው ጉዳይ ነው።

በቁጥር ሶስት ላይ የተጠቀሱት የደቀ መዛሙርቱ ጥያቄዎች፤ በጊዜና በሁኔታዎች ላይ ያተኮሩ ነበሩ። "...መቼ ይሆናል? / ....ምልክትስ ምንድን ነው ?" በሚሉት ሁለት ሃሳቦች ሥር የቀረቡት ጥያቂዎች፤ በዚህ ሁልት ምዕራፎችፕ ውስጥ ጌታ ላስተማረው ትምህርት የመነሻ ምክንያቶች ሆነው ይታያሉ።

## <u>ማቴ 24</u>፡4-8

በእነዚህ ቁጥሮች ሥር የምንመለከታቸው አምስት ምልክቶች "የምጡ መጀመሪያ" በመባል ተሰይመዋል። እነዚህን አምስት ምልክቶች በሌላ እይታ ብናስቀምጣቸው፤ በአለም ውስጥ የታየውንና የሚታየውን የሃይማኖት ፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የተፈጥሮ ቀውስ የሚያሳዩ ይመስላሉ። እኔ ክርስቶስ ነኝ በማለት በስሜ ይመጣሉ ( መንፈሳዊ ወይም የሃይምኖት ቀወስ)። ስለ ጦርነትና ጦርነትን የሚያናፍስ ወሬ እንዲሁም ሕዝብ በሕዝብ መንግስት በመንግስት ላይ ይነሣል (ማህበረሰባዊ ወይም የፖለቲካ ቀወስ)። ረሃብ እና

የመሬት መንቀጥቀጥ (የኢኮኖሚና ተፈጥሮዊ ቀውስ)። በነዚህ ምልክቶች ጊዜ የአማኝ ደርሻ፤ እኔ ክርስቶስ ነኝ ከሚሉ አታላዮች መጥንቀቅና በዓለም ሁኔታ አለመደናገጥ እንደሆነ በግልጽ ተጽፏል።

**ማቴ 24፡9፡14**

በዚህ ክፍል ውስጥ የተዘረዘሩት ምልክቶች ከቁጥር 4-8 ላይ ከተዘረዘሩት በሁለት መልኩ ለይተን ልናያቸው እንችላለን። ከቁጥር 4-8 ያሉት ምልክቶች፤ በአለም ሁሉ ባሉት ላይ የሚደርሱና የምጡ መጀመሪያ ናቸው። ከቁጥር 9-14 ያሉት ደግሞ የተወሰኑ ሰዎች ላይ ያነጣጠሩ፤ በተለይም "ስለ *ሥሜ* ምክንያት" በማለቱ  በጌታ የሚያምኑትን የሚያሳይ ይመስላል። በተጨማሪም እነዚህ ምልክቶች የመጨረሻው ምልክት መምጣቱን የሚያሳዮ ተደርገው በምዕራፉ ውስጥ ተገልጸዋል።

"...ስለ *ሥሜ* ምክንያት...የተጠላችሁ ትሆናላችሁ።" በማቴዎስ 5፡11 ላይ ስንመለከት፤ ስለ ጌታ *ሥም* መጠላትና ማንኛውም አይነት መከራ መቀበል ታላቅ ዋጋ ያለው በረከት ነው። ዓለም የራሱ የሆኑትን ይወዳል እንደሚል፤ እንዲህ አይነቱ መከራ፤ የጌታ መሆናችንን፤ የአለም አለመሆናችንን የሚመሰክር ነውና በእርግጥ ክብር ነው። "በሕዝብ ሁሉ ዘንድ" የሚለው ሃሳብ የጥላቻውን የአድማስ ስፋት ሲያሳይ፤ እንዲህ አይነቱ ጥላቻ የሚፈጥረው ተጽኖ፤ አንዳንዶች ወገኖቻቸውን አሳልፈው እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል። ከዚህ የተነሳ አለመተማመንና ይፍቅር መቀዝቀዝ ይሆናል። መለያየትና ጥላቻ ባለበት ሁሉ ጠላት መሥራቱ የማይቀር ነው። ስለዚህ በዚህ ወቅትም የሐሰት ነቢያት መኖራቸው ተገልጿል።

ከዚህ ሁሉ መከራ ባሻገር " የመንግስት ወንጌል" በአለም እንደሚሰበክ ይናገራል።  አንዳንዶች "የመንግስት ወንጌል" የሚለውን ሃሳብ "ከደህንነት ወንጌል" የተለየ መልዕክት እንድሆነ አድርገው ይናገራሉ።  በእርግጥ መጸሐፍ ቅዱስ እንዲህ አይነት የተከፈለ ሁለት አይነት ወንጌል ስለመኖሩ የሚናገረው ነገር የለም። ወንጌል አንድ ነው። መጥምቁ ዮሐንስ "የእግዚአብሔር መንግስት ቀርባለች ንስሃ ግቡ" ብሎ ሰበከ። መልዕክቱን የተቀበሉትንም በውሃ አጠመቀ። ጌታም ዮሐንስ እስር ቤት ከገባ በኋላ ያንኑ

ስብከት “ የእግዚአብሔር መንግስት ቀርባለችና ንስሃ ግቡ” ሲል ሰበከ። መልዕክቱን ተቀብለው ያመኑበትና የተቀበሉትም መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ(በመንፈስ ተጠመቁ)። የመንግስት ወንጌል የደህንነት ወንጌል ነው። የደህንነት ወንጌል የመንግስት ወንጌል ነው። ሰዎች ንስሀ እንዲገቡና ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ ይህው ይሰበካል።

## <u>*የመወያያ ጥያቄዎች*</u>

1. ከምዕራፍ 23 ጥናት አንጻር፤ የምዕራፍ 24 መግቢያን ስንመለከት፤ በጌታና በተቃዋሚዎቹ መካከል ስለ ነበርው ውጥረትና ውዝግብ ምን እንገነዘባለን? እስከዚህ ሰዓት ድረስ ነገሮች እንዴት ነበር እየተካረሩ የመጡት? (ይህ ጥያቄ ክለሳን ለማነሳሳት ታስቦ የቀረበ ሲሆን፤ አስቀድመን አንዳንድ ጉዳዮችን ለክለሳ ብናዘጋጅ በብቃት መወያየት እንችላለን)
2. ኢየሱስ ከቤተ መቅደሱ ወጥቶ ሲሄድ፤ ደቀ መዛሙርቱ ያደረጉት ምንድን ነበር? የጌታስ ምላሽ ምን ነበር? (የቤተ መቅደሱን ውበት አስዩት (ማር13፡1-2፣ ሉቃ 21፡5-6)/ እርሱም ስለመፈረሱ ነገራቸው)
3. በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ሳሉ ደቀ መዛሙርቱ የጠየቁት ጥያቄ ምንድን ነበር? ማወቅ የፈለጉትስ ስለምን ነበር?
4. ከቁጥር 5-8 ባለው የንባብ ክፍል ውስጥ የተጠቀሱት የዓለም መጨረሻ ምልክቶች ምን ምን ናቸው?
    - እኔ ክርስቶስ ነኝ በማለት በስሜ ይመጣሉ (ቁጥር 5)
    - ስለ ጦርነትና ጦርነትን የሚያናፍስ ወሬ ይሰማል (ቁጥር 6)
    - ሕዝብ በሕዝብ መንግስት በመንግስት ላይ ይነሳል (ቁጥር 7)
    - ራብ (ቁጥር 7)
    - የመሬት መንቀጥቀጥ (ቁጥር 7)
5. ከላይ የዘረዘርናቸው አምስት ምልክቶች ከዓለም መጨረሻ አንጻር በክፍሉ ወስጥ ምን የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል?

6. እነዚህ የምጡ ጣር መጀመሪያ የተባሉት ምልክቶች ዛሬም በዓለም ወስጥ ይታያሉ?ታዲያ ገና አሁንም የምጡ መጀመሪያ ላይ ነው እንዴ ያለነው? እንዴት ነው ልንረዳው የሚያስፈልገው?
7. በዚህ የምጥ ጣር መጀመሪያ ጊዜ ላሉ አማኞች እንዲይደርጉት የተስጧቸው ምክር እና ትእዛዛት ምን ምን ናቸው?
8. ተጠበቁ እና አትደንግጡ የሚሉትን ሃሳቦች በዚህ ዘመን ለምንገኝ አማኞች ምን ያኽል አስፈላጊ ናቸው ትላለህ?
9. ከቁጥር 9-14 ባለው የንባብ ክፍል ውስጥ የተጠቀሱት ምልክቶች ምን ምን ናቸው?
    - ለመከራ አሳልፈው መስጠት መገደልና መጠላላት(ቁጥር 9)
    - ስለስሙ መጠላት እና መገደል ( ቁጥር 10)
    - ሐሰተኛ ነቢያት መነሳት (ቁጥር 11)
    - ፍቅር ይቀዘቅዛል (ቁጥር 12)
    - ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል (ቁጥር 14)
10. ከላይ ባየነው ጥያቄ 4 እና 9 መሰረት ስለ ዓለም መጨረሻ በተሰጡት ሁለት ምልክቶች መካከል ልዩነት ካለው ተነጋገሩ?
11. ሰዎችን ሁሉ የሚመለከቱ ምልክቶች የትኞቹ ናቸው? ክርስቲያኖች ብቻ ላይ ያተኮሩትስ ምልክቶች የትኞቹ ናቸው?
12. የፍቅር መቀዝቀዝ እንደ ምልክት ሆኖ ተቀምጦል፤ ፍቅር እንዲቀዘቅዝ ምክንያት የሆነው ምንድን ነበር? ይህ ሃሳብ ዛሬ እንዴት ሊታይ ይችላል?
13. ከወንጌል ስበከት ጎን ለጎን የሐሰተኛ ነቢያት መነሳት በመጨረሻው ዘመን ስላለው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ምን ያመለክታል?
14. ከዛሬው ጥናት ስለዓለም ፍጻሜ የተለየ የተማርከው ነገር ካለ አካፍል? በዚህ መጨረሻ ዘመን እኛስ በህይወታችን እንዴት እንዴት እንኑር?

***<u>መደምደሚያ</u>***

ጌታ ኢየሱስ ትምህርቱን ከመጨረሱ በፊት የመጨረሻ ዘመን ወይም የእርሱን ዳግም ምጽዓት ምልክቶችን ትምህርት አስተማረ። በመጨረሻ ዘመን የስህተት ትምህርት እንደሚኖር የስህተት ትምህርት ከመለጠጡ የተነሳ "እኔ ክርስቶስ ነኝ" የሚሉ ሁሉ እንደሚነሱ ተናገረ። ሰዎች ክርስቶስ ነኝ ማለት የስህተት ሁሉ ጫፍ እንደሆነ አሰማረ። ነገር ግን ወንጌልም ቢሆን ጎን ለጎን እንደሚሰበክ ጌታ ኢየሱስ አስተማረ።

## ጥናት  አሥራ ሰባት
## ማቴዎስ  ምዕራፍ 24
## ክፍል  ፪
## የንባብ ክፍል ማቴ 24፡15-35

**ዓላማ፤**

በዚህ ክፍል ጌታ ስለ ዓለም መጨረሻና ዳግም ስለ መምጣቱ የሰጣቸውን ምልክቶችን ማስተዋል፣ምልክቶቹ በሚፈጸሙበት ዘመንና ጊዜ ከአማኝ የሚጠበቀው ምን እንደ ሆነ አውቆና ተረደቶ የጌታን መገለጥ በመናፈቅ መኖርን ማነሳሳት።

**መግቢያ፡-**

በዚህ ጥናት ውስጥ የምዕራፍ 24 ሁለተኛውን ክፍል የመጨረሻው ዘመን ምልክቶች እንመለከታለን።

**አጭር ማብራሪያ**

ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ስለ ዓለም መጨረሻና ስለ ዳግም መምጣቱ የሚያሳዩትን የመጨረሻዎቹን ምልክቶች መዘርዘር ሲቀጥል፤ የዳንኤል ትንቢትን (9:27 እና 12:11) መሰረት በማድረግ፤ ስለ "ጥፋት ርኩሰት" "Abomination of Desolation"  ይናገራል። በዳንኤል መጻሐፍ የምናነበው ይህ ትንቢት በዘመን ውስጥ ተደጋግሞ ስለ መፈጸሙ ታሪክ

ይነግረናል። ከቁጥር 15 ጀምሮ ባለው ሃሳብ መሰረት ደግሞ ጌታ ከመምጣቱ በፊት የተፈጸመና የሚፈጸም መሆኑን ይናገራል።

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ168 ዓ.ዓ የሶርያው ንጉስ Antiochus Epiphanes ከነሰራዊቱ ወደ ኢየሩሳሌም ዘምቶ፤ ለግሪኩ ጣኦት ለዙስ (Zeus) በመሰዊያው ላይ አሳማን መሰዋቱና መቅደሱን ማርከሱን ታሪክ ይናገራል። ከክርስቶስ ልደት በፊት በ165 ዓ.ዓ ላይ በተነሳው እንቅሳቃሴ (Maccabean revolution) መሰዊያውና መቅደሱ ለእግዚአብሔር ዳግም ከተቀደሱ በኋላ፤ እንደ ገና በ63 ዓ.ዓ የሮም ጀነራል Pompey እግዚአብሔርን በመዳፈር ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ እንደገባ የአይሁድ መጽሐፈት ይናገራሉ።

በማቴዎስ 24:2 ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ስለ ቤተ መቅደሱ መፈረስ እንደተናገረው፤ በ70 ዓ.ም የሮም ስራዊት ወደ ኢየሩሳሌም ተሞ፤ ከተማይቱናን መቅደሱን ማፈራረሱ ይታወቃል። ይህ ሃሳበ በቁጥር 15 ከለው ሃሳብ ጋር የሚያያዝ ሲሆን በቁጥር 21 ላይ ያለው ደግሞ ገና ወደፊት የሚሆነውን በአውሬው አምካኝነት የሚፈጠረውን ታላቁን መከራ የሚያሳይ እንደሆነ ይገመታል። ጌታ ስለ ቤተ መቅደሱ መፍረስ አስቀድሞ ተናግሮ እንደሆነው፤ አሁንም በቅርብ የጥፋት ርኩስት ወይም የጥፋት ልጅ/ አውሬው በክፋቱ ወደ ኢየሩሳሌምን መዝመቱ የማይቀር ነው። አባት ሆይ እባክህ ምህረትህ ፍጥና ትምጣ እንዳልከውም ቀኖቹ ይጣሩ በኢየሱስ ሥም አሜን!

የጥፋት ርኩስት በተገለጠባቸውና በሚገለጥባቸው ወቅቶች ሁሉ፤ እግዚአብሔርን ከመዳፈሩ ባሻገር፤ ቁጣውን በአይሁድ መግለጡ የተለመደና የማይቀር ነው። ከቁጥር 16-21 ያለውም ክፍል ይህንኑ ሃሳብ እውን ያደረጋል። ከቁጥር 16-18 ያለው ሃስብ፤ በመከራው ጊዜ የሚኖሩ ጨርቄን ማቄን ሳይሉ በፍጥነት ሸሽተው እንዲያመልጡ የተሰጠ ማሳስቢያ ይመስላል። የቤቱ ጣራ ለቤቱ ምን ያህል ቅርብ መሆኑን መገመት አይከብድም። ነገር ግን ጌታ ንብረትን ጥሎ ነፍስን ለማዳን የሚሸሽበት መሆኑን ያስያል። ይህ የማይቀር እንደሆነ ሲያስረግጥ፤ ነገሩ መሸሽ

በማይችሉበት ወቅት እንዳይ ሆን እንዲጸልዩ ከቁጥር19-20 ባለው ክፍል ውስጥ ያዛል። መሸሸ ለምይችሉም ወዮላቸው ብሏል። ቁጥር 21 ስለ ታላቁ መከራ ይናገራል።

ከቁጥር 26-31 ባለው ክፍል ውስጥ ስለ ጌታ ዳግም አመጣጥ ሁኔታዎች ይናገራል። ጌታ በሥውር ለተወሰኑ "ምርጦች" ብቻ እንዲታይ ሆኖ እንደማይመጣ ሲናገር ፤ "... ያውላችሁ በበረሐው...." "... ይኸውላችሁ እልፍኝ ውስጥ...." ቢሏቹህ አትስሙ ብሏል። በግልጸ ሰለመምጣቱም ሲናገር " መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ ምዕራብ ድረስ እንደሚያበራ፤ የሰው ልጅ አመጣጥም እንዲሁ ነው" ብሏል።

በበለስ ዛፍ ምሳሌ፤ ለምልክቶቹ ትኩረት እንዲያደርጉና በእነርሱም ዳግም መምጣቱ መቃረብን እንዲያውቁ በመንገር ያቀረቡትን ጥያቄ 50% ሲመልስ፤ የቃሉንም እርግጥኝነት ሲያጸና ከቁጥር 32-35 ባለው ክፍል ውስጥ እንመለከታለን።

## <u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. ማቴ 24፡15 ላይ ጌታ አንባቢው "ያስተውል" የሚለው ስለምንድን ነው? በዚህ ቁጥር ውስጥ ያለው ሃሳብ ከቁ. 2 ሃሳብ ጋር እንዴት ይገናኛል?
2. በቁ.24፡ 15 መሰረት አማኝ ዘመኑን ለማወቅና ለመመርመር የሚችለው እንዴት ነው?
3. "የጥፋት ርኩሰት" እና "በተቀደሰው ሥፍራ" የሚሉት ሐረጎች የሚያመለክቱት ስለ ምንድን ነው?
4. በቁ.16-18 ለዘመኑ ምልክት ሆኖ የተዘረዘሩት ምን ምን ናቸው? ስለ ምን ጉዳይ ያስረዱናል?
5. ከቁ.19-20 ላይ ያለው ሃሳብ ምንድን ነው? ስለ ዘመኑ ምን ያስረዳናል?
6. ቁ.21 ከቁ.15 ጋር ይዛመዳል? በሁለቱ ቁጥሮች ለዘመኑ ምልክት ሆኖ ስለሚገለጠው የተረዳችሁትን አካፍሉ።
7. ቁ. 23 እና ቁ.26 ላይ የተሰጠው ምክር ወይንም ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው?

8. ቁ. 24 ስለ ሐሰተኛ ክርስቶሶችና ስለ ሐሰተኛ ነቢያቶች መነሳት በመደጋገም መጠቀሱ የሚያመለክተው ምንድን ነው?
9. ቁ. 26, 27 እና 30 ላይ ያሉትን ሃስቦች በማገናዘብ፤ ስለ ጌታ ዳግም አመጣጥ ሁኔታ ከክፍሉ የተረዳኸውን አካፍል?
10. ቁ. 28 እና ቁ. 29 ላይ የተዘረዘሩት የዓለም መጨረሻና የጌታ ዳግም መምጣት ምልክቶች ምንድን ናቸው?
11. ቁ. 30-31 ባለው ክፍል ከጌታ ዳግም መምጣት ጋር የተዘረዘሩት ሃሳቦች ምን ምን ናቸው?
12. ቁ. 32 ላይ የተጠቀሰችው የበለስ ዛፍ ምሳሌ ምንን ለማስተማር የገባ ነው?
13. ከዛሬው ጥናት ለየት ባለ መንገድ የተረዳኸው ወይንም ጥያቄ የሆነብህ ነገር ካለ አካፍል።

## መደምደሚያ

ከክርስቶስ መምጣጥ በፊት የሚሆኑትን ምልክቶች ጌታ በዝርዝር በዚህ ክፍል እንዳስተማረ አይተናል። ይህም ደግሞ ምልክቶቹን ስናይ ብዙዎቹ እየተፈጸሙ እንደሆኑ ግልጽና በገሃድ የታወቀ እውነት ነው (ለምሳሌ በዓለም እየተካሄደ ያለው ጦርነት፣ጥላቻ፣ረሃብ፣የመሬት መንቀጥቀጥ እና ወዘተ) ። ይህን በማየት የጌታ ምጽዓት ስለቀረበ እንደ አማኞች ልንዘጋጅ ይገበናል። ወንድሞችና እህቶች፣ ሁልጊዜ ተዘጋጅቶ መጠበቅ እጅግ ጠቃሚ ነው።

# ጥናት   አሥራ ስምንት

# ማቴዎስ ወንጌል  ምዕራፍ 24

# ክፍል  ፫

# የንባብ ክፍል ማቴ 24፡36- 51

**ዓላማ፤**

***ጌታ በዚህ ቀን በዚህ ሰዓት ይመጣል አይባልም ፤ ምክንያቱም ቀኑንና ሰዓቱን የሚያውቅ አብ ብቻ ነውና።   ስለዚህ ማወቅና ማድረግ የሚገባንንም እንድናስተውል ማሳሰብ።***

***መግቢያ፤***

***ድንገት የሚመጣውን የጌታን ቀን  ነቅተን እንድንጠብቅ የሚያነሳሱን እውነታዎችን በዚህ ጥናት ውስጥ እንመለከታለን። ቀኒቷ ግን ድንገት እንደምትሆን ከቀጣዮ ክፍል ያስተምረናል። ለተሰጠን አደራ ታማኝ ሆኖ መጠበቅ ዋጋ ያለው መሆኑንና ታማኝነትን ማጉደልም አደጋ እንዳለውም እናያለን።***

***አጭር ማብራሪያ***

በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሁለት ዋና ሃሳቦችን እንመለከታለን። በቅድሚያ የምናየው፤ ጌታ ዳግም ተመልሶ የሚመጣበት ጊዜና ሰዓት ከአብ በቀር ማንም የሚያውቅ አለመኖሩን ነው። ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ እንደተናገረው “ መላእክትም ቢሆኑ ወልድም እንኳ” የቀኑን መቼነት አያውቁም። የመላእክቱ አለማውቅ መቼም ጥያቄ አይፈጥርብንም፤ ምክንያቱም መላእክቱ ውስኖች መሆናቸውን እናውቃለን። ምናልባት ግን አንዳዶች ስለምንድ ነው ወልድ ቀኑን የማያውቀው ብለው ሊያስቡና ሊጠይቁ ይችላሉ። በእርግጥ እርሱ ሁሉን የሚያውቅ **ፍጹም አምላክ** ደግሞም **ፍጹም ሰው** መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ይህን ክፍል እንደ ሰው ሆኖ እንደተናገረ ብዙዎች ይምናሉ። የሰው ልጅ በብዙ ነገር የተወሰነ እንደሆነ እናውቃለን። ክርስቶስ ስብዕናውን ስገልጥ ፍጹም እንደሰው ይሆን ነበር።  ሆኖም ግን ይህ ሀሳብ ጥያቄ ሆኖ ቢቀርብ ፤ ካላወቅን “አላውቅም” ማለት እራሱ መልስ ነው።

“...መቼ  ይሆናል?” ለሚለው ጥያቄ ቁርጥ ቀን ባይሰጥም፤ የቀኑን ድንገተኘነት በምሳሌዊ  አስደግፎ በመናገር ጌታ ደቀ መዛሙርቱ ነቅተው እንዲጠብቁት ያዛቸዋል። የኖህ ዘመን ታሪክና በለሊት የሚመጣው የሌባ ምሳሌ የቀኑን ድንገተኘነት ለማስረዳት የቀረብ ናቸው። ቁጥር 40 እና ቁጥር 41 ጌታ ሲመጣ ስለሚሆነው መነጠቅ ይናገራሉ። በታሪኩ መሰረት ሁለት ሰዎች በአንድ ስፍራ ሳሉ የሚከሰት በመሆኑ፤ የነገሩ ክስተት ለቀሪው አለም የሚታወቅ መሆኑንን የሚያሳይ ሃስብ አለው።

ከቁጥር 45-51 ያለው ታሪክ ነቅቶ መጠበቅና አለመጠበቅ ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ነው። ጌታን ነቅቶ መጠበቅ ታማኝነትና አስተዋይነት መሆኑን ቀደም ብሎ ከተጻፈው ሃሳብ እንመለከታለን። ከታሪኩ አንጻር ነቅቶ መኖር የጌታን አደራ በታማኝነት መወጣትና እርሱ ፈጥኖ እንዳሚመጣ ማስብ ነው። ታማኝነቱን ካጎደለው ባሪያ እጣ ፈንታ፤ ጌታን በታማኝነት ነቅቶ አለመጠበቅ ምን ያህል እንደሚያጉድል እንመለከታለን። ነቅቶ መጠበቅ የሚለው ሃሳብ በቀጣዮ ምዕራፍ ላይ በሰፊው እንመለከታለን። በቀጣዮቹ በርካታ ቁጥሮች ውስጥ ሃስቡ በስፋት መብራራቱ፤ ምን ያህል ጌታ ለጉዳዩ ትኩረት ልንሰጥ እንደሚፈልግ ሊያሳስበን ይገባል።

## *<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>*

1. ከዚህ በፊት በነበረው ጥናታችን ስለ ዓለም መጨረሻ እና ስለ ጌታ ዳግም ምጽዓት ቀን እና ሰዓቱን በተመለከት ጌታ ለደቀመዛሙርቱ የተሰጠው መልስ ምን ነበር?
2. ጌታ በዚህ ቀንና በዚህ ሰዓት ነው የሚመጣው ብለው በደፍረት የሚናገሩ ሰዎች፤ የሳቱ የሚሆኑት ከምን የትነሳ ነው?
3. ቁ. 39 ጌታ በኖህ ዘመን የነበረውን የጥፋት ውሃ በምሳሌ ማቅረቡ ምንን ለማጠናከረ ፈልጎ ነው?

4. ቁ. 40- 43 ጌታ ዳግም ሲመጣ ሰዎችን የሚያገኛቸው በምን ሁኔታስ ውስጥ ነው? ለደቀመዛሙርት የተሰጠው ምክር እና ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው? ለምን?
5. ጌታ ስለ ሌባ አመጣጥ የሚናገረው ምንን ለማስረዳት ነበር? ከቁጥር 37-38 ሃሳብ ጋር እንዴት ሊዛመድ ይችላል?
6. ማቴ 24፡ 45- 47 የምናየውን አገልጋይ ታማኝና ልባም ሊያሰኘው የሚቻለው ነገር ምን ነበር? ይህስ ነቅቶ ስለመጠበቅ የሚለውን ሃሳብ እንዴት ያብራራልናል?
7. ሌላኛውን አገልጋይ ክፉ ሊያሰኙት የቻሉት ተግባራትና አስተሳሰብ ምንድ ነው? እንዲህ ላለው አገልጋይ እጣ ፈንታው ምንድን ነው?
8. ከዛሬው ጥናት ለየት ያለ የተረዳኸው ወይንም ጥያቄ የሆነብህ ነገር ካለ አካፍል።

***<u>መደምደሚያ</u>***

“ጌታችሁ በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ”። እዚህ ክፍል ጌታ መቼ ይመጣል ለሚል ጥያቄ መልስ አግኝተናል። ቀኑንና ሰዓቱን ማንም እንደማያውቅ ጌታ በግልጽ አስቀምጦታል። እንደ ኖህ ጊዜ የማያቋርጥ ዝናብ እንደጀመረ ወይም ደግሞ እንደ ሌባ መቼ እንደሚሆን አናውቅምና ካላይ ቃሉ እንደነገረን ተግተን እንጠብቅ። ሌሎችንም በርቱ እንበላቸው። “ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፥ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና” (ማቴ 24፡44)።

# ጥናት   አሥራ ዘጠኝ
# የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 25
# ክፍል ፩
# ማቴ 25፡ 1-13
# የዐሥሩ ልጃገረዶች ምሳሌ

**ዓላማ፡-**

በጥንቃቄ የጌታን ዳግም ምጽዓት እንድንጠብቅ ማሳሰብ

**መግቢያ፡-**

ድንገት የሚመጣውን የጌታ ቀን ፤ ነቅተን እንድንጠብቅ የሚያነሳሱን እውነታዎች በዚህ ጥናት ውስጥ እንመለከታለን። ነቅቶ መጠበቅ የሚለው ሃስብ በዚህ ክፍል ውስጥ በመብራትና የመብራት ዘይት ይዞ በመገኘት ተብራርቷል። ስለዚህም ዘይታችን ሞልቶ እያበራን ጌታን እንድንጠብቅ ከቃሉ እንማራለን።

## አጭር ማብራሪያ

የዚህ ምሳሌ አላማ  በቁጥር 13 ላይ በግልጽ ተጽፏል። ቀደም ሲል በምዕራፍ 24 ከቁጥር 45-51 ባለው ክፍል እንደተመለከትነውና  ቀጥሎን እንደምናየው የጌታ ዓላማ ደቀ መዛሙርቱ ነቅተው እንዲጠብቁት ማስተምር ነበር። በምዕራፍ 25 መግቢያ ላይ የምናገኘው “የዐሥሩ ልጃገረዶች ምሳሌ” ለዚሁ ዓላማ የቀረበ ነበር። ምሳሌው በዘመናችንም ሆነ በባህላችን አይተነው ስለማናውቀው  የሙሽራ አይነት ያወጋናል። ነቀቶ መጠበቅ ፤ ሙሽራውን ለመቀበል የሚያስፈልገውን አሟልቶ መገኘት መሆኑን ከታሪኩ እንረዳለን። ልክ አስተዋይ የተባሉት አምስቱ ልጃገረዶች እንዳደረጉት ማለት ነው።

በቁጥር 5 ላይ “ሙሽራው በዘገየ ጊዜ ሁሉም እንቅልፍ ተጫጫናቸውና ተኙ” የሚል ሃስብ እንመለከታለን። ይህ ሃስብ መጠበቅ ምን ያህል እንደሚያደክም የሚያሳይ ይመስላል። አዎ መጠበቅ አድካሚ ሥራ ነው። በተለይ ደግሞ በምዕራፍ 24 ከቁጥር 4-35 ላይ በተጻፉት የመከራና የስቃይ ጊዜ ውስጥ ሆኖ መጠበቅ እንዲሁ በስሜት የሚሆን አይደለም። ለዚህም ነው ጌታ ደጋግሞ ነቅቶ ስለመጠበቅ ያሳሰበው።

የልጃገረዶቹ ዝግጅት በያዙት መብራት ዘይት ሁኔታ ተወስኗል። አስተዋይ የተባሉት መጥባበቂያ ዘይት ሲኖራቸው ዝንግዎቹ ደግሞ አልያዙም። በዚህ ምሳሌ ውስጥ ያተጠቀሰው የመብራት አይነት እንደ ችቦ ያለ፤ በዘይት ውስጥ በመነከር የሚነድ፣ በተለይም ከቤት ውጭ ላለ ተግባር የሚውለውን አይነት ይመስላል። አንድ ወይም ሁለት ከበዛ ደግሞ አምስቱ መብራት ግኡዙን ጨለማ ለመግፈፍና ሙሽራውን በድምቀት ለመቀበል አይበቃም ነበር? አዎ ይህ የተፈጥሮን ጨለማ ለማባረር ስለሚለኮሱ ችቦዎች የሚናገር ባለመሆኑ ከእያንዳንዱ እጅ የሚያበሩት ችቦዎች ተጠብቀው ነበር።

**_የመወያያ ጥያቄዎች_**

1. ማቴ 25፡1 ላይ መንግሥተ ሰማይ በምን ተመስላለች?
2. በዚህ ክፍል የተጠቀሱትን ቆነጃጅት በሁለት የተለያየ ጎራ እንዲከፈሉ ያደረጋቸው ምክኒያት ምንድን ነው?
3. መጽሐፍ ቅዱስ ሰነፍ የሚላቸው ምን ዓይነት ሰዎችን ነው? ልባሞችስ የሚባሉት ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው?
4. በቁ. 5 ላይ ቆነጃጅቶቹ ሃላፊነታቸውን ወይንም ተግባራቸውን እንደሚገባ እንዳይወጡ ያዘናጋቸው ነገር ምንድን ነው ትላለህ?
5. ለመንፈሳዊ አዚም, ዝለት, ድንዛዜ ብሎም ለመንፈሳዊ እንቅልፍ ምክኒያት ይሆናሉ የምትላቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?
6. በቁ. 6-7 በእኩለ ሌሊት ላይ ቆነጃጅቱ የሰሙትና ያደርጉት ምን ነበር?
7. ቁ. 9 ላይ ያለውን የቆነጃጅቱን ምላሽ ወይንም ተግባር እንዴት እንመለከተዋለን?
8. በቁ. 10 ሙሽራው የመጣው በምን ጊዜ ላይ ነበር?
9. ቁ. 12 የሰነፎቹ ወይንም የዝንጉዎቹ ቆነጃጅት ዕጣ ፈንታ ምን ነበር? ለዚህ ተጠያቂው ማን ነው?
10. የቆነጃጅቱ ምሳሌ ዋና መልዕክት ምንድን ነው? የምሳሌውን መልዕክት በግልጽ የሚያሳየው ቁጥር የቱ ነው? ለምን?

11. ዛሬ ይህ ምሳሌ በእኛ ሕይወት እንዴት ሊተረጎም ይችላል? እንደ መብራትና እንደ ዘይት አድርገን የምንወስደው ነገር ምን ሊሆን ይችላል?
12. ከዛሬው ጥናት በተለየ መንገድ የተረዳኸው ወይንም ጥያቄ የሆነብህ ነገር ካለ አካፍል።

### መደምደምያ

ይህም ክፍል በድጋሚ የሙሽራውን ኢየሱስ ዳግም መምጣት እጅግ ነቅተን መጠበቅ እንዳለብን አስተምሮናል። የኩራዞቻችን ዘይት እንዳያልቅና መንፈሳዊ እንቅልፍም እንዳይወስደን እንንቃ!

## ጥናት ሃያ
## የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 25
## ክፍል ፪
## የንባብ ክፍል ማቴ 25፥14-30

### ዓላማ፡-

ድንገት የሚመጣውን የጌታ ቀን፤ ነቅተን እንድንጠብቅ የሚያነሳሱን እውነታዎች መመልከት፤

### መግቢያ፤

ጌታ በዚህ ቀን በዚህ ሰዓት ይመጣል አይባልም ፤ ምክንያቱም ቀኑንና ሰዓቱን የሚያውቅ አብ ብቻ ነውና። ቀኒቷ ግን ድንገት እንደምትሆን ከቀጣዩ ክፍል እንመለከታለን። ነቅቶ መጠበቅ የሚለው ሃሳብ በዚህ ክፍል ውስጥ ደግሞ ፍሬያማ ሆኖ መጠበቅ በሚል ሃሳብ ተብራርቷል። ስለዚህ እኛም በተሰጠን ስጦታ ፍሬያማ ሆነን ጌታን እንድንጠብቅ ከቃሉ እንማራለን፤ ማወቅና ማድረግ የሚገባንንም እናስተውላለን።

### የክፍሉ ማብራሪያ

መንፈሳዊ መጠበቅ ሕያው መጠበቅ ነው። ጌታን መጠበቅ ዝም ብሎ ተቀምጦ መቅረት ማለት አይደለም። በውስጡ መጥበቅን የሚያሳዩ

ተግባራት አሉት። በምዕራፍ 24፡ 45-51 ባየነው ነቅቶ መጠበቅ ውስጥ አደራን በታማኝነት በመወጣት መጠበቅ የሚል ሀሳብን እናገኛለን። በምዕራፍ 25 ፡1-13 ባለው ክፍል ውስጥ ችቧችንን አብርተን ዘይታችንን ሞልተን መጠበቅን እናያለን። ከቁጥር 14 -30 ባለው ክፍል ደግሞ ፍሬማ ሆኖ መጠበቅን እንመለከታለን። ጌታ እስኪመጣ ያለው ጊዜ የሥራና የፍሬ ጊዜ መሆኑን ያሳያል። ይህ ደግሞ እንደ አማራጭ የተሰጠ ሳይሆን፤ የሚጠበቅ ሕይወት ነው። በታሪኩ ውስጥ የምናያቸው ሶስቱ አገልጋዮች ከጌታቸው እንዲያፈሩ የተሰጣቸው ታላንት ነበር። ዳግም ሲመጣም እንደ መታመናቸው ሲከፍላቸው እናያለን። ጌታ የዓለም መጨረሻና የመምጣቱ ጊዜ መቼ እንደሆን ለጠየቁት ደቀ መዛሙርት፤ በመካከል ያለው ጊዜ የሥራና የፍሬ መሆኑን በምሳሌዎቹ ይናገራል።

በዚህ ክፍል የመክሊት ክፍፍል እና ስለ መክሊቱ ንግድ ያስተምራል። ይህም በመጨረሻ ተጠያቂነትን የሚያስከትል እንደሆነ ያስተምራል።

## <u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. 25ቁ. 14-15 ወደ ሌላ አገር የሄደው ጌታ፡ ለባሪያዎቹ ያለውን ገንዘብ ያከፋፈለው ምንን መሰረት አድርጎ ነበር?
2. የመክሊቱ መጠን መለያየት ስለ አደራ ሰጪውም ሆነ ስለ ተቀባዮቹ ምን ያስተምረናል?
3. ጌታቸው ገንዘቡን ያከፋፈለበት ምክንያት ወይንም ዓላማ ምንድን ነበር? ተቀባዮቹስ ይህንን ዓላማ የተገነዘቡ ወይንም የተረዱ ይመስልሃል?
4. አደራ ተቀባዮቹ ሃላፊነታቸውን ለመወጣት ወይንም ድርሻቸውን ለመፈጸም ይረዳቸዋል ብለህ የምታስበው ነገር ምንድን ነው?
5. የሚጠበቅባቸውን ሃላፊነት የተገነዘቡት ወይንም የተረዱት ባሮች ሃላፊነታቸውን እንዴት ነበር የተወጡት?
6. ቁ. 24 -25 አደራውን ሳይወጣ የጌታውን ገንዘብ ወስዶ የቀበረው ለድርጊቱ ያቀረበው ምክንያት ምንድን ነበር?

7. አምስት የተሰጠው አምስት፤ ሁለት የተሰጠው ደግሞ ሁለት ከማትረፋቸው ፤ የምንማረው ምንድን ነው?
8. ጌታቸው ከሄደበት ተመልሶ በመክሊታቸው ላተረፉት እና ወስዶ ለቀበረው የተናገርውን በዝርዝር ተነጋገሩበት?
9. የተቀበሉትን አደራ የተወጡበት መንገድ ስለ ባሪያዎቹ ባህሪ ወይንም ማንነት የሚነግረን ነገር አለ?
10. የዚህ ምሳሌ ዓላማ ምንድን ነው? ይህስ ዛሬ ከእኛ ህይወት እና አገልግሎት ጋር እንዴት ይዛመዳል?
11. በተሰጠን መክሊት እያተረፍን ውጤታማ እና ፍሬማ በሆነ ህይወት የጌታን ዳግም መመለስ በንቃት እንድንጠብቅ ዛሬም እድል ያለን ይመስልሃል?
12. ከዛሬው ጥናት የተለየ የተረዳኸው ወይንም ያስተዋልከው ነገር ካለ አካፍል።

## ***መደምደምያ***

ጌታ በኤፌ 4፡11-13 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ላይ በሄደ ጊዜ ለአካሉ የተለያዩ ጸጋዎችን እንዳከፋፈለ የጌታ ቃል ይናገራል። እነዚህ ጸጋዎች እያንዳንዱ አማኝ ነግዶ ነፍሳትን እንዲያተርፍ የተሠጠ ስጦታ ነው። ስለዚህ በተሠጠን መክሊት ማትረፍ እንዳለብን በግልጽ ያስተምራል። በተሠጠ መጠን መነገድ አለብን። የእኔ አነሰ የእርሱ በለጠ ማለት የምንችልበት መስከ አይደለም። ስጦታዎቹም ተጠያቂዎች እንደሆነን መርሳት የለብንም። የንግዱም ውጤት በመጨረሻ የጽድቅ ፍሬ እንደሆነ አውቀናል። በትክክል ነግዶ ላተረፈ ጌታም እንዲህ ይላል “አንተ በጎ፥ ታማኝም ባሪያ፤ በጥቂቱ ታምነሃል፥ በብዙ እሾምሃለሁ፥ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው” (ማቴ ፡23)።

# ጥናት ሃያ አንድ
# የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 25
# ክፍል ፫
# የንባብ ክፍል ማቴ 25፡31-46

**ዓላማ፤**

በዓለም መጨረሻ የሚሆነውን፥ ስለ መጨረሻ ዘመን ፍርድ በመማር በየቀኑ ስለምንኖረው ክርስቲያናዊ ኑሮ እንድንጠነቀቅ ማሳሰብ፤

**መግቢያ፤**

በምዕራፍ 24 ደቀ መዛሙርቱ ስለ ዓለም መጨረሻና ስለ ጌታ ዳግም መምጣት ያቀረቡት ጥያቄ በዚህ ክፍል በምናየው የመጨረሻ ፍርድ ይቋጫል።ጌታ የሰዎችን ውለታ የማይረሳና የሚከፍል መሆኑን በታሪኩ ውስጥ እንረዳለን። የጻድቃንን ድል የአመጻኞችንም መጨረሻ እንማራለን።

## የክፍሉ አጭር ማብራሪያ

ይህ ክፍል ጌታ ከመላእክቱ ጋር በክብሩ ዳግመኛ መጥቶ፥ በክብሩ ዙፋን ላይ ተቀምጦ የመጨረሻውን ፍርድ በሰው ሁሉ ላይ እንደሚያደርግ ያሳያል። የተሰጠውን ዝርዝር ሃሳብ ስንመለከት ፍርዱ ተግባር ላይ የተመሰረተ መሆኑን እንመለከታለን። በምንባባችን መሰረት ጻድቃን የሚባሉት በበጎች የሚመሰሉትና በቀኙ የሚቆሙት "ተርቤ አብልታችሁኛል፥ ተጠምቼም አጠጥታችሁኛል፥ ታርዤ አልብሳችሁኛል፥ ታምሜ አስታማችሁኛል፥ ታስሬ ጠይቃችሁኛል" ብሎ የሚላቸው እንደሚሆኑ እንረዳለን። በአንጻሩ ደግሞ የተረገሙ የሚሆኑት፣ በፍየል የሚመሰሉትና በግራው የሚቆሙት ጻድቃን ያደረጉትን ያላደረጉት ይሆናሉ። የሁለቱም ተግባር በቀጥታ በንጉሡ ላይ የተደረገ ሳይሆን በወንድሞቹ ላይ የሆነ እንደነበር ተገልጿል።

ጻድቃን የተባሉት ያደረጉትንና የተቀበሉትን ዋጋ ስንመለከት ወይም የተረገሙ የተባሉት ያላደረጉትንና የተቀበሉትን ፍርድ ስንመለከት 'ድነት በሥራ ነው እንዴ?' የሚል ጥያቄ በውይይታችን ጊዜ ሊፈጠር ይችላል። በመሰረቱ በታሪኩ ውስጥ የጻድቃኑ ተግባር መሰረት ያደረገው ያላቸው

እምነት መሆኑን ከተግባራቸው ማየት ይቻላል። በተጨማሪም ሥራ የእምነት መግለጫ መሆኑን መዘንጋት አይኖርብንም።

ንጉሡ (ጌታ) አድርጋችሁልኛል ወይም አላደረጋችሁልኝም የሚላቸው ነገሮች መሰረታዊ የሰው ልጅ ፍላጎቶች እንደመሆናቸው በየትኛውም ጊዜና ሥፍራ ትክክለኛ በሆነ ልብ የሚደረጉ ናቸው። ከምዕራፍ 24 እና ከምዕራፍ 25 አንጻር ካየነው ደግሞ በተለይ ዓለም ሁሉ የእርሱ የሆኑትንና በሥሙ የተጠሩትን በሚጠላና በሚያሳድድበት ወቅት እንዲህ ያለውን ቸርነት የሚያደርጉ ዋጋቸው ምን እንደሚሆን ልናይ እንችላለን።

"ለዲያብሎስና ለመላዕክቱ ወደ ተዘጋጀው የዘላለም እሳት ከእኔ ተለይታችሁ ሂዱ"(41) ገሃነም እውን ሥፍራ ነው። ለዲያቢሎስና ለመላዕክቱ የተዘጋጀ ቢሆንም፤ ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ሳሉ ጌታን ከደው በመኖራቸው፤ በመጨረሻው ፍርድ ለዘላለም ይገቡበታል።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. በማቴ 25፡31 ላይ ስለ ጌታ ዳግም መምጣት የተሰጠው መግለጫ ምን ይመስላል? የዓለምን ኃጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ከመጣበት ከመጀመሪያ አመጣጥ በምን ይለያል?
2. አህዛብም ሁሉ በፊቱ የሚሰበሰበው ለምንድን ነው? በበጎችና በፍየሎች የተመሰሉት እነማን ናቸው?
3. በቀኙ የሚቆሙት እነማን ናቸው? በግራው ከሚቆሙት በምን ይለያሉ?
4. ንጉሡ በቀኙ የሚቆሙትን እንዴት ባለ መልኩ ነው እያነጋገራቸው የምናየው? ጻድቃን ብሎ ያስጠራቸው ጉዳይ ምንድን ነው?
5. ንጉሡ በግራ ያቆማቸው "ፍየሎቹ" የተረገሙ የሆኑት ከምን የተነሳ ነው?
6. ማቴ 25፡40 እና በቁጥር 45 ላይ የምናየው ምንድን ነው? ይህንን ጌታ በአጽንዖት ከመናገሩ የምንማረው ምንድን ነው?
7. የጻድቃንና የኃጥአን መጨረሻ ምን ይመስላል?

8. ማቴ 25፥41 ላይ ፍየሎቹ የሚሄዱበትን የዘላለም ፍርድ ቦታ፤ ጌታ እንዴት ባለ መልኩ ይገልጸዋል? ከዚህ ምን እንረዳለን?
9. ከዛሬው ጥናት የተለየ የተረዳኸው ወይንም ያስተዋልከው ነገር ካለ አካፍል።

## መደምደምያ

በክፍሉ የመከሊት ክፍፍል፣ የመከሊቱ ንግድና ለጎደላቸው አማኞች ማካፈልን አገናኝተን ማጥናት እንዳለብን ያስገነዝበናል (ከባለፈው ጥናት ጋር እያገናኘን ማጥናት አለብን)። የጽድቅን ፍሬ እና ጽድቅን ገነጣጥለን የምናያቸው ነገሮች አይደሉም። በመጨረሻ ጌታ የራሱ የሆኑትን ይለያል። በዚህ ክፍል አጠንክሮ የነገረን ነገር ቢኖር ህይወታችንና ጸጋዎቻችንን ለሌሎች ማካፈል የጽድቅ ፍሬ እንደሆነ ነው። በሥጋም ካለን ነገር ማካፈል ይጠበቅብናል።

## የማቴዎስ ወንጌል አወቃቀር

በሁለት ይከፈላል፡-

1) የኢየሱስ ማንነት ማቴዎስ 1፡1-4፡11

፩) ማቴዎስ 1:1-25 ለሁለት ይከፈላል፤

ሀ ማቴ 1፡1-17

ለ ማቴ 1፡18-25

፪) ማቴዎስ 2፡1~4፡11 ለሁለት ይከፈላል፤

ሀ* ማቴዎስ 2፡1-23 (ማቴ 1፡1-17 ላይ ሲጨምር)

ለ* ማቴዎስ 3፡1-4:11 (ማቴ 1፡18-25 ላይ ይጨምራል።)

2) የኢየሱስ አገልግሎት ማቴዎስ 4፡1-28፡20

ሀ ድርጊት ክፍል አንድ 4፥12-15 የኢየሱስ አገልግሎት

ሀ* ትምህርት ክፍል አንድ 5:1-7:29

ለ ድርጊት ክፍል ሁለት 8፥1-9:38

ለ* ትምህርት ክፍል ሁለት 10፥1-42

መ ድርጊት ክፍል ሦስት 11፥1-12:50

መ* ትምህርት ክፍል ሦስት 13፥1-58

ሠ ድርጊት ክፍል አራት 14፥1-17:27

ሠ* ትምህርት ክፍል አራት 18፥1-35

ረ ድርጊት ክፍል አምስት 19፥1-22:46 (ሌሎች ይህን ክፍል ከ19-23 መሆን አለበት ይላሉ። የዚህ ጥናት ዝግጅት ክፍል ከዚህ ሀሳብ ጋር አብሮ አይሄድም)

ረ* ትምህርት ክፍል አምስት 23፥1-25:46 (ከላይ እንደተጠቀሰው ማቴ 23 በዚህ ክፍል አይጠቃለልም ይላሉ)

ሰ ድርጊት ክፍል ስድስት 26፥1-28:15

ሰ* ትምህርት ክፍል ስድስት 28:16-20 የደቀ መዛሙርቱ አገልግሎት (ይህ ክፍል ማጠቃለያ ክፍል ትምህርት እንደሆነ የጥናት ዝግጅት ክፍሉ ያምናል)

የእግዚአብሔር መንፈስ ስላስተማረን ስሙ የተባረከ ይሁን! አሜን።

በመቀጠል በአጠቃላይ ከማቴዎስ ወንጌል ጥናት ምን ተማርኩ። ከብዙ ነገሮች አምስቱን ብቻ እንጥቀስ፤

1) ______________________________

2) ______________________________

3) ______________________________

4) ______________________________

5) ______________________________

ከዚህ በታች ባሉት ክፍት ቦታዎች ማንኛውንም ገንቢ ሀሳቦችን በቡድን መሪያችሁ በኩል ወደ ቤተ ክርስቲያኒቷ ትምህርት ክፍል አስተላልፉልን

1) ______________________________
______________________________

2) ______________________________
______________________________

3) ______________________________
______________________________

4) ______________________________
______________________________

5) ______________________________
______________________________

**"የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን። አሜን"** (2 ቆሮ 13፡14)